ለተጨማሪ መረጃ የአካባቢያችሁ የቅሊጣ አማካሪ ጠይቁ ወይም ወደ የአሊያውና ቅሊጣው ሚኒስተር የኢንተርነት ድረገጽ ግቡ።

የአዲስ ገቢዎች ወታደሮችና ተመላሽ ዜጎች መብት መረጃ፦
https://www.gov.il/he/departments/guides/soldiers-olim-rights-guide

የብቸኛ ወታደሮች እርዳታ፦
https://www.gov.il/he/Departments/General/olim_soldiers_lonely_soldiers

- በውጭ አገር ቢያንስ አንድ ዓመት የአካዳሚክ ትምህርት የተማረ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ
- የቅድመ ዝግጁት ገደብ በማይጠይቅ የትምህርት ተቋም መማር የሚፈልግ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ
- የመሀንድስነት ሙያ ወይም ፍቃድ የማግኘት መማር የሚፈልግ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ
- ሁለተኛ ድግሪና የመቀበል ዕጩ/ ኣካዳሚክስ/ ዕድሚያቸው እስከ 40 ዓመት የሆነ የሀይስኩል ትምህርት የጨረሱ፣ በእስራኤል ከፍተኛ ትምህርት የመማር ዕጩ ባይሆኑም

የትምህርቱ ጊዜ 5 ወራት ያህል

ለዲግሪ/ለፍቃድ ትምህርት ዓመታት ከሚደረገው እርዳታ በተጨማሪ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ፕሮግራሞች ሁሉ ወጭ በአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሮዎች አስተዳደር ነው የሚከፈለው::

ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር እርዳታ መጠየቅ

ትምህርት ለመማር ዕጩ የሆነ ሁሉ በአሊያውና ቅሊጣው ሚኒስተር ቢሮ የግል የኢንተርነት ድረ ገጽ ኦን-ላይን ተመዝግቦ በአዲስ ገቢ ዩኒቨረስቲ ተማሪዎች አስተዳደር በኦን-ላይን የምዝገባ ፎርም መሙላት አለበት:: ከምዝገባ በኋላ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት:-

- ወደ የታወቀ የትምህርት ተቋም ለመግባት የመጠየቅ ደብዳቤ
- የእስራኤል አገር ወይም የዉጪ አገር የሀይስኩል ትምህርት ፍቃድ
- የቆዩ የኣካዳሚክ ትምህርት ፍቃዶችና (ዲፕሎማ) የዉጤታቸው ዝርዝር
- ዕድሚያቸው እስከ 22 ዓመት ለሆነ ለትምህርቱ እጩ የሆኑ በመከላከያ ሰራዊት ማገልገላቸው መጀመራቸው ጊዚ ከፍተኛ ትምህርት ስለ ሚማሩ ወደ ፊት ገፍቶ ማራዘም ወይም በመከላከያ ሰራዊት ከማገልገሉ ነጻ የመሆናቸው ፍቃድ::
- ለትምህርት ተቋም ገንዘብ ተከፍሎ ከሆነ የመክፈሉ ደረሰኝ

የእርዳተው ጥያቄ እንደ አዲስ በየትምህርቱ ዓመት ሁሉ ማቅረብ ያስፈልጋል:: በየአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር ድረ ገጽ በሚቀርበው የማቅረቡ የጊዜ መግለጫ መሰረት::

ጥያቄው ለማቅረብ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ።
https://www.gov.il/he/service/online_application_administration_assistance_for_immigrant_students

የአዲስ ገቢ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ በተመለከተ መረጃ ወደ እምከተለው ሊንክ ግቡ:-
https://www.gov.il/he/Departments/Guides/maatefet_students_authority?chapterIndex=1

ለአማርኛ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ።
https://www.gov.il/en/Departments/Guides/am_maatefet_students_authority?chapterIndex=6

ለሙቡቶች መረጃና የአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ።
https://www.gov.il/he/Departments/Guides/student-authority-assitance-list?chapterIndex=5

የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች የእርዳታ ሙበት በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ።
https://www.gov.il/he/Departments/General/ethiopian_jews_students_scholarships

ከከፍተኛ ትምህርት ኮሚቴ (ኮውንስል) እርዳታ

የከፍተኛ ትምህርት ኮሚቴ እርዳታ እስራኤል ከገቡ 15 ዓመት ከሆናቸው ትምህርት ለሚጀምሩ አዲስ ገቢዎች ነው የሚሰጠው- በመከላከያ ሰራዊትና ብሄራዊ አገልግሎት ያገለገሉበት ጊዜ ሳይጨምርና በእስራኤል

ለተወለዱትም ጭምር::

እርዳታው የሚከተለውን ያካትታል:-

- ወታደራዊ/ብሄራዊና ዜጋዊ አግልግሎት ላገለገሉ ወጣቶች መረጃ በቀላል እንዲያገኙ ማድረግ
- ለሳይከመትሪክ መዘጋጀት ኮርስ ክፍያ
- በአንደኛው ዲግሪ ትምህርት ጊዜ ሁሉ (ልኩ የተወሰነ) እርዳታ
- አንደኛ ዲግሪ ለሚማሩ የቅድመ ዝግጁት ከፍያ ለእርዳታ (የኣካዳሚክ የትምህርት) ማበረታቻ እገዛ፣ የመማር እስትራቴጂዎች፣ በቤት ስራ እርዳታ፣ ወደትምህርት የመግባት ፈተና ዝግጁት፣ የመኖሪያ ሆስተል ወይም የመጓጓዣ እርዳታ፣ በሳየኮሌጂስት እንክብካቤ ክፊያ በከፊል መርዳት፣ የመማር ችግር መፈተንና ወዘተ::
- ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የአመራር ፕሮግራም
- ከፍተኛ ዉጤት ለሚያመጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፕሮግራም (በመከታተል እርዳታ)
- የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በኣካዳሚክ ስታፍ አባል የመሆናቸው ፕሮግራም (ለስራ ለሚቀበልዋቸው ተቋማት ስራ ይሰጥዋቸው ዘንድ የገንዘብ ድጎማ ማድረግ)

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለዉ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ድረ ገጽ ሊንክ ግቡ።
https://che.org.il/%D7%9E%D7%9C%D7%92%D7%95%D7%AA-%D7%99%D7%95%D7%A6%D7%90%D7%99-%D7%90%D7%AA%D7%99%D7%95%D7%A4%D7%99%D7%94/

ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ኮሚቴ ጋር ግንኙነት የመፍጠር ዘዴዎች:-

ስልክቁጥር:- 02-5094544 (ማክሰኞብቻ ከ10:00 እስከ 13:00)

ፋክስ:- 02-5094545

ኢሜል:- meida@che.org.il

በመከላከያ ሰራዊት አገልግሎት

የእስራኤል ዜጋ ወይም ኑዋሪ የሆኑ ዕድሚያቸው 18 ዓመት እንደደረሰ በመከላከያ ሰራዊት የማገልገል ግዴታ አለባቸው:: የወታደርነት አገልግሎት ቁም ነገሩ የእስራኤል ጸጥታ ማስከበርና መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የዜግነት መብትም ነው:: እንዲሁም የወታደርነት አገልግሎቱ በእስራኤል ማህበረሰብ የማዋሀድ ዕድል ይሰጣል:: ከወታደርነት አገልግሎት ነጻ መሆን በተመለከተ በየወታደርነት አገልግሎት ህግ በዝርዝር ተጠቅሷል::

ከወታደርነት ምልመላ በፊት

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የቅድመ ዝግጁት ፕሮግራም

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ከመከላከያ ሚኒስተር ጋር በመተባበር ከዓለሙ ሀገራት የመጡት ወጣቶች ይሁዲዎች በመከላከያ ሰራዊት የማገልገላቸው ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ የአንድ ወር የዝግጅት ኮርስ ይደርግላቸዋል:: (ኮርሱ ወታደርነት ከመገባታቸው በፊት አንድ ዓመት ቀድሞ አዲስ ገቢ ለሆኑ ነው የሚደረገው):: ፕሮግራሙ ወታደርነት የመመልመሉ ፕሮግራም ፊሲካሊና መንታሊ መዘጋጀት ፣ ከእስራኤል ማህበረ ሰቡ ትውውቅ ፣ የይሁዲነትና ጽዮናዊነት ምንነት ማጠናከር ፣ ሀገሪቱና የታሪካዊ ቦታዎችዋ ቅርሶችን ማወቅ ፣ የዕብራይስጥ ቋንቋን ማሻሻልና ማዳበር ሲሆን ወደ ፕሮግራሙ ለመጨመር ከቅሊጣው አማካሪ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል::

ወታደራዊ ቅድመ ዝግጁት

በወታደርነት ማገልገል ዕጩ የሆኑ ሁሉ በወታደራዊው ቅድመ ዝግጁት ፕርግራም መመዝገብ ይችላሉ::

- **የአካዳሚክ ቅድመ ሁኔታዎች፦**

  ተማሪው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆን አለበት፡፡

  - የሀይስኩል ፍቃድ ወይም የቅድ መዝግጂት ትምህርት የማጠናቀቅ ፍቃድ የመቀበል መብት ያለው
  - በአዲስ ገቢዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር እውቅና ባለባቸው ተቋማት ተቀባይነት አግኝቶ የሚማር ከሆነ (ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላትም እውቅና ባላቸው)
  - የዩኒቨርሲቲ ተማሪው ዲግሪ ከሌለው /እርዳታው የሚሰጠው ድግሪ ተመሳሳይ ፍቃድም ከሌለው፡ ፡ከውጪ አገር ይዞት የመጣ አንደኛ ድግሪ ያለውና በስቴም(ስታትስቲክስ፤ማትስ፤ኢንጂነሪንግና የኮምፒውተር ሳየንስ) ሞያ ተጨማሪ አንደኛ ድግሪ መማር የሚፈልግ ሳይጨምር፡፡
  - ከአንዱ የትምህርት ዓመት ወደ ተከታዩ መሸጋገሩ ተገቢ መሆን፡፡

በክፍቱ ዩኒቨርሲቲ የሚማሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቅድመ ሁኔታው የተለየ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ።
https://www.gov.il/BlobFolder/generalpage/students_eligibility/he/OpenUniversity.pdf

በትምህርቱ ሂደት ላይ ትምህርት ማቋረጥ ይፈቀዳል-የአካዳሚኩ የትምህርት ጊዜ ለሁለት ዓመት ያህል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አስተዳደሩ ክፍያ ዲግሪ/ፈቃድ ያገኙ ተጨማሪ ዲግሪ/ፍቃድ መቀበል የሚፈልጉ ሁሉ ትምህርታቸው ማቋረጡ በተወሰነ ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው መሆኑ ማክበር/መቀበል አለባቸው፡፡

ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሁሉ አጠቃለይ መረጃ ብቻ ሲሆን ወሳኙ ሁኔታውና በወቅቱ የሚኖሮው ትእዛዝ ነው፡፡ እርዳታው በጀት በመኖሩና በየዓመቱ በሚሰጠው ትእዛዝ ይወሰናል (የወቅቱ ትእዛዝ 403)፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪው ተያያዥ የሆኑ ወጪዎች ሁሉ መክፈል አለበት። እንደ በትምህርት ተቋሙ የመመዝገብ ፣ የጥበቃ ፣ የፈተና ፣ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ድርጀት ፣ የቤት ክራይ ፣ የኢኮኖሚና የግል ወጪዎች የመሳሰሉ ሁሉ ክፍያዎች፡፡

የኑሮ ወጪ (ስኮላርሺፕ)

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የአዲስ ገቢ አስተዳደር ተማሪዎቹ ትምህርት ከጀመሩበት ወቅት ጀምሮ በሚማሩበት ጊዜ ለ9 ወራት በየወሩ የ600 ሽቀል እርዳታ ያደርጋል፡፡ እርዳታው ቢያንስ በዓመት ወይም በሴመስተር 50% ለሚማሩ ነው የሚሰጠው፡፡

በክፍት ዩኒቨርሲቲው የሚማር ተማሪ በሴመስተሩ ቢያንስ እስከ 12 ነጥብ የሚማር ከሆነ ነው እርዳታው የሚገባው፡፡

ላልተማረበት ጊዜ የስኮላርሺፑ የተከፈለው እርዳታው በሙሉ ለመመለስ ይገደዳል፡፡ የህክምና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች (ዶክቶር ለመሆን) በሚማሩባቸው ዓመታት ሁሉ እርዳታው ይሰጣቸዋል፡፡

እርዳታው የማይገባቸው ተማሪዎች፦

- ትምህርታቸው ሙሉ ያልሆነ (ከትምህርቱ ፕሮግራም 50% ያነሰ)የሚማሩ፡፡
- የዲግሪ ማሻሻያ ትምህርት የሚማሩ በተለይ ደግሞ ሁለተኛ ድግሪ ወይም ከዲግሪ በኋላ ፍቃድ ለመቀበል የሚማሩ፡፡
- በበጋው ሴመስተር የሚማሩ፡፡

አፈቅ የሚባል ፕሮግራም

አፈቅ ፕሮግራም የአዲስ ገቢዎቹ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር በስራ ከፍ ያለውጤት ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙ የስራ ሙያዊ ውጤት ከፍ ያለ እንዲሆን የሚንከባከብና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እየቆየ ከፍ እያለ

በሚመጣ የንግድ ስራ ፤ በህዝባዊና አካዳሚክ ረገድ ሁሉ እንዲማሩ ለማድረግ የሚረዳ ነው፡፡

ፕሮግራሙ የአዲስ ገቢዎቹ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር ሲሆን ባለ ሞቲቬሺን እና ከችሎታቸውና ከትምህርት ብቃታቸው ጋር የሚመጣጠን ስራ ለማግኘት ፍላጎት ላላቸውና በስራቸው በጣም ጥሩ ውጤት ለማምጣት ለሚጣጣሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሮዎች ነው፡፡

ፕሮግራሙ ከሁለት ክፍሎች የተሰራ ነው። በመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎቹ በስራ መስማራት በተመለከተ በየሳምንቱ በሚካሄደው ስልጠና ይሳተፋሉ፡፡ በሁለተኛው ክፍል ተማሪዎቹ በበጎ አድራጊዎች በሚሰጥ ይግል ትምህርት እርዳታ ይደረግላቸዋል፡፡ በፕሮግራሙ ተሳታፊዎቹ በሚማሩት ትምህርት ከፍተኛ እውቀትና ስራ ባላቸው በኩል፡፡ እርዳታ ሰጪዎቹ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቁ በሆነ ስራ ለመሰራት በሚዘጋጁበት ወቅት የስራና ማህበራዊ ቡድን በመፍጠር ይረዳሉ፡፡

ፕሮግራሙ የመጀመሪያ የትምህርት ዓመት ለሚማሩ አይደለም ፤ ዲግሪ ለመጨረስ 3 ሴመስተር ለቀረባቸው ነው፡፡ በፕሮግራሙ ለመመዝገብ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ። https://shahak2021.wixsite.com/ofek

የዕብራይስጥ ትምህርትና ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የመዘጋጀት ፕሮግራም

አዲስ ገቢ ወጣቶች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በሚማሩበት ትምህርት የመማር መብት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በኡልፓኑ መማር መቀጠሉ (ኡልፓን አሌፍ) ለአምስት ወር ያህል ነው፡፡

የበጋ ኡልፓን

የአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር ከትምህርት ሚኒስተር የትላልቅ ሰዎች (በዕድሜ የገፉ) ትምርት ክፍልና የአካሚክ ተቋማት ጋር በመተባበር በበጋው ወራት ለወጣት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የዕብራስጥ ትምህርት እንዲማሩ ያደርጋል፡፡

ለፕሮግራሙ ተስማሚ የሚሆነው ማን ነው

- በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር የመረዳት መብት ያላቸውና ከፍተኛ ትምህርት መማር የሚፈልጉ አዲስገቢዎች
- በአካደሚክ ፕሮግራም ቅድመ ዝግጂት የተሳተፉና የጨረሱ
- በአካዳሚክ ተቋማት የሚማሩ እና ከዕብራይስጥ ትምህርት ነጻ ወደ እሚያደርግ ደረጃ ያልደረሱ በአስተዳደሩ መብት ያላቸው ተማሪዎች
- ዕድሚያቸው እስከ 30 ዓመት የሆነ የአካዳሚክ ምሁራንና ዶክተሪቶች

የበጋው ትምርት 5 ሳምንታት ነው፡፡

ከፍተኛ ትምህርት መማር የምትፈልጉ ሁሉ በአዲስ ገቢዎቹ የቅድመ ዝግጂት ፕሮግራም ከሁለቱ በአንዱ ብትሳተፉ ይመረጣል፡፡

የዩኒቨርቲ የአዲስ ገቢዎች ዝግጂት

ለአንደኛ ዲገሪ ትምህርት መመዝገብ አብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች በአዲስ ገቢዎች ቅድመ ዝግጂት መጨረስ ይገድቡታል፡፡ ይህ ግዴታ ከእስራኤሉ የሃይ ስኩል መማር ፈቃድ እኩል ያልሆነ የሃይ ስኩል ትምህርት የመጨረስ የታወቀ ፈቃድ ያላቸው ይመለከታል፡፡ አብዛኛዎቹ ኮሌጆችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪ ለመቀበል ዝግጂቱ አይጠይቁም፡፡ የትምህርቱ ጊዜ የአካዳሚክ ሙሉ የትምህርት ዓመት ነው፡፡

የቅድመ አካዳሚክ ፕሮግራም

ፕሮግራሙ ቅድመ ዝጊጂት የማድረግ ግዴታ ለሌላቸው አዲስ ገቢዎች ነው፡፡

- ከእስራኤል የ12ኛ ክፍል ትምህርት ፈቃድ እኩል የሆነ የ12ኛ ክፍል/የሀይስኩል ትምህርት የመጨረስ ፈቃድ ያለው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ

የትምህርት ሚኒስተር የአገልግሎት ማዕከል

የትምህርት ሚኒስተር ቢሮ የመረጃና እርዳታ ማዕከል አለው። ተማሪዎች ወደ እሚያስፈልጋቸውና የሚመጥናቸው መምራት መረጃ መስጠት ፣ ለወላጆችና ተማሪዎች የስሜት እርዳታ ማድረግ ፣ የህዝብ ጥያቄ መቀበል ፣ ቴክኒካዊና ሌላ።

የማዕከሉ ዋናው የስልክ ቁጥር፦ 073-3983960 / *6552

የተጠየቀው አገልግሎት ለመቀበል፣ በጥሪ ራውተር ውስጥ ባለው የቁጥር ዝርዝር መሰረት በስልኩ መስመር አስፍላጊውን ቁጥር ይጫኑ።

አዲስ ገቢ ተማሪዎች

አዲስ ገቢ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቶች የመቀበል መረጃና የሚረድዋቸው አዲስ ገቢ አስተናጋጆች የስልክ ቁጥሮች አዲስ ገቢ ተማሪዎች በሚለው የትምህርት ሚኒስተር ቢሮ በክፍለ ሀገሩና ዋናው ማዕከል በሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል።
https://parents.education.gov.il/prhnet/gov-education/studies/newcomers-rights

ክፍሉ ስልክ ቁጥር፦ 073-3931543/2

ኢሜል፦ agafklitato@education.gov.il

ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ

ሀገረ እስራኤል በከፍተኛ ትምህርት (ከሀይ ስኩል በላይ) የትምህርት የተለያዩ ኣማራጮች እንዳልዋትና ዜጎች እንዲማሩ ትፈልጋለች። የከፍተኛ ትምህርቱ ተቋማት ዩኒቨርሲቲዎችና ኮለጆች ይገኙባቸዋል። ዩኒቨርሲቲዎቹ የተለያዩ ሰፊ የአካዳሚክ ትምህርት አይነቶች እንደሚያስተምሩ በማሳወቅ ለተማሩት ዲግሪዎች ይሰጣሉ። ኮለጆቹ በትምህርት ላይ ከተጠቀሰው አነስ ያለ አይነት እንዳሉዋቸው ያሳውቃሉ (በአጠቃላይ ኮሎጆች የተወሰነ የትምህርት ረገድ ነው ያላቸው)። ረገዶቹ በሁለት አይነት ይከፈላሉ። የአካዳሚክ የሆኑ ኮሎጆች የአካዳሚክ ትምህረት ያስተምራሉ (እንደ የምርምር ፣ ኢኮኖሚ የመሳሰሉ ሳብጀክቶች የሚያስተምሩ ሲሆን አንደኛና ሁለተኛ ዲግሪ ይሰጣሉ። ይዘታቸው የሙያ ትምህርት ማስተማር የሆነ ኮለጆች ቴክኖሎጂ ፣ ኮምፒውተር ፣ የህክምና ሙያ፣ የእጅ ሙያ ፣ ሙዚቃና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ የሚያስተምሩ ሲሆን ኣካዳሚክ ያልሆነ ፍቃድ ነው የሚሰጡት። ድግሪ ከመስጠትና ወደ የስራው አለም የመግባቱ ዕድል ሰፊ ከማድረግ በተጨማሪ ትምህርቶቹ በእስራኤል ህብረተሰብ የመንቀላቀሉ አማራጭ አላቸው።

የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከመንግስታዊ አካላት የሚደረግላቸው እርዳታ ዝርዝር እንደሚከተለው ሲሆን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጂቶችም እርዳታ የሚሰጡ ከሆነ ማጣራት አስፈላጊ ነው። ይህን በተመለከተ ከአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የአዲስ ገቢዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር እና የማህበራዊ ጉዳዮች ባለ ሙያዎች (ከሶሻል ዎርከሮች) ተጨማሪ መረጃ መቀበል ይቻላል።

የአስተዳደሩ ለአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የአዲስ ገቢዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ክፍል ሲሆን ወጣት አዲስ ገቢዎች በእስራኤል አካዳሚክ ትምህርት እንዲማሩና በትምህርት ዘርፎች የማሰማራታቸው ሀላፊነት አለው።

ከፍተኛ ትምህርት ከፍ ወዳለ ደረጃ የመድረስ ቁልፍ መሆኑ በማወቅና መረዳት አስተዳደሩ ለአዲስ ገቢዎች ወጣቶች የሚያደርገው እርዳታ አስፋፍቷል።

የአዲስ ገቢዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር በተለያዩ የትምህርት አይነቶች አዲስ ገቢዎችን እንዲማሩ ይረዳል። በዩኒቨርሲቲ፣ የአካዳሚክ ኮሌጆች፣ የአስተማሪዎች ስልጠና ኮሌጆች ፣ የተከኖሎጂ ተቋማት እና

እንዲሁም የአካዳሚ ትምህርት ቅድመ ዝግጂት ፣ የአዲስ ገቢዎችን ቅድመ ዝግጂት፣ የአንደኛና ሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ፣ የአካዳሚ ትምህርት ያላቸው ሙያ ወደ ሌላ የመለወጥ ትምህርት ፣ ማሀንዲስነትና የተለያዩ ምርጥ ምርጥ የሆኑ የትምህርት ፍቃድ የሚያስገኙ የትምህርት አይነቶች። የኢትዮጵያ ትውልድ ለሆኑ የሚያደረገው እርዳታ በጊዚያዊው (403) ትእዛዝ የተመሰረተ ሲሆን በበጀት ይገደባል።

እርዳታው የሚደረግላቸው የትምህርት አይነቶች

- የአንደኛ ድግሪ ትምህርት ወይም የትምህርት ፈቃድ የማግኘት ወይም የመሀንዲስነት ትምህርትና እንዲሁም በመንግስት (ታሪፍ) የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት።
- አመች የሆነ የትምህርት አይነት በመምረጥ-በዕብራይስጥ ቋንቋ፣ እንግሊዘኛ ወይም አማሪኛ የትኛው እንደሚመረጥ/እንደሚሻል ምክር መስጠትና አቅጣጫ ማሳየት።
- የአካዳሚክ (ከፍተኛ) ትምህርት ገና በኡልፓኑ ትምህርት እያሉ ማዘጋጅት፣ የአካዳሚክ ትምህርት ቅድመ ዝግጂት፣ ወይም ልዩ የሆኑ (ከፍያቸው እንደ ወታደርነት ያገለገሉ በጀት የሚከፈል ልዩ የሆኑ የቅድመ ዝጂት ትምህርቶች)።
- በአካዳሚው ትምህርት እንደ በግል ወይም በቡድን የትምህርት (በቤትስራ) እርዳታ ማድረግ።
- በእርዳታ ሰጪና ባለሙያ የሆኑት በኩል በግል እርዳታ ማድረግ።
- በማህበራዊና ባህላዊ ረገድ እንቅስቃሴ።
- በማህበረሰብና ማህበራዊ አገልግሎት ፕሮጀክት መሳተፍ።
- የኑሮ ወጭ ክፊያ (ስኮላርሺፕ) (መብት ላላቸው)።
- በትምህርቱ ሂደት ላይ እንግሊዘኛና ዕብራይስጥ የመማር ፍጆት ክፊያ።
- ደረጃው የአካዳሚክ ዕብራይስጥ ቋንቋ የሆነ የማወቅ ፈተና የዝግጂት ኮርስ እርዳታ።
- አፈቅ በተባለው የስራ ቅድመ ዝግጂት የአመራር ፕሮግራም መሳተፍ።

የእርዳታው ልክ

የአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር በትምህርቱ ዓመታት ደረጃ መሰረት ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አዲስ ገቢዎች በ-የትምህርታቸው ክፍያ እርዳታ ያደርጋል። እርዳታው በየዓመቱ በተማሪው ትምህርት መሰረት በመንግስታዊው (ታሪፍ) ሙሉ በሙሉ (100% የትምህርት ክፍያ) ነው።

እርዳታውን የመቀበል ቅድመ ሁኔታ

- **ስታቱስ፦ አዲስ ገቢ** ፣ የአዲስ ገቢዎች ልጅ ፣ አዲስ ገቢ ዜጋ ፣ ተመላሽ ታዳጊ ልጅ።

ለኢንጂነሪንግ ትምህርት ብቻ- ሁለቱ ወላጆቹ ከ1.1.1980 በኋላ እስራኤል የገቡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ

- **የመቀበሉ መብት ጊዜ፦** ከእትዮጵያ እስራኤል የገባ አዲስ ገቢ አዲስ ገቢ ከሆነበትጊዜ አንስቶ እስከ 15 ዓመት። መሀሉ ላይ ወታደርነት/ብሄራዊ አገልግሎት ካገለገሉ የማገልገሉ ጊዜ በመብቱ ጊዜ ውስጥ አይቆጠርም-በዩኒቨርስቲ ትምህርት ተማሪዎች አስተዳደር አካሄድ መሰረት።
- **ትምህርቱ ሲጀመር በዛ ቢባል የዕድሜ ልክ፦**
  - እስከ 28 ዓመት የአዲስ ገቢዎች ቅድመ ዝግጂት/አንደኛ ዲግሪ/ፍቃድ/መሀንዲሶች።
  - እስከ 30 ዓመት ዕድሜ የአካዳሚክ 2ኛ ትምህርት ቅድመ ዝግጂት ላጠናቀቁ፣ የአካዳሚክ ትምህርት ቅድመ ዝግጂት (በአካዳሚክ ትምህርት የመማር ፕሮግራም ወይም የአንደኛ ዲግሪ/ ፈቃድ/ መሀንዲስነት ትምህርት መማር መቀጠል ለሚፈልጉ የአዲስ ገቢዎች ቅድመ።
  - ዝግጂት ዕድሚያቸው እስከ 40 ዓመት ሁለተኛ ዲግሪ ለመማር/የሞያ ለውጥ ትምህርት ለባለዲግሪዎች/ ከአንደኛ ዲግሪ በኋላ ፈቃድ።

ትምህርት

የትምህርት ግዴታ ህገ መንግስት

የትምህርት ግዴታ ህግ (የ1949 ዓ/ም) የአስተዳደግ ግዴታ ህግ በመባልም የሚታወቀው የትምህርት ህግ መሰረት በእስራኤል ልጅ ሁሉ እንዲማር ያስገድዳል። ህጉ አሁን ባለነበት ወቅት ዕድሚያቸው ከ3 እስከ 17 ዓመት የሆነ ልጆች ይመለከታል። ልጅ በቤት በግል እንደማስተማር በመሳሰሉ ልዩ በሆኑ የጥያቄዎች ሁኔታ በትምህርት ቤት ከመማር ነጻ መሆን ይቻላል። በህጉ መሰረት ትምህርት ከሚጀምርበት ዕድሜ ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርቱ ያለ ክፍያ-በነጻ ነው። ዕድሚያቸው ከ3 ዓመት በታች የሆነ ልጆች የትምህርት ግዴታው ህግ አይመለከታቸውም። ግን ዕድሚያቸው ዝቅተኛ ለሆኑት ልጆች የቀን ሆስቴሎች የሚባሉ በስራ ሚኒስተር ቢሮ ቁጥጥር ስር የሆኑ (ለፈላጊዎች) በክፍያ የሚሰሩ የልጆች መጠበቂያ-መዋያ ቦታዎችም አሉ።

በትምህርት ቤት የመመዘገብ መረጃ "መርካዝ ቅሊጣ የመጀመሪያ እርምጃዎች" የሚለውን መረጃ በዚሁ መጽሄት መጀመሪያ ላይ ታገኛላችሁ።

ለአዲስ ገቢዎች ተማሪዎች እርዳታ

ለአዲስ ገቢና ተመላሽ ዜጎች እርዳታና የ12ኛ ክፍል ፈተና እርዳታ ሊገባቸው ይችላል። የእርዳታዎቹ ዝርዝር የትምህርት ዓመቱ በጀመረ ቁጥር (በየዓመቱ) በትመህርት ሚኒስተር ዋና ስራ አስኪያጁ (ዳይረክቶሩ) መግለጫ ይጻፋል።

ወደ የትምህርት ሚኒስተር ዋና ስራ አስኪያጁ መግለጫው በሚከተለው ሊንክ ግቡ፡-
https://apps.education.gov.il/Mankal/Default.aspx

የእርዳታው ዝርዝር የያዘ የዋናው ስራ አስኪያጁ ጽሁፍ ስም፡ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች ተማሪዎች በትምህርት ተቀብሎ ማስተናገድና ማዋሀድ ይባላል። ለአዲስ ገቢዎች ተማሪዎች ሊደርሳቸው የሚችል እርዳታ፡-

በትምህርት ወጪ ክፊያ መሳተፍ

አዲስ ገቢ ተማሪዎች ለትምህርት በሚከፍሉት ክፍያ ከፊሉ እስራኤል ከደረሱ ለ15 ዓመታት ያህል በእርዳታ ሊሰጣቸው ይችላል። (የትምህርት መጻህፍት ፣ የትምህርት መሳሪያ ፣ ለጉብኝት እና ለመሳሰሉት በሚከፈለው ክፍያ)። እርዳታው ለመቀበል የትምህርት ቤቱ ስራ አስክያጅ መጠየቅ።

የእርዳታው ሙሉ መብት በአሁኑ ወቅት እስከ ስንት እንደሆነ ለማወቅ ወደ እሚከተለው የትምህርት ሚኒስተር የኢንተርኔት ድረ ገጽ ግቡ፡-
https://mosdot.education.gov.il/students/immigrants/absorption_basket

በ-የቀኑ ሆስቴሎችና የህጻናት መዋያ ወጪ የሚከፈል ክፍያ እርዳታ

በመርካዝ ቅሊጣ (ጊዚዊው መጠለያ ማዕከሉ) የሚኖሩ ለ-የቀኑ ሆስቴሎችና የቀን የህጻናት መዋያ መዋዕለ ህጻናት ክፍያ በመንግስት እንዲከፈልላቸው የሚያደርግ መብት አላቸው። ክፊያው ልጆቹ በሆስቴሉ በየቀኑ መዋላቸውና መሳተፋቸው ሙሉ ከሆነ ነው።

በመርካዝ ቅሊጣ (በጊዚዊው መጠለያ ማዕከል) የማይኖሩ አዲስ ገቢዎች በተለመደው ክራይተሪያ መሰረት የከፍያ ቅናሽ ይገባቸው ይሆናል።

በቢጡዋኽ ልኡሚ (ብሄራዊ ዋስትና) ተቋም በኩል ለትምህርት በስጦታ የሚለገስ እርዳታ

የቤተሰባቸው መሪ አንድ ለሆነ ወላጆች (በአንድ ወላጅ የሚተዳደሩ) እና አራት ልጆች ላልዋቸውና ከዛም በላይ ልጆች ላለልዋቸው ቤተሰቦች የቢጡዋኽ ልኡሚ ተቋም (የብሄራዊ ዋስትና ተቋም) ለትምህርት በሚከፍሉት ክፍያ ይሳተፋል። ተረጂዎቹ እርዳታው የሚደርሳቸው ከሚከተሉት አንዱ የሚከፈላቸው ከሆኑ ነው።

የአጠቃላይ አካለ ስንኩልነት ፤ የገቢ መረጋገጫ ፤ ምዞኖት (ባልና ሚስት ከተፋቱ በኋላ ለልጆች ማስደጊያ የሚከፈል ገንዘብ) ፤ የጠሮታ ወይም ባል ወይም ሚስት የሞቱባቸውና ለሟቹ/ቹዋ ይከፈል የነበረ ከፍያ ሲሆን የከፍያው ክራይተሪያ የሚያሟሉ ከሆነ ነው። እርዳታው የሚገባቸው ተጨማሪ ባለ መብት ያለ ሚስት/ ያለ ባል ለብቻው/ዋ የገቢ ማረጋጋጫ ክፍያ የሚከፈለው/ላት ፤ በእስራኤል ከዓመት በላይና ከሁለት ዓመት በታች የሚገኝ/የምትገኝ አዲስ ገቢ እና ያለ ወላጆች እስራኤል የገባ ልጅ ብቻው/ብቻዋ የሚያሳድግ/የምታሳድግ እና ወ.ዘ.ተ ናቸው።

የገንዘቡ ስጦታ ዕድሚያቸው ከ6 ዓመት እስከ 18 ዓመት ለሆነ በየትምህርቱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ወደ ባለ መብቱ የልጆቹ ክፍያ የሚገባበት የባንክ ሂሳብ ቀጥታ በመላክ ነው የሚለገሰው።

ስጦታው የመቀበል መብት ካላችሁ ለማወቅ ወደ እሚከተለው የቢጡዋኽልኡሚ (የብሄራዊ ዋስትናው ተቋም) የኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ።
https://www.btl.gov.il/benefits/children/%D7%9E%D7%A2%D7%A0%D7%A7%20%D7%9C%D7%99%D7%9E%D7%95%D7%93%D7%99%D7%9D/Pages/default.aspx

ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የትምህርት ልዩ ስዓታት መስጠት

አዲስ ገቢ ተማሪዎች የዕብራይስጥ ቋንቋ እንዲያውቁና በትምህርታቸው የትምህርት ተጨማሪ ስዓታት በመጨመር ለማጠናከር ያህል ልዩ ተጨማሪ ስኣታት ሊገቡዋቸው ይችላሉ። የሚገቡዋቸው የትምህርት ስዓታት በተለያዩ ክራይተሪያዎች መሰረት ነው የሚሰጡት።

የኢትዮጵያ ቤተ እስራኤል "ፕሮየክት ልኡሚ" ለአዲስ ገቢዎች ትምህርታቸው የማዳበር እርዳታ ያደርጋል። የእርዳታው አላማ ተማሪዎቹ ወደ የአካዳሚክ ትምህርት (ከፍተኛ ትምህርት) ሊገባቸው የሚችል ሙሉ የ12ኛ ክፍል ትምህርት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። ይህ ፕሮግራም ከኢትዮጵያ ቤተ እስራኤል ጋር (ከተወካዮች ጋር) በመተባበር ነው የሚሰራው።

እንዲሁም የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች በትምህርት እንዲሰለጥኑ የሚረዱ ያኤል እና ፕሌ የተባሉትና ሌሎች ፕሮግራሞች አሉ።

ለሚገባቸው የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች (የፋይናልስ ተፈታኞች) በፈተናው ማቃለል

የ12ኛ ክፍል ትምህርት ተፈታኞች አዲስ ገቢዎች በልዩ ፈተና መፈተን ይችላሉ። ልዩ መፈተን የሚባለው እንደ ልዩ ጥያቄዎች ፣ የፈተና ጊዜ ማራዘም ፣ ነጥብ መጨመር፣ ማንበብ ፣ የመጻፍ (የጽሁፍ) ስህተት ያለ መቆጣጠር ፣ በዲክሺነሪ መጠቀም የመሳሰሉ ናቸው። በዚህ ፈተና የመፈተኑ መብትና የፈተናው አይነት በባለ መብቱ ሁኔታ መሰረት ነው የሚወሰነው። ልዩ ፈተና በተመለከተ በትምህርት ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከተውን መጠየቅ።

የልዩ ፈተናው መብት አዲሱ ገቢ እስራኤል ከገባ ለ12 ዓመት ወይም የተፈታኙ ዕድሜ 25 ዓመት እስከ ሆነበት ይቆያል። ከዕድሜውና 12 ዓመቱ ቆይቶ በሚደረሰው ይወሰናል።

በአዳሪ ትምህርት ቤት ለተማሩ ተማሪዎች የገንዘብ ስጦታ

በአዳሪ ትምህርት ቤቶች ተምረው ትምህርታቸው በተለመደው ትምህርትቤት ቀጥለው ለሚጨረሱ ተማሪዎች እስከ በመከላከያ ሰራዊት ወታደራዊ አገልግሎት መግባታቸው ወይም ብሄራዊ አገልግሎት እስከ መጀመራቸው ድረስ ባለው መሸጋገሪያ ጊዜ የኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ እርዳታ ያደርግላቸዋል። የመጀመሪያው ስጦታ 12ኛ ክፍል ለጨረሱ ሁለተኛው ስጦታ በመከላከያ ሰራዊት ለማገልገል ለሚገቡ ብቻ ወይም ብሄራዊ/ሲቪላዊ አገልግሎት ለሚያገለግሉ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ እስራኤል ፣ አዲስ ገቢና የአዲስ ገቢ ልጆች የእርዳታው ጥያቄበሚቀርብበት ጊዜ ወይም አዲስ ገቢ ከሆኑና እስራኤል ከገቡ 15 ዓመት ሳያልፋቸው ከሆነ ነው እርዳታው የሚገባቸው። እርዳታው በጀት በመኖሩ ይገደባል። እርዳታው ለመቀበል የቅሊጣው አማካሪ ጠይቁ።

ከትምህርት ሚኒስተር ጋር ግንኙነት መፍጠር

የትምህርት ሚኒስተር የኢንተርነት ድረ ገጽ፡- https://edu.gov.il/.

የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት

የጤና ጣቢያዎች የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት

እየአንድ አንዱ የጤና ጣቢያዎች 24 ስኣታት ሙሉ የሚሰሩ የስልክ ማዕላት ይገኙባቸዋል፡፡ የስልክ ማዕከላቱ ስልክ ቁጥሮች አድራሻና የስልክ ቁጥር በሚለው አንቀጽ ይገኛል፡፡ ከአስፈለገ በስልኩ በኩል ወደ ሆስፒታል መላክ ይቻላል፡፡ እንዲሁም የጤና ጣቢዎቹ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት በለሊት ፤ በሰንበት (ሻበት) እና በባዓላት የሚሰጡ ማዕከላት በተወሰኑ ቦታዎች ይገኙባቸዋል፡፡ አስቸኳይ ህክምናዎቹ የህክምና ምርመራ ፤ የላቦራቶሪ ምርመራ ፤ የኤክስ ሬይስና መድሃኒት መሰጠት የመሳሰሉ ናቸው፡፡ አገልግሎቶቹ ያስከፍላሉ-ግን በተወሰነ ሁኔታ ከክፍያ ነጻ መሆን ይቻላል፡፡

ሀኪም (የህክምና ዶክቶር) ወደ ቤት መጠራት

ሀኪም ወደ ቤት የመጥራት አማራጭም አለ፡፡ የዚህ አይነት አገልግሎት (ናጣሊና ቢቁርሮፌ) በሚባሉት የግል ድርጂቶች በኩል ነው የሚሰጠው፡፡ የጤና ጣቢያቸው ከየትኛው ድርጂት ጋር እንደሚሰሩ ከነሱ ዘንድ አጣሩ- አገልግሎቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የክፈያው ብዛት(ልክ) ህክምናው በተሰጠበት ስኣትና እንደ የህክምና ጣቢያቸው ከድርጂቱ ጋር ያለው ስምምነት ይወሰናል፡፡ ማሽለማ የሚባል ዋስትና ያለቸው አባላት ክፍያቸው ቅንሽ-እንስተኛ ነው፡፡ ሀኪም ወደ ቤት ለመጥራት አገልግሎቱ ወደ እሚሰጠው ድርጂት ቀጥታ መጠየቅ፡፡ ለእራሱ በእራሱ የመስራት (የመንቀሳቀስ) በጣም ችግር ያለው ባለ ዋስትና አባል ክፈያ ያለመጨመር ወደ ቤቱ ረዳት ይላክለታል.

የአስቸኳይ ጊዜ የጤና ጣቢያዎች

ከጤና ጣቢያዎቹ በተጨማሪ ከነሱ ጋር ስምምነት በማድረግ የሚሰሩ የግል የአስቸኳይ ጊዜ የጤና ጣቢያዎች አሉ፡ (ጣቢያዎቹ እንደ ጠረም ፤ ማልራምና ቢቁርሮፌ) የሚባሉ የመሳሰሉ ናቸው፡፡ እነዚህ የጤና ጣቢዎች በተለይ የተለመዱት የጤና ጣቢያዎች በማይሰሩበት ጊዜ ነው የሚሰሩት፡፡ በለሊት ፤ በሰንበትና (ሻባት) በባኣላት በመሳሰሉት ፡፡ በየጤና ጣቢያዎቹ የስልክ ማዕከላትና ኢንተርነት ከጤና ጣቢያዎቹ በመስማማት የሚሰሩት የአስቸኳይ ጊዜ የጤና ጣቢያዎች የስራ ጊዜያቸው በተመለከተ መረጃ ይገኛል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ጣቢያዎች አገልግሎት በክፈያ ነው፡፡ በተወሰኑ ኢጋጣሚዎች ከክፈያ ናጻ መሆን ይቻላል፡፡

ወደ አስቀድሞ ታማሚዎች መቀበያ ክፍል (ኢሜርጀንሲ ሩም) መድረስ

ሀኪም ለህክማና ወደ ሆስፒታል ከላካቸሁ ወይም እራሳቸሁ በሆስፒታል ህክምና ማደረግ አለብን የምትሉ ከሆነ ለተደረገላቸሁ ህክምና ገንዘብ እንዳትከፍሉ በሀኪሙ ትእዛዝ ብትሄዱ ይመረጣል፡፡ ወደ ሆስፒታሉ ኢሜርጀንሲ ሩም መድረስ አለባቸሁ (የምትፈልጉት ሆስፒታል መምርጥ ትችሉ አላችሁ) ፡፡ ወደ ሆስፒታሉ እራሳቸሁ ወይም በአንቡላንስ ፤ እንደአስፈልጊነቱ መድረስ ትችላላችሁ፡፡

በአጣቃላይ ግን ወደ ኤምርጀንሉ ሩም መደረስ ያስከፍላል፡፡ በሚከተለው እንደሚዘረዘረው በተለየ ሁኔታ ከመከፍል ነጻ መሆን ይቻላል፡- ወደ ሆስፒታሉ በሀኪም ከተላካቸሁ ፤ የህክምና ጣቢያቸሁ የመክፈል (እራሱ እንደሚከፈል) የሚያሳይ ሽኝ ወረቀት ካላቸሁ ፤ የህክምናው አይነት ከክፍያ ነጻ ከሆኑት ይህክምና አይነኖቶች መዝገብ የተመዘገበ ከሆነ ፤ ወይም ታካሚው ለህክምና ሆስፒታሉ ከተኛ፡፡ ታካሚው የህክምናው ክፍያ በከፊል የሚከፍልበት አጋጣሚም አለ፡፡ ያም ሆነ ይህ ከታከማችሁ በኋላ የከፈላችሁት ገንዘብ የሚመለስላችሁ ከሆነ ወደ የህክማና ጣቢያችሁ ሂዳችሁ አጣሩ፡፡

የአምቡላንስ አገልግሎት

ታማሚ አደጋ ላይ ኮሆነ እና አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልገው ከሆነ ወደ ሆስፒታል የሚወስደው የማጌን ዳቪድ አዶም አምቡላንስ መጥራት ይቻላል-24 ስዓታት ሙሉ የሚሰራው አምቡላንስ፡፡ የጤና ጣቢያ አባላት የሆኑና በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል ለህክምና ተወሰደው የተኙ ሰዎች ለአምቡላንስ የሚከፍሉት ክፍያ በሙሉ ይመለስላቸዋል፡፡ በአምቡላንስ ሆስፒታል ተወስደው ለህክምና በሆስፒታሉ ያልተኙ አባላት በተለመደው አምቡላንስ ከሆነ የተወሰዱት የአንቡላንሱ ክፍያ መክፈል አለባቸው (ልዩ ከሆነ ሁኔታ ውጪ)፡፡ በ-የአስቸኳይ

ህክምና አምቡላንስ ወይም በ-የአስቸኳይ ህክምና አምቡላንስ ተወስዶ ከሆነ ለመጓጓጉው የከፈለው ክፍያ በከፊሉ ይመለስለታል፡፡ ክፍያው እንዲመለስላችሁ (የሚመለስላችሁ ከሆነ ለመጠየቅ) በአምቡላንሱ ከተወሳዳችሁበት ቀን በ 60 ቀናት ውስጥ ተመላሹ ክፍያ እንዲመለስላችሁ ጠይቁ፡፡ ወደ ሆስፒታል የተወሰደች አራስ ፤ በጠላት የተጎዱ ፤ በስራ አደጋ የተጎዱ ክፍያው በቢጡዋኽ ልኡሚ (በየብሄራዊው ዋስትና ተቋም) ነው፡፡

ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው የማጌን ዳቪድ ድርጂት የኢንተርነት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡ www.madis.org

ከማጌን ዳቪድ በተጨማሪ “ኢኹድ ሀጻላ“ በሚባለው ድርጂትም መጠቀም ይቻላል፡፡ “የኢኹድ ሀጻላ“ ቡድን ወደ ተጠራበት ቦታ በአስቸኳይ በመድረስ የማጌን ዳቪድ የህክምና ቡድን እስከሚደርስ የመጀመሪያ ህክምና አርዳታ ያደርጋል፡፡

እንዲሁም ኤዝራ የሚባል ድርጂት አምቡላንሶች ህክምና የሚስፈልጋቸው ያለ ክፈያ ወይም በትንሽ ክፈያ ታማሚዎች ወደ ሆስፒታል ያጓጉዛል፡፡ ጋይድ ስታር ወደ እሚባለው የሚከተለው የድርጂቱ ኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ፡- www.guidestar.org.il

አስተውሉ !

ወደ ኢሚርጀንሱ ሩም ከመሄዳችሁ በፊት ከሆነም ይሁን ክፍያ ነጻ እንድትሆኑ ከህክምና ጣቢያችሁ የመላክ (ሽኝ) ደብዳቤ መያዝ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በተለያዩ ቋንቋዎች የሚሰራ(የሚመልስ) የስልክ ማዕከል

የጤና ጥበቃ ቢሮ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚሰሩ ሁለት የስልክ ማዕከላት አሉት፡፡

ቆል ሀብሪኡት (የጤና ድምጽ) - የስልክ ማዕከል አገልግሎት

ማዕከሉ የተቋቋመው በጤና ጥበቃ ሚኒስተር ሀላፊነት ስር የሆኑትን ሁሉ ጉዳዮች ለሰፊው ህዝብ መረጃ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

ከጉዳዮቹ አንድ አንዱ የህክምና ፍቃድ መስጠት ፤ ከበሽታ ለመዳንና ለእንቅስቃሴ የሚረዱ የህክምና መሳሪዎች ፤ የጤና መንግስታዊ ዋስትና እና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት፡፡አገልግሎቶቹ በአረብኛ፤ በዕብራስጥ ፤ በእንግሊዘኛ ፤ በአማርኛ ፤ ፈረንሳይኛ እና ሩሲያኛ ይሰጣሉ፡፡

የማዕከሉ ስልክ ቁጥር፡- *5400 ወይም 08-6241010 ናቸው፡፡

ወደ ማዕከሉ የስራ ስዓታት እና ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/General/health_call_center

እንዲሁም ወደ ማዕከሉ በፋክስ ቁጥር: 02-5655969 እና በሚከተለው የኢሜል እድራሻ መጠየቅ ይቻላል፡፡ Call.Habriut@moh.health.gov.il ወይም የአን-ላይን ፎርም በመሞላት በሚከተለው አድራሻ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/General/health_call_center

በህክምና የትርጉም ማዕከል-ህክምና በቋንቋህ

በማዕከሉ ባስፈለገ ጊዜ ሁሉ የመተርጎም ግልጋሎት አለ፡፡ ታካሚውና አካሚው በሚገናኙበት ወቅት የህክምና ቡድኑ አባላት ወደ የትርጉሙ ማዕከል ስልክ መደወል ይችላሉ፡፡ ከደወሉ በኋላ ወድያውኑ የህኪሙ አባባል ለታካሚው የታካሚው አባባል ለህኪሙ በማዕከሉ ተረጓሚዎችይተረጎማል፡፡ አገልግሎቱ በሩሲያኛ ፤ ፈረንሳይኛ ፤ አማርኛ ፤ ትግርኛና አረብኛ ነው፡፡ የማዕከሉ ስልክ ቁጥር፡- *5144 ወደ ማዕከሉ የስራ ስኣታት እና ወደ ተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/service/medical-interpretation-center

የጤና አገልግሎት በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ “የጤና አገልግሎት“ የሚለው የጤና ጥበቃ መረጃና ገለጻ መጽሄት አንብቡ፡፡ የማዘዝ ፎርም በዚህ መጽሄት መጨረሻ ላይ አለላችሁ፡፡

ለምርምር ተማሪዎች ስኮላርሺፕ

ሳይንቲስቶች ስራ የማስያዙ ማዕከል የእርዳታው መብት ላላቸው የምርምር ተማሪዎች (ዶክቶራል ስቱዴንት) እና የፖስት ዶክቶራል ምርምር ተማሪዎች ይረዳል::

ስኮላርሺፑ ለምርምር ተማሪዎች ወይም በእስራኤል ታዋቂነት ካላቸው ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለምርምር ትምህርት የገቡ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች ነው የሚሰጠው:: ስኮላርሺፑ ለመቀበል ተቀባዩ የመቀበሉ መብት እንዲኖሮው ያስፈልጋል:: ክፍ ብለው የተጠቀሱት እርዳታዎች ዕድሚያቸው ከ37 ዓመት በላይ ላልሆነ ነው::

ሙሉ መብት ካላችሁ ለማወቅ በምትኖሩበት አካባቢ ከሚገኘው የአዲስ ገቢዎች አማካሪ ተነጋገሩ-ጠይቁ ወይም ወደ እሚከተለው የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የኢንተርነት ድረ በገጽ ግቡ:-
https://www.gov.il/he/Departments/General/research_students_scholarship

የጤና አገልግሎት

መንግስታዊ የጤና ዋስትና ህግ

በጤና መንግስታዊ የዋስትና ህግ መሰረት የእስራኤል ኑዋሪ የሆነ ሁሉ የጤና ዋስትና አለው። ስለሆነም የጤና አገልግሎት የመቀበል መብቱ የተጠበቀ ነው:: እነዚህ አገልግሎቶች በሀገሪቱ ሀላፍነት ስር ሲሆኑ በጀታቸው ከህዝብ ነው:: በጤናው ዋስትና (ኢንሹራንስ) አገልግሎት ያካተተው የጽሁፍ ዝርዝር በህጉ አባባል "ሳል ብሪኡት" በመባል ይታወቃል:: የጤናው አገልግሎት የሚሰጡት የጤና ጣብያዎች ስልሆኑ የጤና አግልግሎት ለመቀበል ዜጋ ሁሉ ከጣቢያዎቹ በአንዱ በአባልነት የመመዝገብ ግዴታ አለው:: እንዲሁም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ዜጋ ሁሉ የጤና ጥበቃው ዋስትና እንዲኖሮው በየወሩ የጤና ጥበቃ ዋስትና ክፍያ ለቢጥዋኽ ልኡሚ (የብሄራዊ ዋስትና ተቋሙ) መክፈል አለበት (ለቢጡዋኽ ልኡሚ የዋስትና ክፍያ ከሚከፈለው በተጨማሪ)::

የዋስትና ክፍያ በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን "የቢጡዋኽ ልኡሚ" አንቀጽ ተመልከቱ-አንብቡ::

አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከገቡ ለ12 ወራት ያህል ከጤና ዋስትና ክፍያ መክፈል ነጻ ናቸው (ስራ የማይሰሩ ከሆነ):: **ከመክፈሉ የነጻው ጊዜ ከበቃ በኋላ የጤና ዋስትናው ጉዳይ ከቢጡዋኽ ልኡሚ ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በመነጋገር እንድትከፍሉ ማድረጉ ግዴታ ነው::** (የሚሰሩ ሰዎች የዋስትና ክፍያቸው ከደሞዛቸው ቀጥታ እየተቀነሰ ወደ ቢጡዋኽ ልኡሚ (የብሄራዊ ዋስትና ተቋሙ) ስለሚተላለፍ በግል የመክፈሉ ችግር አይኖርባቸውም)::

አስተዉሉ !

በጤና ጣቢያዎች መመዝገቡ የጤና አገልግሎት የመቀበልና ከመንግስታዊ የጤና ዋስትና ክፊያ ነጻ ለመሆን ግዴታ ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው:: የጤና አገልግሎት ባስፈለጋችሁ ጊዜ መቀበል እንድትችሉ አስራኤል እንደደረሳችሁ ወዲያውኑ በጤና ጣቢያ መመዝገቡ በጣም አስፈላጊ ነው:: አለመመዝገቡ የጤና አገልግሎት ሲሰጥ አላስፈላጊ መተጓጎልና ያልጠተበቀ የገንዘብ ክፍያ ወጭ ሊፈጥር ይችላል::

በጤና ጣቢያ መመዝገቡ እንዴት በሚል ከፍ ብሎ በተጠቀሰው "መርካዝ ቅሊጣ-የመጀመሪያ እርምጃዎች" የሚለውን አንቀጽ ተመልከቱ-አንብቡ::

አዲስ ገቢ ዜጋና ተመላሽ ታዳጊ ወጣት "ባዓሌይ ማዓማድ ኤዝራኽ ያሌ ቭቃጢን ኾዜር" በጤና ጣቢያ (ቁፓት ኾሊም) አባል ለመሆን በአሊና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ መመዝገብ ይችላሉ::

በጤና ጥበቃ አገልግሎት ለአዲስ ገቢዎች ቅናሽ ክፊያ

ወደ ስፔሻሊስት ሀኪም ፣ አውትፔሺንት ክሊኒክ ፣ ወይም ወደ ከሆስፒታሉ ውጭ የህክምና ተቋም ሲሄዱ በክፍያ የመሳተፍ ገንዘብ መክፈል ያስፈልጋል:: ይህ በክፍያ የመሳተፉ ክፍያ ለቤተሰብ የሩብ ዓመት ክፍያ አለ:: አዲስ ገቢዎች እስራኤል እንደገቡ በመጀመሪያው እንድ ዓመታቸው በዚሁ የህክምና አገልግሎት ክፍያ የ50% ቅናሽ ሊደረግላቸው ይችላል::

ለተጨማሪ መረጃ "ኮል ሀብሪኡት" ወደ እሚለው የሚከተለው የጤና ጥበቃ የኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ:-
https://call.gov.il/infocenter/index?page=content&id=GE41

አስተዉሉ !

በጤና ጥበቃ አገልግሎት ፤ መድሀኒትና የህክምና መሳሪያ ክፍያ ረገድ ለጠሮተኞች ፤ የተለያዩ ከፍያዎች ለሚከፈላቸው ፤ የሁል ጊዜ ታማሚዎች ፤ ወይም የሃይለኛ በሺታ ታማሚዎች ፤ በመኪና-መንገድ አደጋ የተጎዱ ፤ ብስራ አደጋ የተጎዱ ፤ በጠላት የተጎዱና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ቅናሽ ክፍያ ይደረግላቸዋል:: በክፊፍያው ቅናሽ ክፍያ የሚገባቸሁ ከሆነ ለማወቅ የጤና ጣቢያውን ጠይቁ ወይም "ኮል ሀብሪኡት" ወደ እሚባለው የሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ:- https://call.gov.il/

የልጆች የጤና አግልግሎት

የቤተሰብ ጤና የጤና ጣብያ (ጢፓት ኻላብ)

በሀገሪቱ ሁሉ አካባቢዎች የቤተሰብ (ጢፓት ኻላብ) የሚባሉ ጤና ጣቢያ ይገኛሉ:: በእነዚህ የቤተሰብ የጤና ጣቢያዎች ህጻናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 6 ዓመት እድሚያቸው እድገታቸውና መዳበራቸው መከታተል ይቻላል:: መከታተሉ ህጻናት የማደጋቸው ሁኔታና በጤና ጥበቃ ሚኒስተር ህግ መሰረት ክትባት መከተባቸው የመሳሰሉ ያካትታል:: ለልጆች እየ አንድ አንዱ ክትባት መከተባቸው የተጻፈበት የክትባት ማስታወሻ ይሰጣል:: የምዝገባው ማስታወሻ ደህና አድርጎ መያዙና መጠበቁ አስፈልጊ ነው::

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው የጤና ጥበቃ ሚኒስተር የኢንተርነት ድረ ገጽ መግባት ይቻላል:-
https://www.health.gov.il/Subjects/pregnancy/health_centers/Pages/family_health_centers.aspx

በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት

በመንግስታዊው የጤና ጥበቃ ዋስትና ህግ መሰረትና በጤና ጥበቃ ትእዛዝ በትምህርት ቤቶች ከ1ኛ እስከ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የጤና አገልግሎት ይሰጣል:: የትምህርት ቤቱ የጤና ቡድን ሲስተር ፤ ሃኪምና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ የህክምና ባለሞያዎች ይገኙበታል:: ተማሪ ሁሉ ወደ ትምህርትቤቱ ለመማር ሲገባና በ12 ዓመት ዕድሜው የማይ ግምት ውጤት አለው:: በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ የጀሮ ድህንነት(የመስማት) ፤ የማየት (የአይን) የጥርስ ምርመራ ይደረግለታል:: እንዲሁም ተማሪዎቹ እንደ የጤና ጥበቃ ሚኒስተር አሰራር መሰረት ክትባት ይከተባሉ::

የጤና ጣቢያዎች የህጻናት ማደግ አገልግሎት

የማደግ ችግር ወይም የጤና ችግር ያላቸው ህጻናት በጤና ጣቢያዎች የህጻን ማደግ (አተዳደጉ) አገልግሎት ይገባቸው ይሆናል (እየተመረመሩ ህክምና የመቀበል)። አገልግሎቶቹ ህክምና ባስፈለገ ቁጥርና እንደ አስፈላጊነቱ በተመጣጣኝ ጊዜና ርቀት ነው የሚሰጡት:: የመታከም ቀጠሮ ተይዞገርም የሚባለው የጥበቃ ጊዜ እስከ 3 ወር ድረስ ነው:: ከ3 ወር በላይ ለመጠበቅ የሚገደዱ የህክምና ዋስትና ያላቸው ባለ ዋስትና አባላት ወደ ግል ህክምና ሄደው የመታከም መብት አላቸው-ለግሉ ህክምና ያጡት የገንዘብ ወጪ የጤና ጣቢያቸው አንደ የጤና ጥበቃ ሚኒስተር ታሪፍ መሰረትና እንደ የህክምናው አይነት ይመለስላቸዋል::

በንግድ አማካሪዎችና የሂሳብ ባለ ሙያዎች ነው የሚሰጠው፡፡

የማዕከሉ ስልክ፡- *8115

ኢሜሉ፡- infobiz@014.net.il

ማዕከሉ ከሻባትና (ቅዳሜ) በዓላት ቀኖች ውጪ 24 ስኣታት ይስራል።

አዲስ ገቢዎች የንግድ ስራ በመስራታቸው የማበራተቻ ፕሮግራም

ከፍሉ አዲስ የስራ ድርጂት በማቋቋምና በስራ ላይ የሚገኝ የስራ ድርጂት በማጠናከር የንግድ እና ግብር ክፊያ ፤ እንዲሁም ለንግዱ ስራ በደህና ሁኔታ ብድር እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

እርዳታው በሚከተለው ረገድ ነው የሚሰጠው፡-

- ለንግዱ ስራ አስፈላጊ ነገሮች ማጣራትና ንግድን በተመለከተ ሃሳብ ማቅረብ
- የሚቆመው የስራ ንግድ (የቢዝንስ) ሞዴል ፕሮግራም ወይም ስራ ላይ የሚገኝ የንግድ ስራ ማሰፋፋት
- በእርዳታ የንግድ ስራ የማቆም ፕሮግራም በማዘጋጀት እገዛ
- የስታርት-ኣፕ የንግድ ስራ በማዘጋጀት እገዛ
- ንግድ በተመለከተ ማለማመድ፣ በስራ ላይ የሚግኝና አዲስ የሚቆም የስራ ንግድ ግብር ክፍያ በተመለከተ ማማከር
- በተለያዩ ጉዳዮች የእውቀት ማደበሪያ ግንኝነቶች (ሰሚናሮች) ማካሄድ

ስታርት-ኣፕ

ከፍሉ የሳይንስና ሀይቴክ ስታርት-ኣፕ የማቋቋም ልዩ ፕሮግራም ይገኝበታል፡፡ የእርዳታው ረገድ፡- አስፈልጊውን ነገር ለይቶ ማወቅ ፤ የፕሮግራሙ የመጀመሪያ ይዘት ፤ የቢዝንስ ሞዴል ማዘጋጀት ፤ ምቹ በሆነ አካፋፈል የሚመለስ የገንዘብ ብድር በማግኘት እገዛ ፤ በእርዳታ የሚቆም ስታርት-ኣፕ የማቆም ፕሮግራም ማዘጋጀት ፤ የንግድ ምክርና ብቅርብ እገዛ ማድረግ ፤ የስታርት-ኣፕ ዲርጂቶች የማቆምና ማስተዳደራቸው በተመለከተ ኮርስ (ስልጣና) ማድረግ እና ግብር ክፊያ በተመለከተ ማማከርና ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ ሁሉ፡፡

ስልክ ቁጥር፡- 03-6335549 / 03-5501128

ኢሜል፡- info@mati-holon.org.il

ድረ ገፅ፡- https://www.startup-israel.org.il/he/

ማኣሎት ማዕከል

የማዕከሉ እርዳታ በአዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች የንግድ ማዕከላት በኩል ነው የሚሰጠው፡፡ ማዕከላቱ በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ወጪ ነው የሚሰሩት፡፡ የስልክ ቁጥራቸው በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ድረ ገጽ እና በዚህ መጽሄት ማጨረሻ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ በንግዱ ማዕከላት የንግድ ድርጂት የማቆሙ በአዲስ ገቢዎቹ በኩል የቀረበው ሃሳብ አጥንተው ግምት የሚሰጡ ባለ ሞያዎች ይገኙበታል፡፡ አማካሪዎቹ ባለ ድርጂቱ ለማቆም ያሰቡት የንግድ ድርጂት ከእቅዱ ጀምሮ እስከ ማቆሙ ያግዙታል፡፡ የንግድ ስራው ለማቆም በመጀመሪያ ላይ የሚያሰፈልገው ገንዘብ ምን ያህል እንደሚሆን ፤ ሊኖሮው (ሊመጣ) በሚቹለው የኪሳራ አደጋ ምን ያህል ነው በሚለው ሁሉ ባለ ድርጂቱ አዲስ ገቢውን ያማክራሉ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ የአሊያውና ቅሊጣው አማካሪ በየአሊያውና ቅሊጣው ሚኒስተር ቢሮ ወይም የክፍለ ሀገራቱ የንግድ ጉዳዮች አማካሪዎችን መጠየቅ፡፡ እንዲሁም በማኣሎት ወይም በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር የኢንተርኔት ድረ ገጽ በኩል ማጣራት ይቻላል፡፡

ተጨማሪ መረጃ በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ድረ ገጽ ወይም በሚከተለው ልዩ ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡-
Business IL
http://www.2binisrael.org.il/

የንግድ ድርጂት በማቋቋም የኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ ሚኒስተር ቢሮ የማበረታቻ እርዳታ

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ለአዲስ ገቢዎች የሚያደርገው እርዳታ እስራኤል ከገቡ ከ15 ዓመታት በኋላ ያበቃል፡፡ ቢሆንም የስራ ንግድ በማቋቋም እርዳታው ከኢኮኖሚና ኢንዱስርትሪ ሚኒስተር ቢሮ መቀበል ይቻላል፡፡

ከኢትዮጵያ ለሚመጡት የሚሰጠው እርዳታ ቀጥሎ እንደሚዘረዘረው ነው፡-

- እራሳቸው ወይም ከወላጆቻቸው አንዱ በኢትዮጵያ ለተወለዱና በእስራኤል አገር ከ15 ዓመት በላይ ለሚገኙት በስራ ላይ የሚገኝ የንግድ ስራ ለማስፋፋት ወይም አዲስ የንግድ ስራ ለመከፈት የገንዘብ በድር፡፡

ለመጠየቅ

በስልክ ቁጥር፡- 053-5210065

በኢሜል፡- hadas@kiedf.org

- የንግድ ምክር(ማኣፍ ማዕከል)-ልዩ የንግድ የሙያ ምክር ፤ ማለማመድና የሙያ ስልጠና፣ የንግድ ስራ ድርጂት የማቋቋም ፕሮግራም ማውጣት እና ለድርጂቱ ማቋቋም ወደ የሚሆን የገንዘብ ምንጭ መላክ ፤ የገንዘቡ ጥያቄ የማቅረብ ጽሁፍ በማዘገጀት እገዛ፡፡

በሳይንስ ስራ ማስያዝ (መስጠት) ማዕከል

ሳይንትስቶች ለስራ መቀበል

በምርምርና ፈጣራ ስራ የሚሰሩና የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ቅድመ ሁኔታ የሚመልሱ (የሚያማሉ) ሳይንቲስቶች ወይም ማህንዲሶች የሆኑ አዲስ ገቢዎችና ተመለሽ ዜጎች በሳይንስ ስራ ማስያዝ ማዕከሉ ሊረዳ ይችላል፡፡

ማዕከሉ ቀጥሎ በሚዘረዘረው መስክ ለሳንትስቶች አገልጎሎት ይሰጣል፡-

- ቴክኖሎጂና ኤክዛክት ሳየንስ መስክ
- በማህበራዊ ሳይንስ መስክ
- የኑሮና ህክምና ሳይንስ መስክ

እስራኤል ከመምጣት በፊትና ከደረሱ በኋላም በሳይንስ ስራ ማስያዙ ማዕከል ከማዕከሉ ሰራተኞች የመማከር አገልግሎት መቀበል ይቻላል፡፡

ማዕከሉ አዲስ ገቢዎችና ተመለሽ ዜጎች በሳይንስ ስራ እንዲያገኙ ፤ በምርምርና በፈጠራ ስራዎች በአካዳሚክ የፈጠራ ስራ ፤ በንግድ ስራዎች መስክም እንዲሰማሩ ይረዳል፡፡ እንዲሁም ማዕከሉ በሚከፈላቸው ደሞዝ በከፊል ይሳተፋል-ይረዳል፡፡ ሳይንቲስት ስራ ይዞ በሚከፈለው ደሞዝ በከፊሉ መሳተፉ በሚለው ለተጨማሪ መረጃ አድራሻው በሚከተለው ወደ ተጻፈው የሳየንስ ስራ ማስያዝ ማዕከል የኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ፡፡
https://www.gov.il/he/departments/topics/absorption_in_science/govil-landing-page

ወይም በሳይንሱ ሳይንቲስቶች ስራ የማስያዙ ማዕከል ኢንተርነት በሚገኘው መጽሄት ድረ ገጽ ገብታችሁ ተመልከቱ-አንብቡ፡
https://www.gov.il/he/departments/publications/reports/integration_in_science_bulletin

በሳይንስ መሰማራት ማዕከል ጋር ግንኙነት የመፍጠር ዘዴዎች፡-

ስልክ ቁጥር፡- 073-3972513

ኢሜል፡- scientist@moia.gov.il

“ስራ ለሚቾት“- ስራ ለሚቾች የሚባለው ፕሮግራም በ-የመከታተል እዝ ለቤተሰቦች የሚደረግ የኢኮኖሚና ስራ ፕሮግራም ነው:: እንደተባላው ፕሮግራሙ ለቤተሰብ ሲሆን ቤተሰቦቹ እየተከታተልከ ጥራት ባላቸው የስራ ቦታዎች እንዲሰማሩ ማድረግና የኢኮኖሚ ሁኔታቸው በማሻሻል እንዲመሩ ማስቻል ነው:: ፕሮግራሙ በአንድ በኩል ሁሉም ያካተተ የእዝ እጅ ማግባት በሌላው በኩል ከቤተሰቦቹ ልዩ ፍላጎቶች የሚስማማ ማድረግ ነው:: ለተጨማሪ መረጃና በ ፕሮግራሙ ተሳታፊ ለመሆን በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘው የማህበራዊ አገልግሎት ክፍል ወይም “ብአጽሚ“ ወደ እሚባለው ድርጂት በስልክ፡- *2119 መደወል ወይም በሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ፡- gitit.sag@be-atzmi.org.il

ከኢትዮጵያ ለመጡት ብቻ ፕሮግራሞች

የስራ ሚኒስተር ቢሮ ከኢትዮጵያ ለመጡት በሙያዊ ስራ መሰኮች እንዲሰማሩ የሚያደረጉ ፕሮግራሞች አሉት:: ፕሮግራሞቹ ከኢትዮጵያ የመጡት የስራው ባህሬ መለየትና ማወቅ እንዲችሉ እርዳታቸውን ይለግሳሉ:: ፕሮግራሙ አስፈላጊነቱን እየለየ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ፣ መሆንዲስትና የሙያ ስልጠና በመላክ አስፈልጊውን እገዛና የማመቻቾት ክትትል ያደርጋል::

ፕሮግራሞች

“ለርቀት“- እንደሚባለው የጆይንት ድርጂት የሚሳተፍበት ፕሮግራም ከኢትዮጵያ ለመጡት ወደ ስራየሚመራ የግል ምክር አገልግሎት ፣ የሙያ ስልጠና ፣ በሰዎች የሚኖሮው የሙያ እውቀት ለማግኘት ስልጠና የመሳሰሉትን እና ወ.ዘ.ተ::

“ዶሊም ብያኽድ“-ዶሊም ብያኽድ የሚባለው ፕሮግራም ከኢትዮጵያ የመጡት የአካዳሚክ ትምህርት የተማሩና በትምህርታቾው በጣም ጎበዝ የሆኑ ለነሱ ብቁ በሆነ ተገቢ ስራ እንዲሰሩ የሚያድረግ ፕሮግራም ነው::

“ቴክ ቃሬራ“-የሀይቴክ ትምህርት የሚማሩትን በ-የሙያው ስልጠና ትምህርታቾው መርዳት::

ስለፕሮግራሙ ተጨማሪ መረጃ ወደ በስራ ሚኒስተር ቢሮ የሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ ሊንክ ግቡ፡- https://www.gov.il/he/Departments/Guides/special-populations-employment

የሰራተኞች መብት

በእስራኤል በሰራተኛና አሰሪ መካከል ስርኣት እንዲኖር የሚያደርግና የሁለቱን ወገኖች ግዴታና መብት ምን መሆን እንዳለበት የሚወስን ህግ አለ (የስራ ህግ ይባላል):: ትልቁ የስራ ህጉ አላማ የሰራተኛው ሁኔታ ከስራ ሰጪው ጋር ሲነጻጸር ሁል ጊዜ የተዳከመ ስለሆነ መብቱን እንዲጠበቅ ማድረግ ነው:: የሰራተኞች መብቶች መጠበቅ የተለያዩ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ያሉባቾው ተከላካይ ህጎችን በመደንገግ ነው:: ድንጋጌዎቹ በስራው ስምምነት ሰነድ ላይ የሚገኙ ሲሆን ሰራተኛ ሁሉ በስራ ህጉ መሰረት የሚገባው መብት ሁሉ እንዲቀበል የሚያደርጉ ናቾው::

እነዚህ የመከላከል ድንጋጌዎች እንደ አንስተኛ ደሞዝ ፤ ከስራ የእረፍት ጊዜ ፤ ዓመታዊ እረፍት ፤ የሴቶች ስራ ፤ ሰራተኛ ከስራ ሲባረር ካሳና ጠሮታ የሚለው ሁሉ ያካተቱ ናቾው::

ሁሉም ያጠቃለለ መረጃ የሰራተኞች መብት በሚለውየስራ ሚኒስተር ቢሮ ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል:- https://www.gov.il/he/departments/topics/workers-rights/govil-landing-page

የስራ ህግ ማክበርና የስራ ስርኣት የሚባለው ክፍል ስራ የሚመለከትጉዳይ ሁሉ በስርኣት የህግ አክባበርና የስራ ህግ መተግበር- በስራ መስክ ሁሉ ስርኣት እንዲኖር ፣ የስራ ህግ እንዲተገበር ፣ የሰራተኞች መብት ሁሉ በሚገባ እንዲከበር ፣ የሰራተኛ መብት መጣስ እና ደሞዛቾው ዝቅተኛ በሆነ ደሞዝተኞች ሰራተኞች ላይ የሚደረሰው ጉዳት አንስተኛ እንዲሆን ማድረግ::

አካሉ የገንዘብና ሌላ የመሳሰለ ቅጣት የመቅጣት ስልጣን አለው::

የአስተዳደሩ ድረ ገጽ፡-
https://www.gov.il/he/departments/units/regularization-and-enforcement

ክስ አቀራረብ

- ስልክ፡- *2570
- በሁሉምስኢታትመልእክትመስቀመጫ (በሌላቋንቋዎችምጭምር) ስልክቁጥር፡- 1-800-354-354
- ኢሜል፡- report.achifa@labor.gov.il
- ፋክስ፡- 03-6828690
- ፎርም በኦን-ላይን፡- https://govforms.gov.il/mw/forms/WorkRightsViolationComplaints@labor.gov.il

ጎን ለጎን ወደ የስራ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይቻላል።

ልዩነት

በስራ ዕድል እኩልነት ህግ መሰረት ሀጉ አሰሪዎች በዘርነት ወይም ሌላ ምክንያት (ሰራተኛ ወደ ስራ በመቀበል ሰራተኛ የሚገባውን መብት) በመሳሰሉት አሰሪው በህግ መሰረት በሰራተኞቹ መካከል ልዩነት ማድረጉ በህግ የተከለከለ ነው:: **የስራ እኩልነት ኮሚቴው** ለሰራተኞችና አሰሪዎች ህግን በተመለከተ በነጻ ምክር ይሰጣል::

ኮሚቴው ለማግኘት ስልክ ቁጥር፡- 074-7696562 ወይም 074-7502429

ኢሜል፡- shivion@economy.gov.il

የኢንተርነት ድረ ገጽ፡-
https://www.gov.il/he/departments/Units/equal-opportunities-at-work-unit

ብህዝባዊ አገልግሎት ተገቢ ውክልና

በህግ መሰረት ከኢትዮጵ እስራኤል ለገቡት በመንግስታዊው እና በህዝባዊው አገልግሎቶች ተገቢ ውክልና ይገባቾዋል::

በመንግስታዊ አገልግሎቶች ለኢትዮጵያ ቤተ እስራኤል የተባሉት ስራዎች ወደ ሀገሪቱ አገልግሎት የኢንተርነት ድረ ገጽ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/General/tenders_ethiopian_community

የስራ እቅድ

የስራ ፕሮግራም የማውጣት ማበረታቻ የአሊያና ቅሊጣ ቢሮ እርዳታ

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር የስራ ፕሮግራም የማውጣት ክፍል በእስራኤል የስራ ድርጂት በመክፈት በስራው አለም መሰማራት የሚፈልጉ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች የስራ ፕሮግራም የማውጣት የማበረታቻ ፕሮግራም አለው:: ይህ በተመለከተ ገና እስራኤል ሳይመጡ (አሊያ ከማድርግ በፊት) በውጪ አገረም እርዳታውን መቀበል ይቻላል::

የስራ ድርጂት መረጃ ማዕከል

ክፍሉ የስራ ድርጂት ማዕከል አለው:: ማዕከሉ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። አዲስ የስራ ድርጂት ሲቋቋም ማዋጣቱ በሚል ፣ ኢኮኖሚ በተመለከተ መረጃ መስጠት ፣ የግብር ክፍያ ባለ ስልጣን ከገንዘብ ምንጭ ብድር መበደር ፣ የንግድ ስራ በሚል ሰሚናሮችና ስብሰባዎች በሚል ሁሉ መረጃ መስጠት:: መረጃው

ስራ ፍለጋ

ተስማሚ ስራ ለማግኘት ፣ የስራው ፕሮግራም ለማውጣት የቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ የቅሊጣ አማካሪዎች ይረድዋችኋል፡፡

ስራ የማግኘት መንገድ፡-

- ስራ የት እንደሚገኝ የማመላከት የአሊና ቅሊጣ ሚኒስተር ማዕከል
- በሚዲያ፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃንና በኢንተርነቱ ተፈላጊ በሚለው ድረገጽ
- ተፈላጊ በሚለው የጋዜጦች ገጽ
- ሰው በሰው
- በግል የስራ ድርጂቶች
- በሰው ሀይል ድሪጂቶችና ስራ ሰጭ ድርጂት
- በስራ ሰጭ ቢሮ

ስራ የመፈለግ ስልጠና

ከቅሊጣ አማካሪ እየተገናኙ በሙያቸው ስራ ያላገኙ አዲስ ገቢዎች ወይም በእስራኤል ተፈላጊ የሆነ ሙያ የሌላቸው አዲስ ገቢዎች በስራ ፍለጋ ስልጠና ሊሰለጥኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ስልጠናዎች የአካዳሚክ ትምህርት ወይም ሌላ የሙያ ትምህርት ላላቸው አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች ስራ እንዲያገኙ የሚረዱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች እራሳቸው ችለው ስራ ፈልገው እንዲያገኙ የእራስ በእራስ መተማመን እንዲኖር የሚያደርጉና ከሙያዊ ስልጠናቸው ጋር የሚሄድ ስራ ለማግኘት ዕድሉ ከፍ እንዲል የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ስራ እንዲያገኝ ማድረግ (ለደሞዝ የሚሆነው ከፍያ መክፈል

አዲስ ገቢ ስራ ከያዘ በኋላ ድርጊቱ በስራው ቦታ መሰማራቱ የሚረዳ ከሆነ የአሊያና የቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ከደሞዙ የተወሰነ ከፊያ ለስራ ሰጪው ሊከፍል ይችላል፡፡ እርዳታው የሚሰጠው ስራ ሰጪው ከጠየቀና አዲስ ገቢው ፈቃደኛ ከሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ስራ ሰጪው አዲስ ገቢው የእርዳታው ጊዜከአበቃ በኋላም በስራው ቦታማስራቱ እንደሚቀጥል ቃል ከገባ በኋላ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃና መብቱ በተመለከተ በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘውን የቅሊጣ አማካሪ ጠይቁ፡፡

ለሳይንቲስቶች፣ ለአርቲስቶችና አስፖርተኞች እርዳታ

ለሳይንቲስቶች እርዳታ

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ቅድመ ሁኔታ የመለሰ ሳይንቲስት በስራ በመሰማራት እርዳታ ሊደረግለት ይችላል ወይም ለምርምር ትምህርት ስኮላርሺፕ፡፡ በሚከተለው ሳየነስ ማስተናገድ በሚለው የማዕከሉ ክፍል እዩ፡፡

ለአርቲስቶች እርዳታ

አዲስ ገቢና ተመላሽ ዜጎች አርቲስትነታቸው በስራ ከፍሉ የሙያ ጉዳዮች ኮሚቴ እውቅና ያገኙ አይነቱ በርካታ የሆነ እርዳታ በአሊያውና ቅሊጣው ሚኒስተር ቢሮ ይደረግላቸዋል፡፡

እርዳታው ለመቀበል የአካባቢያችሁ የስራ አማካሪ ወይም በሰፈራችሁ የሚገኝ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ጠይቁ፡፡ ሞልቶ ወደ ኮሚቴው የሚላክ ፎርም እንዲሰጣችሁ ጠይቃቸሁ ሞልታችሁ ወደ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች የሙያ ኮሚቴ ላኩ፡፡ ከጥያቄው ፎርም አያይዞ የሚላኩ የሚከተሉት ሰነዶች ኮፒ ተደርገው፡

በውጭ አገር የመስራታችሁ ምስክር ወረቀት ፤ አጠር ያለ በእብረይስጥ ወይም በእንግሊዘኛ የተጻፈ የሂወት ታሪክ ፤ አርቲስትነት በሙያችሁ የመማራችሁ ምስክር ወረቀትና የድጋፍ ወረቀትና ወ.ዘ.ተ፡፡. አማካሪው የሰጣችሁት የጥያቄ ሰነዶች ሁሉ ወደ የሞያው ኮሚቴ ሰብሳቢ ያስረክባል፡፡ እንዲሁም በሙችሁ ኮሚቴው ፊት እንድትቀርቡ ሰብሳቢው ይጠራችኋል፡፡

ኮሚቴዎቹ የሚሰሩት በሚከተሉት መስኮች ነው፡- ተያአትርና ተለቪዢን ፤ ዳንስና ኮሪያግራፊ ፤ ተያአትርና ደረጃ ፤ ሙዚቃና ፊጠራ ፤አርቲስትነትና ደራሲነት፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘውን የቅሊጣ አማካሪ ጠይቁ ወይም በሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ አጣሩ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/Guides/recognition-as-an-artist?chapterIndex=1

ለስፖርተኞችና የስፖርት ባለ ሙያ አስተማሪዎች እርዳታ

ስፖርተኞች መሆናቸው በባህልና ስፖርት ሚኒስተር ህፊት ቤት የጉዳዩ ሃላፊ እውቀና ያገኙ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች ወይም የስፖርት ትምህርት ባለ ሙያ የሆኑ የስፖርት መሳርያ መግዣ ወይም የስፖርት ልብስ እንዲሁም በስራ ጂመራ ላይ የአንድ ጊዜ የገንዘብ እርዳታ (ስጦታ) ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ የአካባቢያችሁ የቅሊጣ አማካሪ ጠይቁ፡፡ እንዲሁም በሚከተለው ድረ ገጽ ተመልከቱ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/Guides/recognised-athletes

በስራ ሚኒስተር ቢሮ በኩል በስራ ላይ የማሰማራት ፕሮግራም

የስልጠና እና ሙያ የመለወጥ ኮርሶች

ከኢትዮጵያ የመጣ ወይም ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያ የተወለዱ በስልጠና ኮርሶች ወይም በተለያዩ ቢሮዎች ሙያ የመለወጥ ስልጠና (በቁፖን) ክፍያ እርዳታ ሊደረግለት ይቻላል፡፡ ቁፖኖቹ በስራ ሚኒስተር ቢሮ በኩል ነው የሚሰጡት፡፡ ለማጣራት በሚከተለው የስልክ ቁጥር ጠይቁ፡- 1599-500-818

ለተጨማሪ መረጃ፡ ወደ የሚከተለው ሊንክ ገቡ፡- https://www.labor-shovarim.co.il

ቁፖኑ ለመቀበልየስራ ማሰማራቱ ማዕከል ጠይቁ፡፡ የስራ ማሰማራቱ ማዕከል የጽሁፍ ዝርዝር በሚከተለው ድረ ገጽ፡- https://www.labor-shovarim.co.il/?CategoryID=239

መብት ላላቸው ሁሉ በስራ የመሰማራት ፕሮግራም

የስራ ሚኒስተር ቢሮ መብቱ ላላቸው ሁሉ በስራ የማሰማራት ፕሮግራም አለው፡-

“የዕድል ማዕከል“- የከተማ የስራ አካባቢ ማዕከላት ፤ የከተማው ለስራ ፈላጊ የተባለ የስራ ሁሉ ፕሮግራሞች አጠቃልሎ የያዘ ነው፡፡ በማዕከላቱ የስራ ጉዳይና አገልግሎት ያለው ባለ ሙያ ቡድን ይገኝበታል፡፡ አግልግሎቱ ከመጀመሪያው የጥያቄው ጊዜ ጀምሮ ይስጣል፡፡ በስራ በሚገባ መሰማራት የሚያስችል አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ሰዎች ስራ እስኪያገኙ ድረስ ይከታተላል፡፡ ለተጨማሪ መረጃና ወደ ፕሮግራሙ ለመጨመር ቀጥታ ማዕከሉን መጠየቅ ይቻላል ወይም የአካባቢያችሁ ማህበራዊ አገልግሎቶች ክፍል መጠየቅ ::

“ኤሼት ኻይል“ - ሴቶች ስራ ላይ የማሰማራት ፕሮግራም፡፡ ፕሮግራሙ፣ ወደ ስራ የመውጣት ዝግጂት፣ በስራ በመሰማራቱ ላይ ግላዊ ክትትል ፤ ስራ ደጋፊ የሆኑ ቡዱናዊ እንቅስቃሴ ፤ በስራ ድጋፍና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ናቸው፡፡ በፕሮግራሙ መሰረት ተስማሚ የሆኑ የስራ ጓደኞች ፤ ስራው በመጀመሪያው ላይ ጀምሮ የቀደም ተከተል አካሄድ ያለው ሲሆን እስከ ማረጋገጡ ድረስ ፤ ከተጨማሪ አካላት ጋር መሳተፍ ያለበትና ሰራተኛዋ በቸሎታዋ መሰረትና በምትመርጠው ማሰማራት፡፡ ለመገናኘት “ብአጽሚ“ ወደ እሚባለው ድርጂት በስልክ ቁጥር፡- *2119 ወይም በሚከተለው የኢንተርነት ድረ ገጽ፡-
https://beatzmi.activetrail.biz/imahot

ፈቃዱ የማውጣት ሂደት

የህክምና ሙያ ፈቃድ የማውጣት ሂደት በጤና ጥበቃ ቢሮ ነው የሚወሰነው፡፡ በእስራኤል በህክምና ሙያ የመስራት ፈቃድ የመቀበል የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ ትምህርታቸው በውጭ አገር ያጠናቀቁና ስታዥ ያላደረጉ ፣ ተምረው በሙያቸው በውጭ አገር የሰሩና በውጭ አገር እስከ 14 ዓመት በላይ በሙያቸው የሰሩ ሀኪሞች፡፡ በውጭ አገር የህክምና ትምህርታቸው ያጠናቀቁ አዲስ ገቢዎች ፈቃዱ የመቀበል ጥያቄያቸው ሸኝ ሰነዶች በመጨመር በፖስታ ወይም ወደ የጤና ጥበቃ ቢሮ የህክምና ሙያዎች ክፍል በአን-ላይን መላክ ይችላሉ፡፡

ስራው በህክምና የሆነ ፖርታል ተመዝጋቢዎቹ እንደ ፈተናዎች ፣ ፈቃድና ስታዥ የመሳሰሉ የሞያ የሆኑ ጥያቄያቸው የጤና ጥበቃ ቢሮ እንዲጠይቁ ያደርጋል፡፡ በፖርታሉ በኩል የጤና ጥበቃ ቢሮ የሚጠይቁት የላኩት መልእክት ስታቱስ ማየት ይችላሉ፡፡

የድረ ገጹ አድራሻ፡- https://my.health.gov.il/MyPortal/MedWorkers/Pages/default.aspx

ወደ ድረ ገጹ የመግባት ትእዛዛቱ በሚከተለው ሊንክ ይገኛሉ፡-
https://www.health.gov.il/Subjects/MedicalAndHealthProfessions/Documents/internship_preferences_instructions.pdf

ጥያቄያቸሁ ተቀባይነት አጊንቶ ከተፈቀደ እንደ የሰራችሁበት ጊዜ ርዝመት መሰረት የጤና ጥበቃ ቢሮ የፈቃድ ፈተና ወይም የመለማመጃ ጊዜ ማለፍ ካለባችሁ ወይም ከሌላችሁ የሚያብራራ መልስ ወደ ቤታችሁ ይልካል፡፡ ፈቃዳቸው መታየት ያለበት ሀኪሞች በዓመት ሁለት ጊዜ በሚካሄደው የዝግጂት ኮርስ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ተጨማሪ ሞያዎች-ጉዳዩ እንደሚመለከታቸው የምንግስት ዘርፎች

የፍትህ ሚኒስተር ጽህፈት ቤት (የጠበቆች ቢሮ)
- ጠበቆች

የገንዘብ ሚኒስተር
- የኢንቨስት አማካሪ፣ ኢንቨስትሻጭ፣ የኢንቨስት መዝገብ ሀላፊ
- የጠሮታ ጉዳይ አማካሪ
- የመድን ዋስትና (ሴፍኤጀንት)የሴፍኤጀንት ሀላፊ
- ፐንሺን ማርከቲንግ ኤጀንት

የትምህርት ሚኒስተር ቢሮ
- አስተማሪዎችና የመዋዕለ ህጻናት ሰራተኞች

የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስተር ቢሮ
- የእንሰሳ ሀኪሞች

የስራ ሚኒስተር ቢሮ-አስዳራት ኢሱቂም(የስራ ድርጂቶች እንደየዘርፋቸው **ስርአት ማስያዝ**)
- የመነጸር ስራ ባለሞያዎች
- የመብራት ስራ ባለሞያዎች (ኤሌክቲሪሻኖች)
- መሃንዲሶችና አርቺተክስቶች

የምቾትና ማህበራዊ ኑሮን የማረጋገጥ ቢሮ
- የማህበራዊ ጉዳይ ባለሞያ-ሶሻልዎርከሮች

የፍትህ ሚኒስተር (እንደየተለያዩ ሙያዎች ክፍሎቹ)
- ገለልተኛ መርማሪዎች
- የመሬት ሺያጭ ደላሎች (የመሬት ሺያጭ ደላሎች ምዝገባ መዝጋቢ)
- ሲፐኤ (የሂሳብ ባለሞያ) (የአካውንተሮች ኮሚቴ)

የመገናኛ ቢሮ
- የከባድ መኪና ሹፌሮች
- የህዝብ መኪና ሹፌሮች

ቱሪዝም ቢሮ
- አስጎበኞች

የባህልና ስፖርት ቢሮ
- ስፖርተኞች

የእስራኤል ገጸ ምድር ክምቺት ማዕከል
- ለኪዎች (መለካት)

አስተዉሉ !

ከፍ ብሎ የተጻፈው ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ግዴታ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሙያዎች የመረጃ ዝርዝር ጉዳዩ በሚመለከታቸው የመንግስት ቢሮዎች የኢንተርነት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡፡

እንዲሁም ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የህክምና ሙያዎች የመረጃ ዝርዝር “ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሞያዎች" በሚለው መጽሄት አንብቡ፡፡ መጽሄቱ በየአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር መረጃና ገለጻ ክፍል ማግኘት ይቻላል፡፡ የጥሪ ፎርም በዚሁ መጽሄት መጨረሽ ላይ አለላችሁ፡፡

የእስራኤል ፈቃድ ለበቀበል ማመልከቻዎቹ ጉዳዩ ወደ እሚመለከታቸው ቢሮዎች ማቅርብ፡- ሃኪሞች ወደ ጤና ጥበቃ ቢሮ፤ ጠበቆች ወደ ጠበቆች ቢሮ ፣ አስተማሪዎች ወደ ትምህርት ሚኒስተር እና ወ.ዘ.ተ፡፡

ፈቃድና መዝገባ የሚያስፈልጋቸው ሙያዎች

አርቺተክስትስ ፣ ቸሚካል ኢንጂኔርስ ፣ የህንጻ ስራ መሀንዲሶችና የኤልክትሪክስ መሀንዲሶች የእስራኤል የስራ ፈቃድ መቀበል አለባቸው የእውቅና ምዝገባ ጨምሮ፡፡ ፈቃድ ፤ማለት ለመሀንዲስ ወይም ለአርቺተክስትስ የሚሰጥ የመጀመሪያና ዋና የእውቅና እርምጃ የሚሰጠው በተመዘገበበት ቅርንጫፍ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ የስዎስት ዓመት የስራ ተሞክሮ ማድረጉን ካአሰየ በኋላ ነው፡፡ ፈቃዱ መስጠትና ምዝገባው በስራ ሚኒስተር ቢሮ ፈቃድ ለማያስፈልጋቸው ሙያዎች ስርአት የማስያዝ ድንቦች ክፍል በኩል ነው፡፡ የሙያ እውቅና ለማግኘት ቢሮው በማሀንዲሶችና አርኪቴክቶች ምዝገባ ክፍል መመዝገብ፡፡

ዛሬ በማሀንዲሶችና አርኪቴክቶች ምዝገባ የመመዝገብ ጥያቄ ገና እስራኤል ሳይደረሱ በውጪ አገር ማቅረብ ይቻላል፡፡ ስለ ፈቃድ መቀበሉና ምዝገባው ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው ሊንክ ማግኘት ይቻላል፡-
https://www.gov.il/he/departments/topics/prof-licensure-engineers-and-architects/govil-landing-page

የመገናኛ ዘዴ፡-

ኣስዳራት ኢሱቂም- (የስራ ድርጂቶች በየዘርፋቸው ስርኣት ማስያዝ)

ስልክ ቁጥር፡- 074-7696503

ፋክስ፡- 074-7993006

የማህንዲሶችና አርኪተክቶች የፍቃድ ምዝገባ ክፍል

ስልክ፡- 074-7696660

ፋክስ፡- 074-7993006

ኢሜል፡- engineer@labor.gov.il

የመለካት ስልጣን ያላቸው ሰዎች በኤልክትሪክ ረገድ መሃንዲሶችና ቴክኒሻኖች፣ መስመራቸው ከፍተኛ ቮልት ያለው መብራትና የኤልክትርክ ምህንድስና ለመመዝገብ ወደ እስራኤሉ የካርታ ስራ ክፍል ይሄዳሉ፡፡ መስመራቸው ከፍተኛ ቮልት ለሆነው ለመመዝገብ ወደ ስራው ክፍል መሄድ አለባቸው፡፡

አስተዉሉ !

ለተጨማሪ መረጃ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር አማካሪዎች መጠየቅ ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች መጠየቅ

አስተውሉ !

በዚህ መጽሄት የሚቀርበው መረጃ አጣቃላይ ነው:: እስራኤል የመቆየታችሁ ፤ የቤተሰብ ስታቱስና የመሳሰሉትን የግል መረጃዎች የእርዳታው ሙበት እንዲለወጥ ማድረግ ይችላሉ:: ስለሆነ የሆነ ነገር ከማድረጋችሁ በፊት ሙቢታችሁን በተመለከተ የቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ጠይቁ:: በዚህ ጽሁፍ በሚቀርበው መረጃን ህጉና አስተዳደሩ በሚለው ማህከል ልዩነት (አለመጣጣም) ከተገኘ አስተዳደሩና ህጉ የሚሉትን ነው የሚሺረው::

የማማከር አገልግሎትና ምን አይነት እንደሚሸል

የተወሰነ ኮርስ በመምረጥ ችግር ካለ ወደ የስራ ጉዳዮች አማካሪ ሳይኮሎጂስት የሚያገናኝ ፈቃድ ማግኘት ይቻላል:: ምክሩን ለመቀበል ከአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ፈቃድ ያስፈልጋል::

እርዳታው የመቀበሉ ሙበት ያስፈልጋል ፤ እንዲሁም እርዳታው በጀት በመኖሩ ይገደባል::

የኮምፒዩተር መሰረታዊ ስልጣና

በእስራኤል ስራ ላይ መሰማራቱ ያለው ዕድል ለማስፋት የአሊያና የቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የኮምፒዩተር የስልጠና ኮርስ ያደርጋል:: በስልጠናው የመሳተፍ ሙበት ያላቸው ከ15 ዓመት ዕድሚ በላይ ከሆኑ በኋላ እስራኤል የደረሱ ናቸው:: መብቱ የመቀበል ጊዜ እስራኤል ከደረሱ ወይም የአዲስ ገቢ መብት ካገኙ እስከ 15 ዓመት ነው:: ተመላሽ ዜጎች የተመላሽ መብት ከገኙ በኋላ እስከ ሁለት ዓመት ነው መብቱ የሚገባቸው:: መብቱን ለመጠቀም በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘውን የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ጠይቁ::

እርዳታው የመቀበሉ ሙበት ያስፈልጋል ፤ እንዲሁም እርዳታው በጀት በመኖሩ ይገደባል::

የግል የስራ ፕሮግራም

ለእናንተ አስፈላጊ ከሆነ በስራ መስክ መሰረት የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ አማካሪዎች የግል የስራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ይረድዋችኋል:: ፕሮግራሙ፡ ምን እንደሚያስፈልግ ምክር መስጠት ፤በስራ የመሰማራት የግልፕሮግራም ፤ ስራ ፍለጋ፤ ጠይቆ አስከ ስራ ማግኘቱ ድረስ መከታተል እና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ያካትታል::

ለንግድ ሥራ ባለቤቶች እርዳታ በ "የዛሙት ዒስኪት " ምዕራፍ ውስጥ ከዚህ በታች ይመልከቱ፡-

ወደ ስራ የመላክ (ስራ ማስያዝ) ማዕከል

በአዲስ ገቢዎች አዲስ ኑሮ የቅሊጣ አማካሪ የተረዱና በሞያቸው ስራ ያላገኙ በእስራኤል ተፈላጊ የሆነ ሞያ ያላቸው አዲስ ገቢዎች በስራው የማስያዝ ማዕከል እርዳታ መቀበል ይችላሉ:: በስራው የማስያዝ ማዕከል እርዳታ የመቀበል መብት ያላቸው፡-

- አዲስ ገቢና ተመላሽ ዜጎች ፣ የአከዳሚክ ትምህርት የተማሩና ባለ ሞያ ፤ በሞያቸው የማይሰሩ ወይም ሙሉ ያልሆነ ስራ የማይሰሩና ስራቸው ሙሉ እንዲሆን የሚፈልጉ::
- ደሞዛቸው አንስተኛ የሆነ አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች (ደሞዛቸው በቂ ያልሆነ) ::

እርዳታው በቢሮው አስተዳደር መሰረት የሚሰጠው በየእርዳታ መብቱ ጊዜ ውስጥ ሲሆን

(ለኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከገቡና-አዲስ ገቢ ከሆኑ) እስከ 15 ዓመት ድረስ:: በስራው ማዕከል የምክር ፣ የፈተና እና ስራ የማስያዝ አግልግሎቶች ይሰጣሉ:: ማዕከላቱ በሀገሪቱ አካባቢዎች ሁሉ የሚገኙ ሲሆኑ አገልገሎቶቹ አገልግሎቱ ለመስጠት በተመረጡት አካላት ነው የሚሰጠት::

በስራው ማዕከላት የሚሰጡት አገልግሎቶች፡-

- ኢንቴክ-የመጀመሪያ ቃለ መጠየቅ፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ የስራ ምክር ሰጪው ሳይኮሎጂስት መላክ
- ስራ መለየት-(ኢ.ቢ.ኩን ታኣስያቲ)-ወደ ስራ ወይም ወደ የሞያ ስልጠና መመራት፡
- ስራ መፈለግ

- ወደ የስራ ቃለ መጠየቅ ማዘጋጀት
- የሂወት ታሪክ በመጻፍ እርዳታ
- ስራ ማስያዝ

የስራ ፈቃድ በሚስፈልጋቸው ስራዎች የስራ ፈቃድ መቀበል

በእስራኤል ህግ መሰረት የእስራኤል ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ስራዎች አሉ:: በአብዛኛዎቹ አጋጣሚዎች ፈቃዱ ደህና አድርጎ መታየት የስፈልገዋል::

ፈቃድ የመመርመር የቅድመ ዝግጂት ኮርስ

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ በፈቃዱ የመመርመር የቅድመ ዝግጂት ኮርስ ማዘጋጀትና በሚወጣው ወጪ ይሳተፋል:: ፈቃድ የመመርመር የቅድመ ዝግጂት ኮርስ የሚከተሉት ሙያዎች ይመለከታል:- ህክምና ፤ የጥርስ ህክምና ፤ ፋርማሲ ፤የደካሞች እርዳታ ፤ የህክምና እርዳታ ባለ ሙያዎች ፤የእንሰሳ ህክምና ፤ጥብቅና (ጠበቃ) እና አካውንቲንግ (ሂሳብ የመስራት ሞያ):: በኮርሶቹ የሚሳተፉት አዲስ ገቢዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊሉ ከከፊያ ነጻ ሲሆኑ የመጓጓዣ ከፊያና በሚማሩበት ጊዜ የኑራአቸው ወጪ ደሞዝ ይከፈላቸዋል- በፖሊሲው መሰረት:: በኮርሶቹ ለመሳተፍ ከቅሊጣው አማካሪ ወይም ከስራ ጉዳይ አማካሪው ተነጋገሩ::

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንክ ገቡ:- https://www.gov.il/he/departments/general/employment_courses

አስተውሉ !

የስራ ፈቃዱ ለማውጣት ፤ ለመተርጎምና ሰነዶቹን ለማመሳከር በሚያስፈልገው ወጪ የቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ ይሳተፋል::

ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሙያዎች

በእስራኤል ለመስራት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሞያዎች የጽሁፍ ዝርዝር በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የኢንተርነት ድረ ገጽ ይገኛል- የመንግስት ቢሮዎች በቀደም ተከተል፡-
https://www.gov.il/he/Departments/faq/regulated_professions

በየአንድ አንዱ ሙያ ላይ በመጫን ፈቃድ የማውጣቱ ሂደትና የትኛው ፈቃድ በየትኛው የመንግስት ቢሮ ማውጣት እንደሚቻል የሚያሳይ መረጃና ዝርዝር ይከፈታል::

የህክምና እና የጤና ሙያዎች

ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የህክምና እና የህክምና ረዳት ሙያዎች የሚከተሉት ናቸው።

አጠቃላይ ህክምና ፣ የጥርስ ህክምና ፣ ፋርማሲ ፣ የፋርማሲ ረዳት ፣ የአይን ጤንነት ፣ ይፕኖዛ ፣ ጆኑቲክ ፣ ክሊኒካል ፣ የህክምና ራቦራቶሪ ፣ ክሊኒኤት ቲቅሾሬት ፣ ዳይት ፣ ፊዞትራፒ፣ አኩፒሺናዘረፒሪ ፣ የጥርስ ቴክኒሻን ፣ የጥርስ እንክብካቤ ፣ ደካሞችን የመንከባከብ ፣ ሳይኮሎጂ እና ወ.ዘ.ተ:: ከፍ ብሎ የተጠቀሱቱን በውጭ አገር የተማሩ አዲስ ገቢዎች ፈቃዳቸው ማየትና መመርመር ያካተተ የሙያቸው እውቅና ሂደት ግዴታ ይኖርባቸዋል:: ሙያቸው በህክምናው የሳይንስ ጉዳይ ኮሚቴው እውቅና :: ያገኙ ስፔሻሊስቶች ህኪሞች ፈቃዳቸው ከመመርመር ነጻ ናቸው።

አስተውሉ !

በውጭ አገር ህክምና ተምረው በጤና ጥበቃ እውቅና ያገኙት በእወቅናው በየጊዜው ለውጥ አለ:: ለተጨማሪ መረጃ በሚከተለው የጤና ጥበቃ ድረ ገጽ ጠይቁ-ኣጣሩ፡- https://www.gov.il/he/departments/topics/medical-professions-licensing/govil-landing-page

evaluation

በድረ ገጹ በእንሊዘኛ ፣ ሩሲያኛ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ስፓኛና አማርኛ ቋንቋዎች ተጨማሪ መረጃ ይገኛል፦
https://students.education.gov.il/towards-academic-studies/academic-degrees-evaluation-2

ዲግሪዎች ለማስገመት ጥያቄ ማቅረብ

ከውጭ አገር የመጡ አካዳማዊ ዲግሪዎች ለማስገመት ጥያቄ ማቅረብ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የትምህርት ሚኒስተር ጽህፈት ቤት ኦንላ-ይን ነው፡፡ አስፈላጊዎቹ ሰነዶች በዚሁ ድረ ገጽ ይገኛሉ፡፡

በኦን-ላይን በኩል የሚቀርቡ ሰነዶች ሁሉ ኦርጂናል (ዋናው) የሆነ ማህተም በእስራኤላዊ ጠበቃ በሁሉም የሰነዶቹ ገጾች ላይ መደረግ አለባቸው፡፡

አስተውሉ !

እስራኤል ከመግባታቸው በፊት የተማሩ አዲስ ገቢዎች በሚኖሩበት አካባቢ ወደ የሚገኘው ያአሊያና ቅላጣ ሚኒስተርቢሮ የቅሊጣ አማካሪ ዴኮሜንቶቹ ይዘው ቀርበው ያለ ጠበቃና (ያለ ክፊያ) በኦርጂናሉ ማስፈረም ይችላሉ፡፡

ለተጨማሪም የመጨረሻው መረጃ ወደ የትምህርት ሚኒስተር ጽህፈት ቤት ድረ ገጽ-የውጪ አገር ዲግሮዎች አይቶ መገመት በሚባለው ክፍል፦
https://students.education.gov.il/towards-academic-studies/academic-degrees-evaluation

መረጃዎቹ ከዲግሪው የመገመት ሰነድ ተያይዘው የሚቀርቡ ዴኮሜንቶች ዝርዝር ተጭኖ የሚገኙ ናቸው፡፡

ከዴኮሜንቱ ጋር ተያይዞ በኖቶሪ የተተረጎመ ቀይ ምልክት ያለበት ትርጉም መቅረብ አለበት፡፡ (በእንግሊዘኛ፣ አረብኛ፣ ሩሲያኛና አከራይኛ የሆኑትን ሰነዶች መተርጎም አያስፈልጋቸውም)፡፡ በኖቶሪ የተተረጎሙት ኡርጂናሎቹና ቀይ ምልክት ያለባቸው ዴኮመንቶች ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ መላክ ያስፈልጋል፦

1. ትርጉሙ የዲጂታል አገልግሎት በሚሰጥ ኖቶሪሆኖ ዴኮሜንቱ ወደ አን-ላይኑ መጨመር፡፡

   የዲጂታል አገልግሎት የሚሰጡ ኖቶሪዎች ዝርዝር በሚከተለው ድረ ገጽ፦
   https://www.gov.il/he/Departments/DynamicCollectors/search-notaries?skip=0&IsElectronicService=1

2. የተተረጎመው ዴኮመንት በአደራ መልእክት በሚከተለው አድራሻ መላክ፦

   የትምህርት ሚኒስተር ጽህፈት ቤት የውጪ አገር አካዳማዊ ዲግሪዎች ግመታ ክፍል

   ካንፊይ ንሻሪም መንገድ 22 እየሩሳሌም፡፡

   משרד החינוך, הגף להערכת תארים אקדמיים מחו"ל, רחוב כנפי נשרים 22, ירושלים

   ጉዳያቸሁ ከታየ በኋላ በኖቶሪ የተተረጎሙት ሰነዶቻቸሁ በፖስታ ይመልስሏችኋል፡፡ ዴኮመንቶቹ ለመቀበል የሚከተሉትን የግል ዝርዝራቸሁ አያይዛቸሁ ላኩ። ሙሉ ስም ፣ የማታወቂያ ወይም የፓስፖርት ቁጥር ፣ አድራሻና ስልክ ቁጥር፡፡

አስተዉሉ !

ዋናዎቹ (ኦርጂናሎቹ) ማታወቂያዎች በፖስታ አትላኩ ወይም ደግሞ በጠበቃዎች ቢሮዎች አስቀምጣቸሁ አትሂዱ፡፡

የድግሪ ገማች ክፍል ስልክ ቁጥር፦ 073-3934455 ሲሆን የሚደዉሉ ሰዎች ጥሪያቸው መቀበያ ቀኖች፦

እሁድ፣ ማክሰኞ ፣ ሀሙስ ሲሆን የመደዎያዎቹ ሰኣታት ከ8:30 እስከ 13:00 ነው፡፡

ኢሜል፦ diplomot@high.education.gov.il

የሞያ ማበረታቻ ኮርስ

ለባለ ሞያዎች የዕብራይስጥ ትምህርት ኮርስ

በስራ ቦታዎች መሰማራታችሁ ለመርዳት ሲባል የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ለተለያዩ ሞያዎች የሚመለከት የዕብራይስጥ ትምህርት ኮርስ ያደርግላችኋል፡፡ የምትፈልጉሁሉ በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘውን የአሊያና ቅልጣ ሚኒስተር ቢሮ የግል አማካሪችሁ ጠይቁ፡፡ ስትጠይቁ የኡልፓን አሌፍ ትምህርት የመጨረሳችሁ ፈቃድ ይዛችሁ ቅረቡ፡፡ ኮርሱ ከመጀመሩ በፊት የእውቀታችሁ ደረጃ ለማወቅና የምትማሩበት ክፍል ለመለየት ያህል በትምህርት ሚኒስተር ፈተና ይደረግላችኋል፡፡ ኮርሶቹ በመላ ሀገሪቱ በሚሰባሰበው የጥያቄ ብዛት መሰረት ነው የሚከፈቱት፡፡

ለባለ ሞያዎች ሁለት አይነት የዕብራይስጥ ኮርስ ነው ያሉት፦

1. **ለስራ የሚጠቅም የዕብራይስጥ ትምህርት**

   በኮርሱ የምትማሩት ዕብራይስጥ በተለይ ስራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡አዲስ ገቢዎቹ በትምህርቱ ክፍሎች እንደየሞያቸው ይከፋፈላሉ(ይመደባሉ)፡፡ ኮርሱ በሳይኮሊጂስትና የስራ ጉዳዮች ሃላፊ ክትትል ነው የሚካሄደው፡፡

   የተጠቀሱት ኩርሶች ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሞያዎች ሳይጨምር አዲስ ገቢ የሆነ ሁሉ ይመለከታሉ፡፡ ዉጤቱ ከ60 በላይ የሆነ የኡልፓን ትምህርት መጨረስ ይጠይቃል፡፡

2. **የተሻሻለ የዕብርይስጥ ትምህርትና ሞያዊ ቴርሚኖለጂ፦**

   በኮርሱ የተሻሻለ ዕብርይስጥና ሞያዊ ቴርሚኖለጂ ትምህርት ይማራሉ፡፡ አዲስ ገቢዎቹ እንደየሞያቸው በየክፍሉ እንዲሰማሩ ይደረጋል። ሀኪሞች ፤ ፋርማሲስቶች ፤ ሲስተሮች ፤የህክምና ሞያዎች ባለ ሞያ ፤ ጠበቆች ፤ የሂሳብ ባለ ሞያዎች እና ሳይኮለጂስቶች፡፡

   ከፍ ብሉ የተጠቀሱት ኮርሶች ፈቃድ ለሚያስፈልጋቸው ባለ ሞያ የሆኑ ናቸው፡፡

በቁፖን የሚደገፉ የስልጠና እና ሞያ የመቀየር ኮርሶች

የአሊና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የስራ ሞያ ስልጠና የሚፈጀውን ክፊያ ያህል ክፊያ ለአዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች (በቁፖን) ይረዳል፡፡ የምትፈልጉ ሁሉ በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘውን የቅሊጣ አማካሪ ጠይቁ፡፡ ካልሆነም በግላችሁ በአን-ላይን መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡

ጠያቂው የሚከተሉትን ሰነዶች በማቀረብ ነው የሚቀርበው፦

- ትምህርት ከሚሰጠው አካል የኮርሱ ፍጆት የሚያሳይ ፈቃድ፡፡
- የትምህርቱ ፕሮግራም፡፡
- የተቋሙ ትምህርት በመንግስት ቁጥጥር ውስጥ መሆኑ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ስር ላለሆኑ-ኮርሶች ካበቃ፡፡ በኋላ ኮርሱ የጨረሱት ተማሪዎች ስራ የማስያዛቸው ግዴታ ማቅረብ፡፡

እርዳታው የሚሰጠው እርዳታ የመቀበል መብት ላላቸው ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው ሊንኪ ገቡ፦
https://www.gov.il/he/departments/general/voucher_project

ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው የስራ ሞያዎች የመስራት ፈቃዱ እንዲታይላቸው-በሚከተለው ተመልከቱ፡፡

ግብር በመክፈል በአስተያየት ቅናሽ ክፈያ

በእስራኤል አገር ገቢ ያለው ዜጋ ሁሉ ግብር የመክፈል ግዴታ አለው፡፡ እስራኤል እንደየገቢው ፣ በቀደም ተከተል (የግብር አከፋፈል ደረጃዎች) አስራር ትጠቀማለች፡፡ ገቢው ከፍ ያለ እንደሆነ በዛ መጠን የግብር ክፈያው ከፍ ይላል፡፡

በገንዘብ ሚኒስተር ድንጋጌ መሰረት አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች ግብር በመክፈል በአስተያየት ቅናሽ የመክፈል መብት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

የአስተያየቱ ይዘት ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ናቸው፡-

የገቢው ምንጭ ዉጪ አገር የሆነ የገቢው ግብር ከመክፈለና ሪፖርት ከማቅረብ ነጻ መሆን

ለመጀመሪያ ጊዜ የእስራኤል ኑዋሪ የሆነ አዲስ ገቢና ተመላሽ ዜጋ (ከመመለሱ በፊት እስራኤል ሰይመጣ 10 ዓመት ሙሉ ውጪ አገር የቆየ) ምንጩ በውጪ አገር የሆነ ገቢና ንብረት ካላቸው እስራኤል ከገቡ አንስቶ ለ10 ያህል ግብር ከመክፈልና ለገቢዎች ባለስልጣን ሪፖርት ከማቅረብ ነጻ **መሆን ይቻላሉ።**

የመብት የግል ነጥቦች

ገቢያለው ሰው ሁሉ እንደ የግሉ ሁኔታ ሁሉ የመብት ነጥቦች ይሰጡታል፡፡ ነጥቦቹ ባለገቢው በገቢው መሰረት መክፈል የነበረበት የግብር ልክ ያስቀንሳሉ፡፡

ከ 1.1.2022 በፊት እስራኤል የገቡ አዲስ ገቢዎች

የተጠቀሱት አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከገቡ ለ3.5 ዓመት ያህል የግብር ቅናሽ ክፈያ ነጥቦች ሊገቧቸው ይችላል፡-

- እስራኤለ ከገቡ በመጀመሪያዎቹ 18 ወራት 3 ነጥቦች
- ካዛ በኋላ በሚቀጥሉት 12 ወራት 2 ነጥቦች
- ከዛ በኋላ በሚቀጥሉት 12 ወራት አንድ ነጥብ

በ1.1.2022 እስራኤል የገቡ አዲስ ገቢዎች

በሚከተለው እንደተዘረዘረው አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከደረሱ በመጀመሪያዎቹ 4.5 ዓመታት ከግብር ክፈያ ነጻ የሚያደጓቸው ነጥቦች ሊገቡዋቸው ይችላሉ፡

- በመጀመሪያዎቹ 12 ወራት ከግብር ክፈያ ነጻ የሚያደርግ አንድ ነጥብ
- ከዛ በሚቀትሉት 18 ወራት ከግብር ክፈያ ነጻ የሚያደርጉ 3 ነጥቦች
- ከዛ በኋላ በሚኖሩት 12 ወራት 2 ነጥቦች
- ከዛ ቀጥሎ በተጨማሪዎቹ 12 ወራት አንድ ነጥብ

አዲስ ገቢዎች በወታደርነት ያገለገሉበት እና በከፍተኛ ትምህርት ቤት የተማሩበት ጊዜ ከግብር ክፈያ ነጻ ከሚያደርጉ ዓመታት ተቆጥበው (ሳይቆጠሩ) ነጥቦቹ እንዳይጨመሩ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ሰራተኛ ይህ መብቱን ለማስጠበቅ ቁጥሩ 101 የሆነው ፎርም ሞልቶ የግብር ክፈያው ዓመት ሳያልቅ (ማለት ከታህሳስ ወር መጨረሻ በፊት) ለአሰሪው መሰጠት አለበት፡፡ ከፎርሙ ጋር የአዲስ ገቢዎች ፈቃድ ወይም የመብት ፈቃድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ በደሞዛቸው ወረቀት ከግብር ክፈያ ነጻ የሚያደርጉትን ነጥቦች መጻፋቸው አረጋግጡ፡፡ በተጨማሪ ስራ ቦታ የሚሰራ ሁሉ ከተጨማሪው ስራው ደሞዝ ከፍ ያለ ግብር ላለመክፈል “ቲኡምማስ" በሚል የሚታወቀው ፈቃድ (ሰነድ) ከገቢዎች ባለስልጣን አውጥቶ ለአሰሪው መሰጠት ይኖርበታል፡፡

እራሳቸውን በእራሳቸው በግል ድርጂት የሚተዳድሩ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሪፖርትሲያቀረቡ ቁጥሩ1301 የሆነው ፎርም ሞልተው የአዲስ ገቢ ፈቃዳቸው በመጨመር ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ነገሮች በተመለከተ በሚከተለው የገቢዎች ባለስልጣን የኢንተርነት ድረ ገጽ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡-
https://www.gov.il/he/Departments/General/immigrant-guide

የግብር ባለስልጣንን ለማግኘት፡-
*9848 / 074-7619848
https://www.gov.il/he/departments/israel_tax_authority/govil-landing-page

ስራ

ለሰራተኛው የሚስማማ ስራ ማግኘት አዲሱ ኑሮው ጥሩ እንዲሆን የሚያደርግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

ስራ ከመጀመር በፊት መደረግ ያለባቸው በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች፡-

- ✓ ከጊዚያዊ መኖሪያው ማዕከል (መርካዝ ቅሊጣው) የስራጉዳይ አማካሪ ጋር ሁለ ጊዜ ግንኙነት ማድረግ፡፡
- ✓ (የስራ ስአት ፣ ደሞዝ ፣ ዕርፍትና ወ.ዘ.ተ) የመሳሰሉቱን በማጣራት የሚስሟቿሁ መሆናቸው ማረጋገጥ ፣ (የስራው ቅድመ ሁኔታ ለመለወጥ ከስራ ሰጪው ጋር መነጋገር ይቻላል)፡፡
- ✓ የባለስራው ስምና እንደ (አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ ኢሜል) የመሳሰሉትን የመገናኘት ዘዴዎች ጽፎ መያዝ፡፡

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ አዲስ ገቢዎች በስራ ረገድ እንዲሰማሩ እርዳታ ያደርጋል ፣ ስራ ለመያዝ በሚያደረጉት የቀደም ተከተል ሂደት ሁሉ በመከታተል ይረዳል፡፡ ይህንኑ እርዳታ የመቀበል መብት ጊዜው እስከ 15 ዓመት ነው፡፡

ስራ የመያዝ (መጀመር) የቀደም ተከተሉ ሂደት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. የውጭ አገር አካዳማያዊ ዲግሪ አይቶ ግምቱን ማወቅ
2. በስራ ሞያ የመሰማራት ስልጣና
3. የስራ የግል ፕሮግራም
4. በእስራኤል ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው ሞያዎች የመስራት ፈቃድ መቀበል
5. ስራ መፈልግ

የውጭ አገር የአካዳሚክ ዲግሪ አይቶ መገመት

ውጭ አገር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቀበላችሁት ዲግሪ ካላችሁ ወይም የተቋማቱ ቅርንጫፍ በእስራኤል ካልዋቸውና ከነሱ ዲግሪዎች ካልዋችሁ በስራ መሰኮች ለመሰማራት ያህል ዲግሪዎቹ እንዲገመቱና እውቅና እንዲገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በህዝባዊ ዘርፎችና በሌሎች የስራ ቦታዎች የደሞዝ ደረጃለመወሰን ሲባል፡፡ ይህ ያስፈለገው የአካዳሚክ ዲግሪ የሚያስፈልጓቸው መንግስታዊ ጨረታ የሚወጣላቸው የስራ ቦታዎች ስለሚኖሩ በነሱ ለመወዳደር ያህልም ነው፡፡

የውጭ አገር አካዳማዊ ዲግሮች እያየ የሚገመተው የትምህርት ሚኒስተር የመገመት(ገማች) ክፍል ነው፡፡

የዲግሪዎቹ አገማመት(ምርመራ) በተወሰነ የህግ አሰራር ሲሆን የግመታው ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ ለየዲግሪ ግመታ ተጨማሪ መረጃ ወደ የሚከተለው የትምህርት ሚኒስተር የኢንተርነት የድረ ገጽ አድራሻ ግቡ፡-
https://students.education.gov.il/towards-academic-studies/academic-degrees-

3. አዲሱ ገቢ እስራኤል በገባበት ዋዜማ በመጠባት አገር ጊዜው ያላለቀ መንጃ ፈቃድ ከነበረው፡፡
4. አዲስ ገቢው በእስራኤል ጊዜው ያላለቀ መንጃ ፈቃድ ካለው፡፡ ከዚህ ቅድመ ሁኔታ አዲስገቢው እስራኤል ከገባ እስከ አንድ ዓመት ያህል አይፈልገውም-ነጻ ነው፡፡

አስተዉሉ !

አዲስ ገቢዎች መኪና በውጭ ገዝተው ሲያስገቡ ወይም በእስራኤል ከገዙ ከጉምሩክ ክፊያ ነጻ ከመሆናቸው በተጨማሪ ከግዢ ግብር ክፊያም ነጻ ናቸው፡፡

ከውጭ አገር እስራኤል ለማስገባት ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው እቃዎች

እስራኤል ለማስገባት ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው እቃዎች ወይም የማስገባት የሰነድ ፈቃድ ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለ ስልጣን የሚያስፈልጋቸው አሉ፡፡ የማስገባቱ ፈቃድ እቃዎቹ እስራኤል ከገቡ በኋላም ማውጣት ይቻላል፡፡ ግን እቃው ፈቃዱ ሳይሰጥ (ከመሰጠቱ በፊት) ከጉምሩክ ማስለቀቅ አይቻልም፡፡ እቃ እስራኤል ከማስገባት በፊት እቃው ከመግባቱ በፊት ፈቃድ ማስወጣቱ ግዴታ ነው፡፡

እንዲሁም የተወሰነ እቃ እስራኤል ለማስገባት ፈቃድ የሚያስፈልግ ወይም የማያስፈልግ መሆኑ የግል እቃ ማስገባት በሚለው ማጣራት ይቻላል፡፡
https://www.gov.il/he/service/customs-tax-calculation-import-by-israelis

ለማስገባታቸው ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልገው ምሳሌ የሚሆኑ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ብረት (ፈቃዱ ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስተር)
- የመገናኛ ብዙሀን እቃዎች (ፍቃዳቸው ከመገናኛ ብዙሀን ቢሮ)
- እንሰሳና የብቃያ ዘር (ፍቃዳቸው ከግብርና ሚኒስተር ቢሮ)

ወደ እስራኤል ማስገባታቸው ክልክል የሆኑ እቃዎች

እስራኤል ማስገባታቸው ጭራሽ የተከለከለ የሚባሉ ሁሉ ሳይሆን የከፊሎቹ ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፡-

- ቢላዋ (ካራ) ታጣፊና ለሞያ እንደ ለፋብሪካ ስራ ፣ በድርጂት፣ በቤት ወይም ለተፈቀደ ሌላ ላላማ ጠቃሚ ካልሆነ በስተቀር
- የለይዘር ፍጥነት እንዲበላሽ የሚደርግ መሳሪያ
- የተጭበረበረና አስመስሎ የተሰራ ኮይንስና ሰነዶች
- ገጽታው እንደ የተኩስ መሳሪያ የሚመስል የሚያነቫ (እንቫ) መሳሪያ
- የተከለከሉ የጨወታ እቃዎች
- የሚፈነዳና ቃጠሎ የሚያነሱ የሆኑ ነገሮች ፣ እቫቭ ፣ የተወሰኑ የውሻ አይነቶችና ተመሳሳይ አደገኛ የሆኑእቃዎች
- አደጋ የሚያስከትል አደገኛ ዕጽ (ኻሺሽ) ለማዘጋጀት የሚጠቅምና ወይም አጠቃቀሙ የሚያስተምር

አስተዉሉ !

እስራኤል ከመምጣታችሁ በፊት ምን አይነት እቃ ይዛችሁ መግባት እን ደሚቻልና ምን አይነት እንደማይቻል አጣሩ፡፡

የመብቱ ጊዜ

እቃዎች	የመጠቀሙ ጊዜ
የግል እቃዎች	በገቡበት ወሳኝ የሆነ ጊዜ
ልብስና ጫማ የመሳሰሉ በፖስታ የሚገቡ	በደረሱበት ቀን ወይም 30 ቀን ከዛ በፊት ወይም 3 ዓመት ከዛ በኋላ
የቤት እቃ ፤ የስራ መሳሪያ ፤ ሌላ እቃዎችና ለድርጂት የሚጠቅሙ ማሺኖች	አዲስ ገቢ ከሆኑ በኋላእስከ 3 ዓመት
ተሽከርካሪ	አዲስ ገቢ ከሆኑእስከ 3 ዓማት

የመብቱ ጊዜ ማራዘም

የመብቱ ጊዜ ማራዘም በሚከተለው ሁኔታ ይቻላል፡-

መደበኛ ወታደራዊ የግዴታ አገልግሎት-የወታደርነት አገልግሎት ጊዜ በመብቱ ጊዜ ውስጥ አይገባም፡፡ ማለት ወታደርነት አገልግሎት ከመጀመር በፊት የቀረው የመብት ጊዜ ከተለቀቁ በኋላ እንደ አዲስ ይጀምራል፡፡ የወታደርነት አገልግሎቱ ጊዜ ከተለቀቁ በኋላ ለመብቱ ጊዜ ይሰጣል ማለት ነው፡፡

እስራኤል ከመግባታቸው በኋላ በ18 ወራት ውስጥ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም መማር (የህክምና እና የፍትህ ትምህርት የሚማሩ) የጀመሩ አዲስ ገቢዎች ትምህርታቸው ያለ ማቋረጥ ከቀጠሉና ከ5 ዓመት በላይ ካላለፈየትምህርት ጊዜያቸው ማራዘም ይቻል ይሆናል-በዚህ ሁኔታ የአዲስ ገቢ መብታቸው ትምህርታቸውን ከበቁ በኋላ ከበቁበት ጀምሮ ለአንድ ዓመት ይራዘማል፡፡ ትምህርታቸውን ካበቁ በኋላ ውጭ አገር የሄዱ የመብቱ ጊዜያቸው አይጠበቅላቸውም፡፡

(ታዳጊ ልጆች ሳይጨምር) ያለ ማቋረጥ ወጭ አገር 6 ወር የቆዩ አዲስ ገቢዎችውጭ የቆዩበት ጊዜ ከመብታቸው ጊዜ ውስጥ አይቆጠርም ፤ ከተመለሱ በኋላ የመብታቸው ጊዜ ከመሄዳቸው በፊት ከነበረው ጀምሮ ይታሰብላቸዋል፡፡ የመብቱ ጊዜ በአን-ላይን በሚሞላ ፎርም ሊንክ ይራዘማል፡፡
https://www.gov.il/he/service/customs-extension-entitlement-newimmigrants

አስተውሉ !

የነጻ መብቱ አዲስ ገቢው ለእራሱ ብቻ እንዲጠቀምበት ነው የሚሰጠው፡፡ ከጉምሩክ ክፊያ ነጻ የመሆን መብት ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚጠቀመው፡፡ ኋላ ላለ መጻጸትና ለምን እንዲህ አደረግኩ ላለማለት ከጉምሩክ ክፍያ መክፈል ነጻ መሆኑ ደህና አድርጎ አስቦ መጠቀም ይመረጣል፡፡

ተጨማሪ መረጃ የማግኘትና ጥያቄ የመጠይቅ ዘዴ

ተጨማሪ መረጃና ጥያቄ የማቅረብ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ኢሜል፡- Matan_MeidaYe@taxes.gov.il
- የጉምሩክ ክፍል የኢንተርነት ድረ ገጽ፡-
  https://www.gov.il/he/departments/topics/customs_israel_tax_authority/govil-landing-page

  ብድረ ገጹ ሳይት በሚከተለው ድረ ገጽ ሊንክ የሚደረስ የአዲስ ገቢዎች መብቶች መረጃ የያዘም አለ፡፡

  https://www.gov.il/he/Departments/Guides/guide-for-immigrants-and-foreign-residents?chapterIndex=11
- ስልክ ቁጥር፡- 074-7612731

አስተዉሉ !

በዚህ መጽሄት የሚገኝ መረጃ ሁሉ አጣቃለይ መሆኑ እስታዉሱ-ሁሉም መረጃ ሙሉ በሙሉ የያዘ አለመሆኑ:: እስራኤል ከመጣችሁ ፤ በቤተሰብ ስታቱሳችሁ ለውጥ ካለ ለውጡ በመሳሰሉት የግላችሁ ለውጦች በመብታችሁ ላይ ተጽኖ ሊኖራቸው ይችላል:: ስለሆነ የሆነ ስራ ከመስራታችሁ በፊት ወደ ቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ ሂዳችሁ ለውጡ በማሳወቅ መብታችሁን አጣሩ::

በዚህ የመጽሄቱ መግለጫ ከቀረበውና በተለመደው አሰራር መካከል ልዩነት/አለመጣጣም ካለ የተለመደው አሰራር ነው የሚሸረው::

ቅናሽ ግብር መክፈል

የግል ዕቃዎች ፣ የቤት ዕቃዎች ፣ ተንቀሳቃሽ የስራ ዕቃዎች፣ ባለ ሞተር ተሸከርካሪ (በከፊሉ) እና የመሳሰሉት ከውጪ አገር እስራኤል የሚያስገቡ አዲስ ገቢዎች ከግብርና ጉምሩክ ክፊያ ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ:: እንዲሁም እስራኤል የተሰራ ማቀዝቀዣ ከገዙ ከቫተ ክፊያ ነጻ ናቸው::

የጉምሩክ ህግ በርካታ ቅድመ ሁኔታ ያካተተ በመሆኑ ምክንያት ለመረዳት አስቸጋሪ ነው:: በዚህ ጽሁፍ የሚቀርበው መረጃዋና ዋና ነገሮች ብቻ የያዘ ነው:: ተጨባጭ ዝርዝር የያዘ መረጃ ለማግኘት ወደ ግብር ባለ ስልጣን የኢንተርነት ድረ ገጽ መግባት ወይም የግብር ክፍል መጠየቅ:: መግባቱና ማግኘቱ እንዴት እንደሆነ ለመረዳት በምዕራፉ መጨረሻ ላይ መግባት::

የግብር ቅናሽ ክፊያ መብት የመወሰን ቅድመ ሁኔታና ትእዛዛት

የቅናሽ ክፍያ መብቱ የግል ከውጭ የመጣ ዕቃ፣ በአምጪው ስታቱስ ሁኔታ መለወጡ መሰረት፤ በዕድሜና እስራኤል አገር ሲገቡ የነበረው የቤተሰብ ስታቱስ ሁኔታ እና ሲገቡ በያዙት ሰነድ (ዴኮሜንት) በተጻፈው መሰረት::

የመብቱ ቅድመ ሁኔታ:-

1. ከውጭ የመጣው ዕቃ ሰነድ በባለመብቱ ስም መሆኑ::
2. የመጣው ዕቃ ከደረሰበት ወይም በጉምሩክ ከተለቀቀበት ዕለት ጀምሮ ቢያንስ ለ6 ዓመት በባለቤቱ እጅ መቆየቱ-መጠቀሙ-መኪና ከሆነ 4 ዓመት:: ዕቃዎቹ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለጊዜያዊ ሆነ ቋሚ መጠቀም ወደሌላ ሰው ማስተላለፍ የተከለከለ ነው:: ይህ የተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ መጣስ/ያለማክበር የተሰጠው የቅናሽ ክፊያ መብት ይሰርዛል/ይሸራል:: ከጉምሩክክፊያነጻሆነውያለዋስትናየተለቀቁቢሆንምለባለቤቱመጥ ቀማቸውምስክርነትያስፈልጋል::
3. የእቃው ልክ ሳይበዛ መካከለኛ::
4. ዕቃው ከጉምሩክ የሚያስለቅቀው ባለቤቱ እራሱ ወይም ህጋዊ ውክልና በተሰጠው ወኪል::

የጉምሩኩ ቅናሽ ክፊያ የሚመለከታቸው ዕቃዎች

የግል ዕቃዎች

የግል ዕቃዎች ብቻ የያዘ አዲስ ገቢ እስራኤል ሲገባ በአየር ማረፊያው አረንጓዴው መስመር ማለፍ ይችላል:: የግል የሚባሉት እቃዎች:- ልብስ ፤ ጫማና የንጽህና ዕቃዎች ፤ ዋጋቸው እስከ 200 የአመሪካ ዶላር የሆነ:- ብዛታቸው እስከ ሁለት ሌትር የሆነ የወይን መጠጥና ሌላ ብዛታቸው እስከ አንድ ሌትር የሆነ የአልኮሀል መጠጦች-የሚፈቀደው ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ለሆነ ሰው ሲሆን የታባቅ አይነት እስከ 250 ግራም::

አዲስ ገቢው ሌላ ዕቃ ወይም ብዛቱ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው በላይ የሆነ ዕቃ ከያዘየያዘው ዕቃ ከጉምሩክ ክፊያ ነጻ ቢመስለውም በቀዩ መስመር አልፎ የያዘው ዕቃ ማስመዝገብ አለበት:: ልኩ ከጉምሩክ ክፊያ ነጻ እንዲሆን ከሚፈቀድለት በላይ የሆነ ዕቃ የያዘ ከሆነ ለተጨማሪው ዕቃ ጉምሩክ መክፈል ይገደዳል::

የቤት እቃዎች

የቤት እቃዎች ማለት ለቤት ስራ የሚጠቅሙና ለኢንስተለሺን የሚጠቅሙ ነገሮች እንደ የጥገና እቃዎች ፤ የህንጻ ማነጽ ፤ ምድር ቤት ለመስራት የሚጠቅሙ የመሳሰሉትና ወ.ዘ.ተ. ስራዎች የሌላቸው:: እቃዎቹ አዲስ ገቢው እስራኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲደርስ በአውሮፕላን ወይም በመርከብ ይዞላቸው ከገባ በተጨማሪ እቃዎች በሰዎስት መልእክት መስገባት ይችላል:: አዲስ ገቢው እንደ ተጨማሪ ጭነት የሚቆጠር እስራኤል ሲገባ ማምጣት ከፈለገ ይዞት ሲገባ “በቀዩ መስመር“ በማለፍ መያዙ በማሳወቅ መድረግ ያለበት ተጨማሪ መረጃ ይሰጣዋል::

የቤተሰቡ ሁሉ 3 ተለቪዢንና 3 የግል ኮምፒውተሮች ይዞ መግበት ይችላል:: እንደ የኤለክትሪክ እቃዎችና የቤት ሌላ እቃዎች ከየአንድ አንዱ አንድ እቃ ማስገባት ይቻላል::

ከቀረጽ ነጻ መሆን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ያስፈልገዋል:: ለተጨማሪ የሙሉ መብት ቅድመ ሁኔታ በጉምሩክ ቢሮ ማጣራት ይቻላል::

በእጅ የሚያዙ የስራ እቃዎች (መሳሪያ)

አዲስ ገቢ በእጅ ይዞ የሚሰሩ (መኒዋል) የሞያ እቃዎች ይዞ መግባት ይችላል-የጉምሩክ ባለ ስልጣን እንደሚወስነው:: የዋጋቸው ግምት የገቢዎች ባለ ስልጣን ከወሰነው ከፍ ያለ ሳይሆን:: ይህ የመረጃ መጽሄት እስከ ተጻፈበት ድረስ ዋጋቸው እስከ $1.650 የሆነ::

የንግድ ዲርጂት የማቋቋም የስራ መሳሪያዎች

በእስራኤል የንግድ ዲርጂት የሚያቋቁም (የሚከፍት) አዲስ ገቢ ለኢንዱስትሪ ስራ የሚጠቅሙ ማሺኖች ፤ ለቀላል ፋብሪካ ፤ ለእርሻ ስራ ወይም በጉምሩክ ባለ ስልጣን የተፈቀዱ ሌላ አላማዎች የሚጠቅሙየስራ መሳሪያዎች ያለ ቀረጽ ማስገባት ይችላል:: (ዋጋቸው ይህ ጽሁፍ እስከ ተጻፈበት ጊዜ ደረስ እስከ $36.000 የሆነ):: ይህ የዋጋ ልክ በእጅ ይዞ (ምኒዋል) የሚሰሩ የስራ መሳሪያዎች ጨምሮ ነው:: እቃዎቹ በባለ መብቱ (እንደ ትንሽ ፋብሪካ ፤በሰፊሩ አካባቢ የሚሰራ ስራ ፤ ንግድ) የመሳሰሉ የሚጠቅሙ ሲሆን መሳሪዎቹ መቆያ ቦታቸው በፋብሪካው ውስጥ ነው:: አዲስ ገቢው በእቃዎቹ ይጣል በነበረው የጉምሩክ ክፊያ ዋጋ የሚገመት የባንክ ዋስትና መያዣ እንዲያስይዝ ይጠየቃል::

ትሸከርካሪ

በስማቸው የተጻፈ መኪና (ሞተር ሳይክልም ጨምሮ) እስራኤል የሚያስገቡ ወይም ባለ ፈቃድ ከሆኑ እምጪዎች በእስራኤል የሚገዙ አዲስ ገቢዎች ከጉምሩክ ክፊያው በከፊል ነጻ ናቸው:: የጉምሩክ ክፊያው 50% እና ቫት ጨምሮ 75% ነው::

የግብር ቅናሽ ክፊያ ቅድመ ሁኔታ:-

1. መኪናው በመገናኛና የጉዞ ጥንቃቄ ቢሮዎች ባለ ስልጣን እስራኤል እንዲገቡ ከተፈቀዱት አይነት መሆን አለበት (ተጨማሪ መረጃ በመገናኛ ቢሮ የጥራት ክፍል ማግኘት ይቻላል):: ተፈላውቱ ተሸከርካሪ እስራኤል ለማስገባት የመገናኛ ፎርም በኦን-ላይን መሙላት ያስፈልጋል::

   የመሙላቱ ድረ ገጽ ሊንክ:-
   https://www.gov.il/he/Departments/Guides/personal_import_of_vehicles

   https://www.gov.il/he/Departments/Guides/personal_import_of_vehicles_guide?chapterIndex=3
2. መኪናይቱ ባለ መብት (አዲስ ገቢው) እስራኤል ከገባ 3 ዓመት እስከ ሞላው ድረስ ብቻነው ማስገባት የሚቻለው::

እርዳታው ብምንድን-ነው የሚሰጠው	የእርዳታው አይነት	የመብቱ ጊዜ	የመብቱ ጊዜ ርዝመት	ማሳሰቢያ
ስራ	ፍቃድ በማውጣት ኮርስ በመለወጥና ስልጠና እርዳታ	እስራኤል ከደረሱ እስከ 15 ዓመትና በጀት እንደሚፈቅደው	በኮርሱ ሂደት (የአስተማሪዎች ለውጥ ሳይጨምር)	ስራ በተመለከተ ምክር ከተሰጠ በኋላ በአስተዳደሩ አሰራር መሰረት የኑሮና የማጓጓዣ ወጪ ሊጨምር ይችላል
	ስራ በማስያዝ መጣጣር	እስራኤል ከገቡ እስከ 15 ዓመት- እንደ በጀቱ ሁኔታ	እስከ 12 ወር	ለአዲስ ገቢው ስራ ወደ የሚያሰራው ይተላለፋል
	ለስፖርተኞች እርዳታ	እስከ 15 ዓመት	የአንድ ጊዜ እርዳታ	
	ለአርቲስቶች እርዳታ	እስከ 15 ዓመት	የአንድ ጊዜ እርዳታ	
ለሳይንትስት ስራ መስጠት (ማስያዝ)	ሳይንትስቱ ስራ ሰጥቶ በማሰራቱ ከፍያው መሳተፍ	15 ዓመት	እስከ 3 ዓመት	
	ለምርምር ተማሪዎች ስኮላርሺፕ	እስከ 15 ዓመት	እስከ 3 ዓመት	ዕድሜው ከ37 ዓመት ከፍ ለማይል የዴክተረት ትምህርት ተማሪ ስኮላርሺፕ
የንገድ ድርጀት የማቆም እቅድ	መመሪያ የሙያ ምክር ብድር	15 ዓመት	አንድ ጊዜ	
የአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር	የትምህርት ክፍያ	15 ዓመት	በትምህርት ጊዜ ሁሉ	እርዳታው ትምህርቱ በስተኛው እድሜ በመጀመሩና መሟላት ባለባቸው የአካዳሚክ ጥያቄዎች ይገደባል

እርዳታው ብምንድን-ነው የሚሰጠው	የእርዳታው አይነት	የመብቱ ጊዜ	የመብቱ ጊዜ ርዝመት	ማሳሰቢያ
ምኞት	የከፍለ ሀገሩ አስተዳደር ልዩ በጀት- ጊዚያዊ ትልቅ ቼግር ላላቸው አዲስ ገቢዎች የአንድ ጊዜ እርዳታ	እስራኤል ከደረሱ ለ15 ዓመት	አንድ ጊዜ	እርዳታው ለመጠየቅ የቅሊጣ አማካሪውን መጠየቅ
ብቸኛ ወታደሮች	ለብቸኛ ወታደሮችና የቤተሰብ ክፍያ ለሚገባቸው ወርሀዊ ስጦታ- ከመከላከያ ሰራዊት	አዲስ ገቢ ፤ አዲስ ገቢ ተመላሽ ዜጋና ተመላሽ ታዳጊ ልጅ-እስራኤል ከደረሱ 15 ዓመት- ተመላሽ ዜጋ አዲስ ገቢ ከመሆኑ ለሁለት ዓመት	በመከላከያ ሰራዊት በደበኛው አገልግሎት ጊዜ ሁሉ	የሚገባቸው፡ ብቸኛ ወታደር መሆናቸው እውቅና ያላቸው አዲስ ገቢ ፤ አዲስ ገቢ ዜጋ ፤ ተመላሽ ታዳጊ ልጅና ተመላሽ ዜጋ ወይም የቤተሰብ ክፍያ
	ለብቸኛ ወታደሮችና የቤተሰብ ክፍያ ለሚገባቸው -ከቅልጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ ወርሀዊ ስጦታ	አዲስ ገቢ ፤ አዲስ ገቢ ዜጋና ታዳጊ ልጅ ተመላሽ ዜጋ እስራኤል ከመድረሳቸው -እስከ 15 ዓመት ተመላሽ ዜጋ -እስራኤል ከመግባቱ እስከ ሁለት ዓመት	በመከላከያ ሰራዊት መደባኛ አገልግሎት በሚያገለግልበት ጊዜ ሁሉ	የሚገባቸው፡ ብቸኛ ወታደሮች በሆናቸው ወይም የቤተሰብ ክፍያ እንደሚገባቸው እውቅና ያላቸው

የቅሊጣና ኣሊያ ሚኒስተር ቢሮ ለየኢትዮጵያ ፤ ለየመንና ለብኔይ ምናሼ አዲስ ገቢዎች የሚያደርገው ሁሉንም ያካተተ እርዳታ ፤ ሳል ቅሊጣና የገቢ ማረጋገጫ ክፍያ ሳይጨምር አዲስ ገቢ ነው ከተመዘገቡበት ጊዜ ጀምሮ ለ15 ዓመት ያህል ነው::

እርዳታው የሚሰጥበት ጊዜ ማራዘም

የእርዳታው ጊዜ ርዝመት የተወሰነ ነው:: ጊዜው "የመብት ጊዜ ይባላል:: ቢሆንም ይህ ጊዜ ከመብቱ ጊዜ ውስጥ የማይቆጠር (የማይገባ) ጊዜ ይገኝበታል:: እሱም በ-የመብቱ ጊዜ ውስጥ በወታደርነት ማገልገል ፤ ብሄራዊ /ዜጋዊ አገልግሎት እና በውጪ አገር ያለማቋረጥ ለ6 ወራት ያህል መቆየት የመሳሰሉ ናቸው:: እንዲህ ከሆነ እነዚህ ጊዚያቶች በመብቱ ጊዜ ውስጥ አይደሉም:: ስለሆነ አገልግሎቶቹና ወጪ አገር መቆየቱ ከበቁ በኋላ የእርዳታው መብት ጊዜ እንደ አዲስ ይጀምራል:: ውጭ አገር መቆየት የመብቱ ጊዜ እንዲጠበቅ ማድረግ ሁሉ መብቶች ሊያስገኝ አይችልም-ከፊሉ ካልሆነ በስተቀር:: ይህ በተመለከተ በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ማጣራት ይቻላል::

የገንዘብ እርዳታ በተመለከተ በመላ ሀገሪቱ ከሚገኙ በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ቅርንጫፎች አማካሪዎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል:: እንዲሁም ቢሮው ከሚያወጣቸው ማስታወቂያዎች በኢንተርነት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል-በሚከተለው ድረ ገጽ:- www.klita.gov.il

አስተውሉ !

ሁሉም የስምምነቶቹ ሰነዶች ኮፒያቸው እየሰጣቸሁ ዋናው በእጃችሁ ማስቀረት አለባችሁ:: ከሰነዶቹ ዋናው በጣም አስፈላጊ ሆኖ ከተፈለገ ኮፒውን በእጃችሁ አስቀርታችሁ ስጡ-ኮፒው ማሰቀረቱ አትርሱ::

ህዝባዊ ቤት

በቤት ዕደላ ህግ መሰረት የተወሰኑ አዲስ ገቢዎች ከህዝባዊው ቤቶች ቤት መቀበል ይችላሉ::

ህዝባዊ ቤት ማለት በመንግስት ባለቤትነት የሚገኙ ቤቶች ናቸው:: ቤቶቹ የሚሰጡት ቤት ለሌላቸው (ቤት የለሽ ለሆኑ) ቤት የመቀበል መብት ላላቸው ዜጎች በቅናሽ የቤት ኪራይ ክፊያ ነው:: ቤቶቹ በቤት ዕደላ ድርጅቶች ነው የሚተዳደሩ:: አብዛኛዎቹ የሚገኙበት በሀገሪቱ ማህል ያልሆኑ አካባቢዎችና በተለይም በሰሜንና በደቡብ አካባቢ ነው:: የቤቶቹ ብዛት አንስተኛ ስለሆነ ቤት የመቀበሉ ጥበቃ ጊዜ ረዢም ሲሆን የመቀበሉ ጉዳይም የተረጋገጠ አይደለም:: ህዝባዊ ቤት ለመቀበል በተጠባባቂዎቹ መዝገብ መመዝገቡ ጠያቂው አሰራኤል የገባበት ጊዜ መቾ ነው፤ የሶሻልችግሩ ምን ያህል ነው በሚል የመሳሰሉ ሲሆን ይህ ሁሉ በምትኖሩበት አካባቢ በሚገኘው የቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ ነው የሚሆነው:: የቤቱ ኪራይ ክፍያ፤ ቤቱ እንደሚገኝበት ቦታ ፤ የቤቱ ልክና የተከራዩ ገቢ በሚል ይለያያል::

ህዝባዊ ቤት እስከ እሚገኝ ድረስ በጥበቃው ጊዜ አዲስ ገቢዎች የቤት ኪራይ እርዳታ ይደረግላቾዋል::

ህዝባዊ ቤት የመቀበል የአዲስ ገቢዎች የጥበቃ ጊዜ መብቱ እስከ 15 ዓመት ይቆያል:: ከ15 ዓመት በኋላ አዲስ ገቢዎቹ ወደ ግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ ሀላፊነት ስር ይተላለፋሉ:: የግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ እንደ የእራሱ አሰራር መሰረት ቤት የመቀበላቾው መብት ያጣራል::

የቤት እርዳታ እንዲደረግለት ጠያቂው ቤት የለለው መሆኑ (ቤት የለሽ መሆኑ) የምስክር ወረቀትና ተጨማሪ ሰነዶች ያስፈልጋሉ:: ቤት የሌለው መሆኑ ፈቃድ ከቤት እርዳታ ድርጂቶቹ አንዱ (አሚዳር፤ሚልጋም እና አሎኒም ማዕከላት ከተባሉት ድርጂቶች መቀበል::የስልክ ቁጥራቾውና አድራሻቾው ስልክ ቁጥር በሚለው አንቀጽ ይገኛል) :: ተጨማሪ የሚያስፈልጉት ሰነዶች በምትኖሮበት ላካባቢ ሁሉከቅሊጣው አማካሪ መቀበል ትችላላቾሁ::

በህጉ መሰረትና ቢሮው ካለው አማራጭ አኳያ ህዝባዊ ቤት የመቀበል መብት ካለ የአሊያውና የቅሊጣው የቤት ጉዳይ አማካሪ መጠየቅ ያስፈልጋል::

ለተጨማሪ መረጃ ወደ የሚከተለው ግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ የኢንተርነት ድረ ገጽ ይግቡ:-

https://www.gov.il/he/departments/topics/public_housing/govil-landing-page

አስተውሉ !

አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከደረሱ በኋላ ከሚኖሩባቾው የመጀመሪያዎቹ 24 ወራት ቆይታ ውስጥ ለ12 ወራት የመዘጋጃ ቤት ግብር ቅናሽ ክፊያ ይገባቾዋል:: የመዘጋጃ ቤት (አርኖና በመባል የሚታወቀው ክፊያ) ቅናሽ ክፊያ ገቢያቾው በቂ ላልሆነ፤ ለጠሮተኞች ፤ ለአካለ ስንኩል ፤ ከሹኣ (ከናዚዎች ህዝበ እስራኤል ከምድር ፊት የማጥፋት ግዲያ) ለተረፉት፤ ለወታደሮችና ወ.ዘ.ተ ይደረጋል::

በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የሚለገሰው የገንዘብ እርዳታ በምን በመን የመሆኑ መረጃ ያጠቃለለ የጽሁፍ ዝርዝር

ከኢትዮጵያ የሚመጡት አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከደረሱ አንስቶ እስከ 15 ዓመት ድረስ ከአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ በተለያዩ መስኮች እርዳታ ይገባቾዋል:: እርዳታው:- በዕብራይስጥ ትምህርት፣ በመኖሪያ ቤት ፣ በስራ ፣ በየሆነ ስራ የመስራት ፕሮግራም ማቅረብ ፣ በወታደሮችና ብሄራዊ አገልግሎት ፣ የዩኒበርሲቲ ተማሪዎች አስተዳደር፣ ከፍለ ሀገር የእርዳታ ገንዘብ ፣ በሳይንስ መሰማራት፣ ለስፖርተኞች ፣ አርቲስቶችና እና ወ.ዘ.ተ በሆኑት በመሳሰሉ ሁሉ:: ሳል ቅሊጣ በመባል የሚታወቀው እርዳታ ለአንድ ዓመት ነው የሚሰጠው:: ሳል ቅሊጣ በተመለከተ "መርካዝ ቅሊጣ"-የመጀመሪያው እርምጃዎች የሚለው ምዕራፍ ተመልከቱ::

ከ-የእርዳታው መብቶች አንድ አንዱ ቋሚ አይደሉም ፣ እንደአስፈላጊነቱ ጊዚያዊና በጀት በመኖሩ ቅድመ ሁኔታ ይገደባሉ::

እርዳታው ብምንድን-ነው የሚሰጠው	የእርዳታው አይነት	የመብቱ ጊዜ	የመብቱ ጊዜ ርዝመት	ማሳሰቢያ
እስራኤል እንደገቡ ለመጀመሪያው ኑሮ የገንዘብ አርዳታ	ሳል ቅሊጣ	እስራኤል ከገቡ እስከ አንድ ዓመት	12 ወራት	
በመርካዝ ቅሊጣው የዕብራስጥ ትምህርት (ኡልፓን)	በዕብራስጥ ትምህርቱ (ኡልፓን) መሳተፍ	በመርካዝ ቅሊጣው (ጊዚያዊ መኖሪያ ማዕከሉ) በሚኖሩበት ጊዜ	10 ወራት	
የዕብራይስጥ ትምህርት ኡልፓን ወይም በግል ተቋማት ለዕብራይጡ ትምህርት የቋፓን እርዳታ (ቫኡቾሪም)	የትምህርት ክፍያ	በየጊዜው በሚኖሮው ትእዝዛና እንደ በጀቱ ሁኔታ- እስራኤል ከደረሱ 15 ዓመት	ኡልፓን (የዕብራይስጥ ትምህርት) 5 ወር (ቫኡቾሪም) -አንድ ኮርስ	በጉዞ እና በኑሮ ወጪዎች በመብት ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት እርዳታ ሊኖር ይችላል።
የግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ በመሳተፍ መኖሪያ ቤት	በቤት ኪራይ እርዳታ ህዝባዊ መኖሪያ ቤት- ቤት በመግዛት እርዳታ	ቤት በመከራየት እርዳታ- በመርካዝ ቅሊጣው (ጊዚያዊ መኖሪያ ማዕከሉ) ከወጡና አዲስ ገቢ መከሆኑ እስከ 5 ዓመት ድረስ:: ከዛ በኋላ በመብቱ ቅድመ ሁኔታ መሰረት ቤት በመግዛትና ህዝባዊ ቤት በመከራየት እርዳታ- በመብቱ ቅድመ ሁኔታ ነሰረት	የቤት ኪራይ-5 ዓመት- 5 ዓመት ካለፈ በኋላ በመብቱ ቅድመ ሁኔታ መሰረት ቤት መግዛትና ህዝባዊ መኖሪያ ቤት-በመብቱ ቅድመ ሁኔታ መሰረት	ቤት በመግዛትና ህዝባዊ ቤት በመቀበል እርዳታው "የቤት የለሽ" ፍቃድ በመኖሩ ይገደባል ቤት በመግዛት እርዳታው- መርካዝ ቅሊጣው ለሚለቁ ብቻ ነው

2. የሚገዛ ቤት ለማግኘት ከደላላይ ጋር ማገናኘት፡፡ በሚከተለው እንደሚዘረዘረው ከደላላዩ ጋር ነገር ከመዝጋት በፊት አንድ አንድ ነገሮች ማረጋገጥ በጣም እስፈላጊ ነው፡፡

3. የሚገዛው (የሚሸጠው)ቤት ደላላዩ እንዲያገኝላችሁ ስምምነት አድርጎ ከእሱ ጋር መፈራረም፡፡ግን ጉዳዩ ከማሰር በፊት አንድ አንድ ነገሮች ማረጋገጥ በጣም እስፈላጊነው፡፡

4. ወደ ቤቱ ሁለት የጭነት መኪናዎች እንዲመጡ ማዘዝ፡፡

5. ስጦታው የመቀበል ፈቃድ ከኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ መቀበል፡፡

6. ስጦታው ለመቀበል ወደ የቤት መግዣ ብድር አበዳሪው ሂዶ መጠየቅ፡፡

የድለላ አገልግሎት

ለሺያጭም ለኪራይም በደላሎች በርካታ ቤቶች ይቀርባሉ-(ሻጩና ገዢው ወይም አከራዩና ተከራዩ የሚያገናኙት)፡፡ በመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ እየተረዳቸው ወደ ደላሎች ሂዱ ፤ ሂዳችሁ የተለያዩ ቤቶች እዩ ፤ስታዩ አሰፈላጊ የሚባሉትን ነገሮች መርምሩ-እወቁ፡፡ ደህና አድርጋችሁ ካያችሁ በኋላ ለእናንተ ምቹ የሆነ ቤት ምርጡ፡፡ ከደላላዩ ጋር የድለላው ስምምነት መፈራረም አለባችሁ፡፡ የመረጣችሁት ቤት እንደመረጣቸሁት እስከ መግዛት ደርሳችሁ ከገዛችሁት በኋላ ለደላላዩ የድለላው ክፊያ ትከፍላላችሁ፡፡ (በሚከተለው እንደተባለው)፡-

አስፈላጊ ነገር፡-

በድለላው ሰነድ ከምፈረም በፊት ከመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ ጋር መማከር፡፡

ደላላዩ ጊዜው ያላለፈና በድለላ ምዝገባ የተመዘገበበት ፈቃድ እንዳለው ማረጋገጥ፡፡ አንዲሁም ደላላዩ የእራሱ ፎቶ የሚገኝበት በፍትህ ሚኒስተር የተፈረመ የድለላ ፈቃዱ እንዲያሳያቸሁ ጠይቁ፡፡

የሚከተለው ዝርዝር በሚገኝበት ደላላዩ እንዲሰራላቸሁ የጠየቃቸሁበት ስምምነት መፈረም፡- የደላላዩና የገዢው ስምና መለያ መታወቂያ የሚገኝበት ስምምነት ፤ የጊዢው አይነት (ግዥ ወይም ኪራይ) የንብረቱ ሁኔታ፤ የቤቱ ዋጋ እና ለድለላ የሚከፈለው ክፍያ (ቫት የሚጨምርም ከሆነ ተጨምሮ)፡፡

የድለላ ክፍያ

በህጉ መሰረት ለደላላዩ የድለላው ክፍያ መከፈል አለበት-ግን እንዲከፈለው የሚከተሉትን ሶስት ነገሮች መተግብር (መሟላት) አለባቸው፡፡

1. ደላላዩ የድለላ ፈቃድ ካለው

2. ደላላዩ ለገዢው (ቤት ፈላጊው) ቤት እንዲያገኝለት የተፈረመ ስምምነት መኖሩ፤በአዲስ ገቢው ቋንቋ የተተረጎመ (የድለላ አገልግሎት ፎርም)

3. የሁለቱ ወገኖች ፤የሻጭና ገዢ ግዴታ ያለበት ወደ መሸጥና መግዛት ያደረሰ ስምምነት እንዲኖር ያደረገ ጥሩ ደላላይ መሆኑ፡፡

ቤት የመሸጥና መግዛት የድለላ ክፊያ ሻጩና ገዢው ሁለቱ ይከፍላሉ፡፡ በድለላው ስምምነቱ የድለላው ክፊያ ካልተጻፈ ቫትም ጨምሮ ሁለቱ ወገኖች እየአንድ አንዱ 2% ይከፍላሉ፡፡ ከዚህ በላይ አይከፈልም፡፡ የድለላው ስምምነት ከመደረጉ በፊት የሚከፈለው ገንዘብ በተመለከተ መከራከር ይቻላል-እንዲያውም በክፊያው መገባየቱ አስፈሊጊ ነው፡፡

ቤት ሲከራዩ ቤቱን የሚያከራየው ባለ ቤቱ ብቻ ነው የድለላው ክፊያ የሚከፍለው፡፡ የድለላው ክፍያ ከሚከራየው ሰው መጠየቅ ክልክል ነው፡፡ ደላዩ ተከራዩ የድለላ ክፊያ እንዲከፍለው አስቀድሞ ነግሮት (ተዋውሎት) ከሆነ ወይም ተካራዩ እራሱ ደላላዩ ቤት እንዲፈልግለት ጠይቆት ከሆነ ብቻ ነው የድለላው ክፊያ መክፈል ያለበት፡፡

እባክዎን ልብ ይበሉ፣ በእስራኤል ሀገር ያለው ህግ ለአንድ ደላላ ከ 6,000 ሸቄል (ከ2022 ጀምሮ) በጥሬ ገንዘብ መክፈልን ይከለክላል። ለማንኛውም፣ ለእያንዳንዱ ክፍያ ደረሰኝ ሊሰጥዎት ይገባል። ደረሰኝ የመቀበል መብትዎን ለማስከበር ይታገሉ

የጠበቃ አገልግሎት

ቤት ስትገዙ ለእናንተ ብቻ የሚሰራ (ሻጩ ሳይጨምር) የጠበቃ አገልግሎት ይኑራቸሁ፡፡ ጠበቃ ለማግኘት የመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛው ይረዳቸኋል ፤ እንዲሁም በስምምነቱ መፈራረሙ ይረዳቸኋል፡፡ የጠበቃው ስራ የምትገዙት ቤት ህጋዊነት ማረጋገጥ ፤ (ቤቱ የተመዘገበበት ቦታ ማወቅ ፤ ሻጩ የቤቱ ባለቤት መሆኑ ማረጋገጥ ፤ ቤቱ እዳ የሌለው በሆኑ ማረጋገጥ) የመሳሰሉና ቤቱ ከገዛቸሁት በኋላ በመሬት አስተዳደር ባለስልጣን በስማችሁ እንዲመዘገብ ማድረግ፡፡ የቤቱ መግዣ ሰነዶች ጠበቃው ያዘጋጃቸዋል፡፡ የእናንተ ጥቅም በማያጎዳ (መከበር ባለበት) አስራር ያዘጋጀዋል፡፡ ለጠበቃው አግልግሎት ገንዘብ ይከፈላል፡፡ የስምምነቱ ጽሁፍ በዕብራይስጥ ነው የሚሆነው፡፡ ካስፈለጋቹሁ ስምምነቱ በሚረዳቸሁ ቋንቋችሁ እንዲተረጎምላችሁ ጠበቃውን መጠየቅ ትችላለችሁ- በስምምነቱ መሰረት ግዴታችሁ ምን መሆኑ ደህና አድርጋችሁ ማወቅ እንድትችሉ፡፡ **የስምምነቱ ሰነዶች በሚገባ ሳትረዱ አትፈርሙ፡፡**

አስተውሉ !

በመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ ሳትረዱ (ሳትታገዙ)በሆነ ይሁን ሰነድ አትፈርሙ፡፡

አስተውሉ !

ለደላላዩም ሆነ ለጠበቃው የምትከፈሉት ክፍያ ደረሰኝ ጠይቁ (እንደ ደረሰኝ አድርጎ በእጅ የተጻፈ ብጣሽ ወረቀት አትቀበሉ)፡፡

በቤት ግዢ ስምምነት መፈራረም

በስምምነቱ ላይ ከመፈረም በፊት በጣም አስፈላጊ ነገር፡-

- ✓ የምትገዙት ቤት የሚገኝበት አካባቢ ለትምህርትም ሆነ ለስራ ምቹ መሆኑ የመርካዝ ቅሊጣው ሀላፊና የሶሽኑት ይሁዲት ሰራተኞች ጠይቁ፡፡
- ✓ የሚሰጣችሁ እርዳታ ምን ያህል መሆኑ የመርካዝ ቅሊጣው ሀላፊና የሶሽኑት ይሁዲት ሰራተኞች ጠይቁ፡፡
- ✓ የቤት መግዛት የመብት ፍቃዳችሁ ጊዜው ያላለፈና ቤት የሌላችሁ መሆኑን (ቤት የለሽ መሆናችሁ) የሚያሳይ ያለበት መሆኑ ማረጋገጥ። ፈቃዱ ከቤት እርዳታ ምዝገባ ድርጂቶቹ አንዱ ነው የሚሰጠው፡፡
- ✓ የሚገዛው ቤት፣ ህንጻውና ሰፈሩ ማታና በጨለማ ሳይሆን ምንኑቱን ለማወቅ በቀን በተደጋጋሚ ማየት፡፡
- ✓ አንዲሁም ደላላዩ የእራሱ ፎቶ የሚገኝበት በፍትህ ሚኒስተር የጸደቀ የድለላ ፈቃዱን ለማየት ጠየቁ፡፡ በየድለላው ስምምነቱ የድለላው ክፍያ በተመለከተ በጽሁፍ መስማማትና (ቫትን ጨምሮ ከ2% የማይዘል) ክፊያ ነው መሆን ያለበት-ከዚህበላይ አይከፈልም፡፡
- ✓ በቤት ግዢው ስምምነት ላይ የሚከተለውን የሚገኝበት ግዴታ ያለበት አንቀጽ መኖር አለበት። ይህ ሰምምነት ህጋዊ የሚሆነውየቤትመግዣው የገንዘብ ስጦታ መፈቀዱ ከአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ፈቃድ ከመገኘቱ በኋላ ነው የሚል፣ የቤት መግዣው የገንዘብ ስጦታ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ካልፈቀደ ሻጩ በገዢው በኩል የተከፈለው ቀብድ እንዲመልስ በቢሮው ከተጻፈለት በ5 ቀን ውስጥ መመለስ አለበት-ያለ ወለድና የገንዘቡ ተመን (ግምት) ያለመቀነስ ያለ ካሳ ወይም ያለ የሆነም ይሁን ስምምነት ባለመተግበሩ ሊኖር የሚችል ቅጣት፡፡
- ✓ ወደ ስምምነቱ ጊዜው ያላለፈ የቤት መግዛት የመብት ፈቃድ ፤ እንዲሁም ደላላዩ የእራሱ ፎቶ የሚገኝበት በፍትህ ሚኒስተር የጸደቀ የድለላ ፈቃዱ ከደላላዩ ጋር የተደረገው የድለላ ስምምነት ፤ የቤቱ ግዢ ስምምነት ኮፒ ፤ የስሞች ዘርዝር ኮፒ፡፡ የቤት ኪራይ ከሆነ ጊዜው ያላለፈ የመብቱ ፈቃድና የኪራዩ ስምምነት መጨመር፡፡

ወደ ቋሚ ቤት ማለፍ

በጊዚያዊው መኖሪያችሁ ማዕክል (መርካዝ ቅሊጣው) በቆያችሁበት ጊዜ በሀገሪቱ ኑሮው በተቻለ መጠን ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ቋሚ መኖሪያችሁ ቤት ትመራላችሁ። ለዚህ ሲባል የእስራኤል መንግስት የገንዘብ እርዳታ ያደርግላችኋል። አዲስ የምትኖሩበት ቤት ለማግኘት ከመፈለጉ ጀምሮ እስከ ስምምነት ተደርሶ መፈረሙ ድረስ ፤ ሰነዶች ማቅረብ ፤ የእርዳታ ገንዘቡ ለመቀበል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መጠየቅ እና ቤቱ እስክትገቡ ድረስ የመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ በጎናችሁ ቆሞ ይረዳችኋል።

አስተውሉ !

ለደላላይ (ገዢና ሻጭ አገናኙ) ቃል ከመግባታችሁ በፊት እና ስምምነት አድርጋችሁ ከመፈረማችሁ በፊት በመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ መረዳቱ በጣም እስፈላጊ ነው።

ለቤት መግዣ የገንዘብ ስጦታ

በመርካዝ ቅሊጣ የሚኖሩ ቤት መግዛት የሚፈልጉ የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች እንደየቤተሰባቸው ብዛት የቤት መግዣ የገንዘብ ስጦታ የመቀበል መብት ሊኖራቸው ይችላል። የቤቱ መግዣ የገንዘቡ ስጦታ በግንባታና የቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ ነው የሚሰጠው፡

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው የግንባታና የቤት ዕደላ ሚኒስተር የኢንተርኔት ድረ ገጽ ግቡ።

የገንዘቡ ስጦታ ለመቀበል ቤት የሌላችሁ መሆኑ የምስክር ወረቀት (የመቀበል መብት እንዲኖር የሚያደርግ ፈቃድ) ለቤት መግዣ ከብድር ሰጪዎቹ ባንኮች አንዱ መቀበል ያስፈልግል። ይህ ለማድረግ የመርካዝ ቅሊጣው ለእናንተ የሚሰራው ሰራተኛ ይረዳችኋል። የገንዘቡ ስጦታ በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ጠይቁ።

ከሚደረግላችሁ የገንዘብ ስጦታ ጎን ለጎን በየቤት ግዥ ብድር አበዳሪዎቹ ባንኮች ውሳኔ መሰረት ተጫማሪ የገንዘብ ብድር ይገባችኋል። ይህ ብድር የሚገዛው ቤት ለባንኩ በመያዣ በማስያዝ ነው የሚሰጠው።

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው የግንባታና የቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ ሊንክ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/departments/guides/maanakey-diyur-leoley-ethiopia?chapterIndex=1

ማማከር ፤ የገንዘብ አጠቃቀም የመረዳት መከታተል (እገዛ)

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ በመርካዝ ቅሊጣ የሚኖሩ አዲስ ገቢዎችና በተደረገላቸው የገንዘብ እርዳታ ቤት ለመግዛት የሚፈልጉት የገንዘብ አጠቃቀም "ዖገን" ከሚባለው አማካሪ አካል እንዲያማክሩ ተስማምቷል። "ዖገን" ቡድን የኢኮኖሚ አስተዳደራቸው (አጠቃቀማቸው) እና ከባንኮቹ ብድር የመበደራቸው ሁኔታ ምን ያህል ነው የሚል ክትትል እንዲደረግ የሚፈልጉ ሁሉ አድራሻ ነው።"ዖገን" ቡድን እየአንድ አንዱ ቤተሰብ የሚያስፈልጋቸውን ብድር እንዲበደሩ አስፈላጊነታቸው በሚመለከት ይከታተልላቸዋል-ይረዳቸዋል።

ብድር የመበደር መብት (ለቤት መግዣ ከመንግስት የገንዘብ ብድር)

የቤት መግዣ ስጦታ የማይሰጠው ሰው ሁሉ በመንግስት ውሳኔ መሰረት ከግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ የቤት መግዣ ብድር ሊሰጠው ይችላል። ብድሩ የመበደር የመብት ፈቃድ በአበዳሪው ባንክ በኩል ነው የሚሰጠው። ብድሩ ቤት ለሌላቸው አዲስ ገቢዎች ነው የሚሰጠው። የብድር መብቱ የሚመለከታቸው እና የመበደር መብት የሚያሰጥ ጊዜው ያላለፈ ፈቃድ በእጃቸው ላላቸው ሰዎች ነው የሚሰጠው። የብድሩ መብታችሁ ለማጣራት ወደ የቤት መግዣ ብድር የሚያበድሩት ባንኮች አንዱ ጉብታችሁ ጠይቁ።

በቤት ግዥ ግብር ቅናሽ ከፊያ

በእስራኤል ቤት የሚገዛ ሁሉ የቤት ግዥ ግብር ይከፍላል። አዲስ ገቢዎች ግን በእስራኤል የሚገዙት ቤት ከግብር ከፊያው ቅናሽ ሊደረግላቸው ይችላል። ቅናሽ የመከፈሉ ጥያቄ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ በሚገኘው የመሬት ግብር ከፊያ ባለ ስልጣን መጠየቅ ይቻላል። ሲጠይቁ በጥያቄው ላይ አስፈላጊዎቹን ሰነዶች መጨመር ያስፈልጋል። ቤት ስትገዙ የመግዛቱ ጠበቃችሁ በሚመለከቱት ሁሉ ሰነዶች ያስፈርማችኋል።

አንድ ነብስ ለሆኑና ለሺማግሌዎች በቤት ኪራይ ከፊያ እርዳታ

ብቸኞችና ብቸኛ ሺማግሌዎች እንዲሁም ባለቲዳር ሺማግሌዎች ጨምሮ ለቤት የሚደረግላቸው የ90 ሺህ ሸቀል ስጦታ ለቤት ኪራይ ለ5 ዓመት ለሚሰጣቸው እርዳታው ወደ 1.500 ሸቀል ከፍ እንዲል እንዲደረግላቸው ማድረግ ይችላሉ። ለየወሩ1.500 ሸቀል ለ60 ወራት ማለት ነው። ይህ መብት መተግበር/መጠቀም የሚቻለው ቤት የለውም የሚል የቤት የለሽ የመብት ፈቃድ ከመቀበል በኋላና የኪራዩ ስምምነትና የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ፈቃድ ያስፈልጋል። የቤት ኪራዩ እርዳታ በግንባታና ቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ በኩል ነው የሚሰጠው።

የቤት ኪራይ እርዳታ የሚደረግላቸው የቤት ኪራዩ እርዳታ መሰጠት ከተጀመረው የቤት መግዣ የስጦታቸው መብት ለ5 ዓመት ይጠበቅላቸዋል- መርካዝ ቅሊጣ ለሚኖሩት እንደሚደረገው። የቤት መግዣው እርዳታ የቤት ኪራዩ እርዳታ መሰጠት ከተጀመረ ከሁለተኛው ዓመት ጀምሮ እስከ 5 ዓመት መጠቀም ይቻላል። አዲስ ገቢዎቹ ከ5 ዓመት በኋላም በቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ በኩል አዲስ ገቢዎች በመሆናቸው ምክንያት እንደሚገባቸው ሁሉ በሚደርገው እርዳታ መሰረት መብት ላላቸው በሚሰጠው ህግ መሰረት በግንባታና የቤት ዕደላ ሚኒስተር ቢሮ የቤት ኪራይ እርዳታ የገባቸዋል።

የቤት ኪራይ እርዳታው የሚሰጠው ቤት እንደሌላቸው (ቤት የለሽ መሆናቸው) የምስክር ወረቀት ላላቸው ነው። የምስክር ወረቀቱ ለመቀበል የመርካዝ ቅሊጣው ለእናንተ የሚሰራው ሰራተኛ ይረዳችኋል። እንዲሁም ወደ የቤቶች አስተዳደር ባለስልጣን ይመራችኋል። አሚዳር ፤ ሚልጋም ፤ ወይም መርካዝ አሎኒም ወደ የሚባሉት የቤቶች አስተዳደር ድርጂቶች።

ቤት የሌላችሁ መሆኑ የቤት የለሽ የምስክር ወረቀት ስትጠይቁ የሚከተሉትን ሰነዶች ይዛችሁ ቅርቡ፡-

- ማታወቂያ
- የአዲስ ገቢ ማታወቂያ
- የቤተሰባችሁ ሁኔታ የሚያሰዩ-እንደ የጋብቻ ፈቃድ ፤ የፍች ፈቃድ ፤ ከባልና ሚስቱ አንዱ ከሞተ/ችየመሞት ምስክር ወረቀት የመሳሰሉት የሚገኙባቸው ሰነዶች
- እርግዝና በተመለከተ-የተረገዘ እርግዝና ካለ ከተረገዘ አምስት ወር ከሆነው በኋላ ከታወቀ የማርገዙ የህክምና ተቋም ፈቃድ-የምስክር ወረቀት
- ጥያቄው እስከቀረበበት ድረስ የመጨረሻዎቹ 6 ወራት የወር ገቢ የሚያሳይ ፈቃድ
- የሚጠየቅ ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሰነዶች

ለተጨማሪ መረጃ ወደ እሚከተለው የግንባታ ሚኒስተር ሊንክ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/departments/guides/maanakey-diyur-leoley-ethiopia?chapterIndex=1

ለቤት መግዣ የሚለገሰው ስጦታና የቤት አገዛዝ ሂደት

በምታደርጉት ሁሉ የመርካዝ ቅሊጣው የሰራተኞች ቡድኑ አባላት ይረድዋችኋል።

1. የቤት መግዣ የመብት ፈቃድ ከቤቶች መግዣ ብድር አበዳሪዎቹ ባንኮች ቤት የሌላችሁ (ቤት የለሽ) መሆናችሁ የሚያሳይ ፈቃድ ማውጣት።

ይቆያል:: የጊዩሩ ትምህርት ኤልፓን ለአንድ ዓመት(1000 ስኣታት) ሲሆን ይዘቱ ከሰዓት ነው የሚካሄደው::

ለብራይስጥ ትምህርት የቁፖን እርዳታ ፕሮግራም

መርካዝ ቅሊጣው ከተዋቸሁ በኋላ ዕብራይስጥ በግል ትምህርት መማር ትችላላችሁ::

የቅሊጣና አሊያ ቢሮ በግል ትምህርት ለሚማሩ ለሚማሩበት ትምህርት የሚከፍሉት ክፊያ እርዳታ በየቁፖን እገዛ ያደርጋል:: እርዳታው እንዲደረግላቸው መብት ላላቸው ሲሆን እርዳታው በተቻለ መጠንና በጀት በመኖሩ ይገደባል:: ትምህርቱ ዕውቅና ባላቸው የትምህርት ተቋማትና በቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር የኢንተርነት ድረ ገጽ የሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች ነው:: የቁፖኑ (ቫውቸሩ) መጠቀም መብት ጊዜ እስራኤል ከገቡ ጀምሮ እስከ 15 ዓመት ነው::

የቁፖኑ እርዳታ የሚገባችሁ ከሆነ የአዲስ ገቢዎቹ አማካሪ ጠይቁ::

የዕብራይስጥ ትምህርት በኦን-ላይን

የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የዕብራይስጥ ቋንቋ ማዳበር በሚል ፕሮጀክት "ቅሰሙ" የሚል የዕብራይስጥ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም በኢንተርነት ማወቅ ፣ በቋንቋው መስታዎት የእስራኤል ባህል ማጥናትና ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ነው::

የኢንተርነት ድረ ገጹ አድራሻ የሚከተለው ነው:- https://govextra.gov.il/moia/learn-hebrew-he/he/

በቺግር ጊዜ እርዳታ

የእርዳታ እና ለአዲስ ገቢዎች የጭንቀት በሺታ የባለሞያዎች የእገዛ ማዕከል

የአሊና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ኣራን ከተባለው ድርጀት በመተባበር የጭንቀት በሺታ ላላቸው አዲስ ገቢዎችና ተመላሽ ዜጎች እርዳታ የሚሰጥበት ማዕከል አለው:: እርዳታው በተለያዩ ቋንቋዎች በጭንቀት በሺታ ረገድ ባለሞያ በሆኑት ነው የሚሰጠው:: የማዕከሉ እርዳታ (አዲስ ገቢ እስራኤል የኖሩበት ጊዜ ብዛት ባለመቁጠር) ዕድሚያቸው ከ18 ዓመት ከሆነ ጀምሮ ነው የሚደረገው:: የእርዳታ ፈላጊዎች የእርዳታው ጥያቄ በአጠቃላይ በሚስጥር የተጠበቀ ነው::

ማዕከሉ ከሚያደርጋቸው እርዳታዎች:-

- የአዲስገቢ በሀገሪቱ በሚያልፉት ሂደት ምክንያት የጭንቀት በሺታ ላላቸው አዲስ ገቢዎች:: ከባህላቸውና ልምዳቸው ጋር የሚሄድ (የሚስማማ) እርዳታ ማድረግ
- ብቸኝነትን ማቃለል
- የግልና የቤተሰብ የማበረታቻ እርዳታ
- እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወላጆች የሚንከባከቡ አዲስ ገቢዎች የነበስ ጭንቀት እርዳታ
- በጭንቀትና አስቸጋሪ ሁኔታ ጊዜ ችግሩን የመቋቋም እርዳታ
- አስፈላጊ ከሆነ በመከታተል ወደ ባለሞያዎች መላክ

ማዕከሉ በሚከተሉት ቋንቋዎች ነው የሚሰራው:- እንግሊዘኛ ፣ ሩሲያኛ ፣ አማርኛ፣ ፈረንሳኛ እና እስፓኛ: : የሚሰራባቸው ቀናት:- ከእሁድ እስከ ሀሙስ ከ16:00 እሰከ 21:00 (የባአላት ዋዜማና ባአላትን ሳይጨምር) :: የተደወለ ስልክ መቀበል በማይኖርበት ጊዜ መልእክት ታስቀምጡና ስራ በሚጀመርበት ቀን ዙሮ ይደወልላችኋል::

የማዕከሉ ስልክ:- *3201

በጊዚያዊ የክፉ ችግር ወቅት በክፍለ ሀገሩ አስተዳደር የሚደረግ ልዩ እርዳታ

በጊዚያዊ የክፉ ችግር ወቅት የአካባቢው አዲስ ገቢዎች ተቀብሎ ማስተናገድ-የቅሊጣ ጉዳዮች ኣማካሪ መጠየቅ ወይም የቦታው የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ቅርንጫፍ የገንዘብ እርዳታ መጠየቅ-የዚህ አይነት እርዳታ ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚደረገው:: ለተጨማሪ መረጃ ከአዲስ ገቢዎች ተቀብሎ ማስተናገድ የቅሊጣው ኣማካሪ መጠየቅ ይቻላል::

አስተውሉ !

በጊዚያዊው መኖርያ (መርካዝ ቅሊጣ) በምትቆዩበት ጊዜ እንደ በቢጥዋኽ ልኡሚ የሚከፈላችሁ ክፊያ የመሳሰሉ መብቶች ሊኖሮአችሁ ይችላል:: የተለያዩ መብቶች በሚከተሉት አንቀጾች ቀርበዋል::

ከፍትህና ፍርድ ሚኒስተር ቢሮ የጠበቃ እርዳታ

አዲስ ገቢዎች እንደ በሙግዚትነት ህጻናት ማሳደግ ፣ ከስራ አሰሪ የሚገባቸውን (የገንዘብ-መብት) መጠየቅ የመሳሰሉና የተለያዩ ጉዳዮች በፍትህና ፍርድ ሚኒስተር ቢሮ የጠበቃ እርዳታ ሊደረግላቸው ይችላል::

ከጊዚያዊው መኖርያ ማዕከል (መርካዝ ቅሊጣ) መውጣት-መልቀቅ

በጊዚያዊው መኖርያ ማዕከል (መርካዝ ቅሊጣ) ቆይታቸሁ ከአበቃ በኋላ ወደ ቋሚ መኖሪያ ቤት ትመራላችሁ/ታልፋላችሁ:: በህዝባዊ ቤት የመኖር መብት ላላቸው ሰዎች ቤቱ ተመርተው ተሰጥቷቸው ሊኖሩ ይችላሉ:: ይህን በተመለከተ በሚከተለው ቋሚ መኖርያ ቤት በሚለው ምዕራፍ የሰፈረው መረጃ ተመልከቱ:: ቤት በመፈለጉ ሂደት ላይ ፣ ገንዘብ በማዘጋጀቱና ስምምነቱ ተፈራርሞ እስከ ቤቱ መግባት ድረስ የጊዚያዊው መኖርያ ማዕከሉ (መርካዝ ቅሊጣው) ሰራተኞች ይረድዋችኋል::

አስተውሉ !

ቤት በመግዛቱ ሁሉና (ወይም በመከራየቱ) ሂደት ሁሉ ያለ የጊዚያዊው መኖርያ ማዕከሉ (መርካዝ ቅሊጣው) ሰራተኞች እርዳታ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ጉዳይ ምንም ነገር አታድርጉ::

ጊዚያዊው መቆያ ማዕከሉ (መርካዝ ቅሊጣው) ለሚለቁ የቤት እቃ መግዣ የገንዘብ እርዳታ

ጊዚያዊው መቆያ ማዕከል (መርካዝ ቅሊጣው) ለሚለቁ እንደ የቁም ሳጥን ፤ ፍሪጅ እና ማብሰያ ምድጃ የመሳሰሉት መግዣ የገንዘብ እርዳታ ሊሰጣቸው ይችላል:: ይህ መብት ለመተግበር ጊዚያዊው መቆያ ማዕከሉ (መርካዝ ቅሊጣው) የመተዋቸሁ ምስክር ወረቀት ይዛችሁ የመኖሪያችሁ አካባቢ የቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ ጠይቁ:: ወደ "ቋሚ መኖሪያ ቤት ማለፍ" የቤት ተጨማሪ እርዳታ የሚለውን አንቀጽ ተመልከቱ::

ፕሮጀክተሮች (አዲስ ገቢዎች በአዲስ ኑሮአቸው በመከታተል የሚረዱ የመዘጋጃ ቤቶች ሰራተኞች)

መዘጋጃ ቤቶች አማርኛና ትግርኛ ተናጋሪ አዲስ ገቢዎች የቆዩበት ጊዚያዊ መኖሪያ ማዕከል ለቀው ወጥተው ቋሚ መኖሪያ ቤት ከተሰጣቸው በኋላ በአዲስ ኑሮአቸው እንዲረዱ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮእገዛ ያደርግላቸዋል:: ፕሮጀክቶሮቹ በምትኖሩባቸው አካባቢዎች እንደ ምቹ ኑሮ እንዲኖራችሁ፤ ምክር፤ትምህርት ቤትና መኖሪያ ቤት በመምረጥ፤የገንዘብ እርዳታ፤ሰነዶች መተርጎምና ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ ይረድዋችኋል:: የአካባቢያችሁ ሰራተኛው የፕሮጀክቶሩ ስልክ ቁጥር የኑሮአችሁ አማካሪ ጠይቃችሁ ብትቀበሉ ይመረጣል::

ሳል ቅሊጣው ለስንት ጊዜ ነው የሚሰጠው

የአዲስ ገቢ ስታቱስ ካገኙወይምየአዲስ ገቢመብት ከተሰጣቸውጀምሮ ለአንድ ዓመት ነው።

ውጪ አገር መሄድ የሳል ቅሊጣው ክፊያ ያቆማል። ወጪ አገር ሂደው ከሄዱ በመጀመሪያው ዓመታቸው የተመለሱ የሳል ቅሊጣ ክፊያቸው ይታደሳል። ከተመለሱ በኋላ ክፊያው መታደሱ ያረጋግጡ ፤ካልሆነም እንደአስፈላጊነቱ የአዲስ ገቢዎች የኑሮ ጉዳዮች አማካሪ መጠየቅ።

የሳል ቅሊጣው እርዳታ አከፋፈል

ሳል ቅሊጣው በ13 ክፊያዎች ነው የሚሰጠው። የመጀመሪያው ክፊያ አዲስ ገቢዎቹና እንደደረሱ ግማሹ በቤን ግሩዮን አየር ማረፊያ በጥሬ ገንዘብ ሲሰጣቸው የቀረው ወደ ባንክ ሂሳባቸው ይተላለፍላቸዋል። የቀረው ክፍያ በ12 ወራት በየወሩ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ይተላለፍላቸዋል። የሳል ቅሊጣው ገንዘብ ወደ ባንክ ሂሳባችሁ እንዲተላለፍላችሁ የእስራኤል ገንዘብ የባንክ ሂሳብ ከፍታችሁ አንድ ሸቀልም ቢሆን ገንዘብ አኑሩበት-ይህን በተመለከተ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ዝርዝር እዩ።

ሳል ቅሊጣ በሚል የሚታወቀው እርዳታ በመከፈሉ የሆነም ይሁን ስህተት ከተከሰተ ወዲያውኑ የአዲስ ኑሮው አማካሪ ጠይቁ።

እስራኤል ከገቡ ከሁለተኛው ዓመት ጀምሮ በቢጡዋኽ ልኡሚ የሚከፈል የገቢ ማረጋገጫ ክፊያ

እስራኤል አገር ከገባችሁ ሁለተኛው ዓመት ሲጀምርና የሳል ቅሊጣው የሚደረግላችሁ እርዳታ መለገሱ ሲያበቃ በቢጡዋኽ ልኡሚየገቢ ማረጋገጫ ክፊያ እንዲከፈላችሁ የሚያደርግ መብት ሊኖራችሁ ይችላል። ይህን በተመለከተ ወደ ቢጡዋኽ ልኡሚ ቢሮ ጥያቄ መቅርብ ይኖርባችኋል። ከዚህ ጎን ለጎን በስራ ሰጪ ቢሮ ተመዝግባችሁ መዝገብ በመክፈት በወር አንድ ቀን (እንደ የቢሮው ሰራተኞች ውሳኔ) በቦታው መገኘት አለባችሁ።

በቢጡዋኽ ልኡሚ የገቢ ማረጋገጫ ክፊያ የሚከፈለው ጥያቄው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን ከጥያቄው ጋር አስፈላጊዎቹ ሰነዶች በማያያዝ ማቅረቡ ግዴታ ነው።

አስተዉሉ !

ባልና ሚስት አብረው ካልቀረቡ የገቢ ማረጋገጫው ክፊያ ሊያሰጣችሁ የሚችል መብት አይኖራቸውም።

የእብራይስጥ ትምህርት ኡልፓን ተምረው ትምህርታቸው ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ስራ ሰጪ ቢሮ ወይም ወደ ቢጡዋኽ ልኡሚ መሄድ የለባቸውም። ስራ መያዝ በተመለከተ በምዕራፉ መጨረሻ ላይና ስራ በሚለው አንቀጽ ተመልከቱ።

የገቢ ማረጋገጫው ክፊያ በተመለከተ ለተጨማሪ ዝርዝር በቢጡዋኽ ልኡሚ አንቀጽ ተመልከቱ። እንዲሁም በዚሁ www.btl.gov.il የቢሮው ድረ ገጽ አድራሻና የኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ቢጡዋኽ ልኡሚው መጽሄት መረጃ ማግኘት ትችላለችሁ።

ልጆች በትምህርት ቤት ማስመዝገብ

የትምህርት ግዴታ ህግ

የ1949ኙ የመማር ግዴታ ህግ (የትምህርት ግዴታ ህግ በሚልም የሚታወቀው) የእስርኤል ልጅ ሁሉበመዋዕለ ህጻናትና በትምህርት ቤት እንዲማር ያስገድዳል። በአሁኑ ጊዜ ትምህርቱ በሚጀመርበት ወቅት ዕድሚያቸው ከ 3 እስከ 17 ዓመት የሆነ ልጆችና ታዳጊ ልጆች ሁሉ እንዲማሩ የትምህርት ግዴታ ህጉ ይመለከታቸዋል። ተጨማሪ መረጃ በዚሁ ጽሁፍ በሚከተለው ትምህርት በሚለው አንቀጽ ታገኛላችሁ።

ልጆችን እንደየዕድሚያቸው በትምህርት ቤቶች ማስመዝገብ ያስፈልጋል።

ዕድሚያቸው ከ3 ወር እስከ 3 ዓመት የሆነ መማራቸው ግዴታ አይደለም። የሚፈልጉ ሁሉ በመንግስት ቁጥጥር በሚሰሩ የቀን ሆስቴሎች በሚባሉ የህጻናት መዋያ ወይም ህዝባዊ ቤተሰባዊ በሚባሉት መጣም ህጻናት የሆኑት መዋያ በክፊያ የሚሰሩ ቦታዎች ማስመዝገብ ይችላሉ።

ዕድሚያቸው ከ 3 እስከ 6 ዓመት የሆነ በመዋዕለ ህጻናት።

ዕድሚያቸው ከ 6 እስከ 12 ዓመት የሆነ-በመሰረታዊ ትምህርት ቤት(ከ1ኛ እስከ 2ኛ ክፍል)።

ዕድሚያቸው ከ 12 እስከ 15 ዓመት የሆነ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች(ከ7ኛ እስከ 9ኛ ክፍል)።

ዕድሚያቸው ከ 15 እስከ 18 ዓመት የሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች(ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል)።

አከፋፈላቸው ከዚህ የተለየ ትምህርት ቤቶችም አሉ። ለምሳሌ መሰረታዊ ትምህርት ቤቶች ሆኖው ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የሚማሩባቸው።

አመዘጋገቡ

ልጆቻችሁ ለትምህርት ስትመዘግቡ የጊዚያዊው መኖሪያችሁ (መርካዝ ቅሊጣው) ሰራተኞች ይረዷቹኋል።

የቀን የህጻናት መዋያ መዋዕለ ህጻናትና የትናንሽ ህጻናት እንክብካቤ ምዝገባ

በ-የቀን የህጻናት መዋያ መዋዕለ ህጻናትና የትናንሽ ህጻናት መንከባከቢያ ምዝገባ በኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ የአሰራር ክፍል ይደረጋል። በምዝገባው ሂደት የመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኞች ይረድዋችኋል።

በመዋዕለ ህጻናትና በትምህርት ቤት ልጆችን ማስመዝገብ

የመሰረታዊ ትምህርት ቤትና የመዋዕለ ህጻናት ምዝገባ በመዘጋጃ ቤት በኩል ነው የሚሆነው።

ዛሬ በአብዛኛዎቹ መዘጋጃ ቤቶች ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ቤቶች ለማስመዝገብ ተብሎ በተዘጋጀ በተረጋገጠ የኢንተርነት ድረ ገጽ-ፖርታል ማስመዝገብ ይችላሉ፦
www.cityedu.co.il

ወደ ሰከንደሪ ሰኩል በመዘጋጃ ቤቶች ወይም በትምህርት ቤቱ ማስመዝገብ ይቻላል-እንደ አካባቢው ሁኔታ።

የቢጡዋኽ ልኡሚ ቢሮን መጠየቅ

እስራኤለ እንደደረሳችሁ የገንዘብ ድርሻችሁ ያለችሁን መብት ለማወቅ ቢጡዋኽ ልኡሚን ጠይቁ። የመርካዝ ቅሊጣው ሰራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ወደ ቢታው አብረዋችሁ መሄድ ድረስ ይረድዋችኋል።

ዕድሚያቸው እስከ 18 ዓመት የሆነ ልጆች ያልዋቸው ቤተሰቦች ከቢጡዋኽ ልዐሚ ቢሮ የልጆች ክፍያ ይገባቸዋል። ክፊያው ቀጥታ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ይተላለፍላቸዋል።

ዕድሚያቸው ጠሮታ የደረሰ አዲስ ገቢዎች የጠሮታ ክፍያቸው ጥያቄ ቢጥዋኽ ልኡሚን እንዴት መጠየቅ እንዳለባቸው ለማወቅ የሚኖሩበት ማዕከል ረጂዎቻቸውን ይጠቁ።

ለቢጡዋኽ ልኡሚ ዋስትና መክፈል ያስፈልጋል። አዲስ ገቢዎች በእስራኤል በመጀመሪያ ወራት ኑሮአቸው ከዋስትናው ክፍያ ነጻ ናቸው/አይከፍሉም። ከዋስትናው ክፍያ ነጻ መሆናቸው ለስንት ጊዜ መሆኑ ማጣራት ይኖርባቸዋል። ነጻ የመሆኑ ጊዜ ከአበቃ በኋላ አከፋፈሉ እንዴት እንደሆነ አጣርቶ መክፈሉ መጀመር። ይህን በተመለከ ተጨማሪ መረጃ ቢጡዋኽ ልኡሚ የሚለውን አንቀጽ ተመልከቱ።

የቢጡዋኽ ልኡሚ ስልክ ቁጥር *6050 እና የኢንተርኔቱ ድረ ገጽ፦ www.btl.gov.il

የዕብራይስጥና የጊዩር ትምህርት

እስራኤል እንደደረሳችሁ የመጀመሪያ መዘጋጀትና መደራጀት ካደረጋችሁ በኋላ የዕብራይስጥና የጉዩር ትምህርት (ኡልፓን) ትማራላችሁ። የዕብራይስጡ ትምህርት ኡልፓን በየጥዋቱ ስዓታት በሳምንት 5 ቀናት ለ10 ወራት

*3833፣ ለኤሚት የስልክ ቁጥር፡- *507 ሲሆኑ ከመካከላቸው በመረጣችሁት አንዱ መመዝገብ ትችላላችሁ፡፡ አየር ማረፊያ እንደደረሳችሁ ጀምሮ መመዝገብ ይቻላል (ያለ ክፍያ)፡፡ በአየር ማረፊያ ካልተመዘገበችሁ በፖስታ ቤት አንዱ ቅርንጫፍ (በክፍያ) መመዝገብ ትችሉ አላቸሁ፡፡ ወይም እስራኤል ከደረሳችሁ ከሰወስት ወር በኋላ በቢጡዋኽ ልኡሚ ድረ ገጽ (ያለ ክፍያ) መመዝገብ ትችላላችሁ፡፡ ከተመዘገባችሁ በኋላ ምዝገባው ለማሟላት ያህል ወደ ጤና ጣቢያዉ ግዴታ መሄድ አለባችሁ፡፡ ምዝገባችሁ ወደ መኖሪያ ቤታችሁ ቅርብ በሆነ ጤና ጣቢያ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ሂደቱ በምታደርጉበት ጊዜ የምትኖሩበት ጊዚያዊ ማዕከል ሰራተኛ ይረዳችኋል፡፡

አስተዉሉ !

የህክምና አገልግሎት በሚያስፈልጋችሁ ሁሉ እንዲሰጣችሁ (መቀበል እንድትችሉ) እስራኤል እንደደረሳችሁ ወዲያዉኑ በጤና ጣቢያ መመዝገባችሁ በጣም አስፈልጊ ነው፡፡ አለመመዝገባችሁ ህክምና ሲያስፈልጋችሁ ያላስፈላጊ ችግር ፈጥሮ ያልተጠበቀ ወጪ ሊያስወጣችሁም ይችላል፡፡

ሙሉ በሙሉ ከተመዘገባችሁ በሁዋላ በመኖሪያ ሰፈራችሁ አካባቢ በሚገኘው የተመዘገባችሁበት የጤና ጣቢያ ቅርንጫፍ የህክምና አገልግሎት ይሰጣችኋል፡፡

አስተዉሉ !

እስራኤል እንደደረሰ በጤና ጣቢያ በ 90 ቀን ውስጥ ያልተመዘገበ ሰው በቢጡዋኽ ልኡሚ ብቻ ነው መመዝገብ የሚችለው፡፡

የጤና ዋስትና ክፊያ በተመለከተ የጤና እና የቢጥዋኽ ልኡሚ አገልግሎት ዋስትና በሚሉት አንቀጾች ተመልከቱ፡፡

የባንክ ሂሳብ መክፈት

የሚገባችሁን የገንዘብ እርዳታ ለመቀበል ያህል የእስራኤል ገንዘብ ሂሳብ በመረጣችሁት ባንክ ሁሉ መክፈት አለባችሁ፡፡ የቤተሰቡ ቁጥር ባልና ሚስት ብቻ የሆናችሁ ሁሉ የባንክ ሂሳቡ በሁለታችሁ ስም ስለሚሆን ሁለታችሁ በባንኩ ተገኝታችሁ ሂሳቡ ብትከፍቱት ይመረጣል፡፡ ሂሳቡ ስትከፍቱ የምትኖሩበት ማዕከል ሰራተኛ አብርዋችሁ ቢገኝ ይምረጣል፡፡

ወደ ከፈታችሁት የባንክ ሂሳብ የእርዳታው ገንዘብ ማስተላለፍ እንዲቻል ተንቀሳቃሽ ይሆን ዘንድ የሆነም ይሁን ገንዘብ (አንድ ሽቀልም ቢሆን) ማስቀመጥ አለባእሁ፡፡ ሂሳቡ ከከፈታችሁ በኋላ የከፈታችሁበት የመክፈቻው ዝርዝር የያዘው ፈቃድ (ዋናው) ለኑሮአችሁ አማካሪው ስጡ፡፡ እንዲሁም ሂሳብ የተከፈተበት ዝርዝር የሚገኝበት ፈቃዱ ለቢጡዋኽ ልኡሚ መስጠት እንዲቻል ኮፒው ቢጡዋኽ ልኡሚ በተመለከተ ለሚከታተለው ሰራተኛ ስጡ፡፡ ቢጡዋኽ ልኡሚ ለልጆች የሚገባ እና ሌላም የሚገባ ክፍያ ካለ በዛ መሰረት እንዲከፍላችሁ፡፡

አስተዉሉ !

እስራኤል ከገባችሁ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የባንክ ሂሳቡ መቀየር አይስፈልግም፡፡ ለመቀየር ተገዳችሁ ከቀየራችሁ መቀየራችሁ ለኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር እና ለቢጡዋኽ ልኡሚ ቢሮዎች አሳውቁ፡፡

የባንክሂሳብ ለመክፈት የሚያስፈልጉት ሰነዶች

- የአዲስ ገቢ ፈቃድ/የባልና ሚስቱ የመብት ፈቃድ፡፡
- ከባልና ሚስቱ አንዱ ባንክ መሄድ የማይችል/ትችል ከሆነ/ች ለሚሄደው የኖቶሪ ውክልና ያስፈልጋል፡፡
- ማታወቂያ ተሰጥቷቸው ከሆነ ይዞ መቅረብ፡፡ በህግ መሰረት ባንኮች አዲስገቢ እስራኤል ከደረሰ እስከ 30 ቀኖች ድረስ በማታወቂያ ፈንታ የአሊያ ፈቃድ (ማታወቂያ) ይቀበላሉ፡፡ የመብት ፈቃድ ያላቸው ሁሉ አስቀድመው በህዝብ ምዝገባ ቢሮ ማታወቂያ ማውጣት አለባቸው፡፡ ከመጣችሁበት አገር በገቢዎች ቢሮ መዝገብ ቁጥር የሚጠይቁ ባንኮች መኖራቸው እወቁ፡፡

አስተዉሉ !

ሂሳብ ከከፈታችሁባቸው ባንኮች የመከፈታችሁ ፈቃድ (ደረሰኝ) መቀበሉ አትርሱ (በሂሳቡ ገንዘብ የማስገባታችሁ ደረሰኝ እንዲሰጣችሁ ብትጠይቁ ይመረጣል)፡፡ የእርዳታው ገንዘብ ቀጥታ ወደ ሂሳባችሁ እንዲገባላችሁ የባንኩ ሂሳብ ደረሰኝ ከአዲስ ኑሮው አማካሪ ስትገናኙ ይዛችሁት ቅረቡ፡፡

ከየመጀመሪያው ኑሮ የግል አማካሪ ጋር መገናኘት

የመጀመሪያውና ዋናው የሚረዳችሁ የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የግላችሁ አማካሪው ነው፡፡ በመጀመሪያው የምትኖሩበት ማዕከል ከግል አማካሪያችሁ ጋር ለመተዋወቅ ፣ መንነታችሁን ለማረጋገጥ፣ የሚሰጣችሁ የገንዘብ እርዳታ እና በእስራኤል የመጀመሪያው ኖሮአችሁ በተመለከተ መረጃ ለመሰጠት ትገናኙት አላችሁ፡፡ ወደ የግሉ አማካሪ ግንኙነት በባንክ ሂሳብ የከፈታችሁበት ደረሰኙና የመብት ፈቃድ ይዛችሁ ቀረቡ፡፡

የአዲሱ ኑሮ አማካሪ በአን-ላይን መጠየቅ

የአሊያና ቅሊጣ ቢሮ የአዲስ ገቢዎች የዲጂታሉ አገልግሎት አስፋፍቷል፡፡ ማስፋፋቱ የቅሊጣው አማካሪ በአን-ላይን (በኮምፒውተር ወይም በሞባይል) በግሉ የኢንተርነት ድረ ገጽ በኩል መጠየቅ የሚያስችል አድርጎታል፡፡ ይህ የተደረገው ከቂሊጣው አማካሪ ጋር በአካል ያለመገናኘት ቅጽበታዊና ጠቃሚ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ አገልግሎቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ይሰጣል፡፡

በዚህ አይነት አካሄድ የሚከተለውን ያካተቱ በርካታ ስራዎች ማከናወን ይቻላል፡-

- ወደ የመጀመሪያው ኑሮ አማካሪ በአን-ላይን ጥያቄ መላክ
- ጥያቄ ማቅረብና ጉዳይን ማጣራት
- የጸሁፍ ጥያቄ ፎርሞና አብረው የሚሄዱ ሰነዶች መላክ
- መረጃ መቀበል
- ሰነዶች መላክ
- ፈቃድ ማውጣት

ጥያቄው በ5 የስራ ቀኖች ውስጥ ይታያል፡፡ መታየቱ ካበቃ በኋላ ጥያቄው መድረሱ የማሳወቅ መልእክት ለጠያቂው በግሉ ድረ ገጽ ይላክለታል፡፡ አገልግሎቱ ለመቀበል በመንግስታዊው የመረጃ አገልግሎት ድረ ገጽ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ ወደ እሚከተለው ድረ ገጽ በመግባት፡-
https://my.gov.il/landing

ከዛ በኋላ ወደ እሚከተለው የቅሊጣና አሊያ ሚኒስተር ቢሮ የግል ድረ ገጽ መግባት ይቻላል፡-
https://www.gov.il/ssoapps/moia/personalinfo

ሳል-ቅሊጣ መቀበል

ሳል ቅሊጣ በሚል አጠራር የሚታወቀው የገንዘብ እርዳታ አዲስ ገቢ እስራኤል እንደደረሰ በመጀመሪያዎቹ ጊዚያቶች ለመደራጀቱ የሚለገስ እርዳታ ነው፡፡ እርዳታው በየወሩ የሚሰጥ ሲሆን ለኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች ለዓመት ያህል ይለገሳል፡፡ ሳል ቅሊጣው ቤተሰባዊ ሲሆን(ዕድምያቸው እስካ 21 ዓመት የሆነ ልጆች ላኋዋቸው ቤተሰቦች ሁሉ የሚሰጥ ነው፡፡ ስንትነቱ (ልኩ) በቤተሰብ ብዛት መሰረት ይወሰናል፡፡ ገንዘቡ የገቢ ማረጋገጫ ክፊያም ያካተተ ነው፡፡

እድምያቸው ከ18 እስከ 21 ዓመት የሆነ እና በቤተሰቡ የአዲስ ገቢ ማታወቂያ የተመዘገቡ የአዲስ ገቢዎች ልጆች እስራኤል ከገቡበት ከሰባተኛው ወር ጀምሮ እስከ 12ኛው ወር ከቤተሰባቸው ለይቶ የገቢ ማረጋገጫ ክፊያም ሊገባቸው ይችላል፡፡

ወደ እስራኤል ገንዘቦችን ስለማስገባት እና ከሀገር ስለማውጣቱ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

ሕገ_ወጥ የገንዘብ ዝውውርን የሚከለክለው ሕግ ክፍል 9 አንድ ሰው ወደ እስራኤል ሲገባ ወይም ሲወጣ የያዘውን ገንዘብ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። የገንዘቡ መጠን ሪፖርት ደረጃው ከ50,000 ሺቄል፣ እና 12,000 ሺቄል (በየብስ ድንበር ማቋረጫ) ከሆነ።

አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ከተጓዘ፣ በሚከተለው ጊዜ ሪፖርት ማድረግም ግዴታ ነው።

1. አንድ ተሳፋሪ ገንዘቡ ከሪፖርት ማቅረቢያ ገደብ በላይ የሆነ ገንዘብ የያዘ፣ ከሌላ ተሳፋሪ ጋር መጓዙ (የቤተሰብ አባልም ቢሆን) ከማሳወቅ ግዴታ ነፃ አያደርገውም።
2. የተለያዩ ተሳፋሪዎች እያንዳንዳቸው ከሪፖርት ማቅረቢያ ገደብ በታች የሆነ መጠን ሲይዙ እና አጠቃላይ መጠኑ ከሪፖርት ማቅረቢያ ገደብ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ገንዘቦችን በጋራ ባለቤትነት ይይዛሉ። ለምሳሌ፣ የቤተሰብ አባላት አብረው ሲጓዙ እና ገንዘቡ በጋራ የቤተሰብ አባላት ሲሆኑ።

የማሳወቅ ግዴታን በሚመለከት በማንኛውም ጥርጣሬ ከጉምሩክ/መክስ ሰራተኞች ጋር በድንበር ማቋረጫ ላይ ማማከር ይችላሉ።

ሪፖርቱን እንዴት ማስገባት እንደሚቻል ድረ-ገጹን ይመልከቱ - ወደ እስራኤል ገንዘብ ስለማስገባት እና ከአገር ውስጥ ስለማውጣቱ ሪፖርት ማድረግ (ቅጹ በዕብራይስጥ ፣ በእንግሊዝኛ ፣ በአረብኛ እና በሩሲያኛ ይገኛል)።

መርካዝ ቅሊጣ-የመጀመሪያው መጠልያ ቦታ-የመጀመሪያ መራመድ

የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች በእስራኤል የመጀመሪያ ጊዜያቸው በመርካዝ ቅሊጣ የመኖር ሙበት አላቸው። አዲስ ገቢዎች በመርካዝ ቅሊጣው የመጀመሪያ በእስራኤል ኑሮአቸውና መልመዳቸው ምቹ እንዲሆን ያደርጋል። መርካዝ ቅሊጣው በሶኽኑት ይሁዲት የአሊያና ቅሊጣ ክፍል ነው የሚተዳደረው። ከዚህ የመለማመድ ጊዜያቸው አዲስ ገቢዎች ወደ ቋሚ መኖሪያ ቤት ይመራሉ። በመርካዝ ቅሊጣው የመኖሩ ቅድመ ሁኔታ በሶኽኑት ይሁዲት አስተዳደርና አካሄድ መሰረት ነው። በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ለሚመጡት መኖሪያ መርካዝ ቅሊጣ በሚከተሉት ቦታዎች ይገኛሉ፡- ብኤር ሸባ ፣ንህሪያ ፣ ጽፋት ፣ ጥበሪያ ፣ ቅሪያት ጋትና ወ.ዘ.ተ።

በመርካዝ ቅሊጣ (ጊዜያዊ መጠለያ ቦታው) የመኖሩ ሂደት

ወደ መርካዝ ቅሊጣው ከመግባታችሁ በኋላ በተሰጥዋችሁ ቤቶች መደራጀት ትችሉ አላችሁ።

በዚሁ የማዕከሉ ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ይረድዋችኋል። በነዚህ በተሰጥዋችሁ ቤቶች እንደ (ቁም ሳጥን ፣ ፍሪዥ ፣ አልጋና ወ.ዘ.ተ) የመሳሰሉ መሰረታዊ ነገሮች ይገኛሉ። እንዲሁም እንደ ሳህን ፣ ማንኪያ ፣ ለአልጋ የሚያስፈልጉ ነገሮችና ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት የሚበቃ (የምግብ አስቤዛ እንደ ዳቦ ፣ ወተት ፣ ፍረፍሬና አትክልት ፣ የደሮ ስጋ ፣ የመሳሰሉና የጽዳት ማጸዳጃ ነገሮች ይሰጣችኋል። ኪራዩ በቅናሽ ዋጋ የሚሰጣችሁ ቤት በመከራየቱ ስምምነት ትፈርማላችሁ። ቦታ ተስጥቷችሁ ከያዛችሁና ከተደራጀችሁ በኋላ ስለ መርካዝ ቅሊጣው መረጃ በመቀበል ከሰራተኞቹ ጋር ትተዋወቁ አላችሁ። ከገባችሁ በኋላ በመጀመሪያው አንድ ሳምንት የምትኖሩበት ቦታ አካባቢ የማወቅ እየተዘዋወሩ ጉብኝት ይደረግላችበጉብኝቱ በአካባቢው የምገኙ እንደ ሱቆች ፣ የጤና ጣቢያ ፣ የልጆች መንከባከቢያየመሳሰሉት ቦታዎች ታያላችሁ ትተዋወቁ አላችሁ።

የመርካዝ ቅሊጣው የአቀባበል ቡድን አዲስ ገቢዎቹ በእስራኤል ማህበረሰብ ተዋህህደው የመኖሩ ፕሮግራም ያሰራል- ይተገብራል። አዲስ ገቢዎቹ ከህብረተሰቡ የተለያዩ የኑሮ አገልግሎቶች መስኮች ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በጊዜያዊው መኖሪያችሁ ማዕከል በምትቆዩበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃና የማወቅ ሰሚናሮች፣ ማህበራዊና ባህላዊ ድግሶችና የተለያዩ ነገሮች የማወቅ ትምህርት ይሰጣሉ። በየመጀመሪያው ኑሮ ፕሮግራም ከቦታው ወደ ቋሚ መኖሪያ ቤት መውጣቱ በተመለከተ ትምህርት ይሰጠል።

በጊዜያዊዉ የመኖሪያ ማዕከሉ ሰራተኞች ሶሻል ዎረከሮቹ ይገኛሉ። ሶሻል ዎረከሮቹ ለአዲስ ገቢዎቹ የማማከርና

አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በተመለከተ በተለይም ችግር ላላቸውና ቀውስ ላጋጠማቸው አዲስ ገቢዎች ግልጋሎት ይሰጣሉ። እንዲሁም ሶሻል ዎርከሮቹ እንደ ከቢጡዋኽ ልኡሚ ፣ የማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮና የማህበራዊ ዋስትና ማረጋገጫ አካላት ከመሳሰሉት የሚገባውን መብት መተግበር በተመለከተ ይረዳሉ።

የአዲሱ ኑሮ አማካሪዎች ለማማከርና መረጃ ለመሰጠት ወደ ጊዜያዊ መኖሪያ ማዕከሉ አልፎ አልፎ ነው የሚመጡት።

አስተዉሉ !

ችግር ላይ ላለመውደቅ ከጊዜያዊዉ መኖሪያ ማዕከል ሰራተኞች ጋር ሳትማከሩ በተለያዩ ጉዳዮችና ግዴታ ባላቸው ውሎች በማዋዋል ሊያስፈርሟችሁ ከሚሞክሩ የግል አካላት ጋር አትፈርሙ።

በእስራኤል በመጀመሪያዎቹ የቆይታ ቀናት

በጊዜያዊዉ የመኖሪያ ማዕከሉ በእስራኤል አዲሱ ኑሮአችሁ በተመለከተ አስፈላጊ ነገሮችን ታደርጋላችሁ። የማዕከሉ ሰራተኞች ከጎናችሁ ቆመው በሚያስፈለገው ጊዜ የመተርጎም አገልግሎት ይሰጥዋችኋል።

ማታወቂያ ማውጣት (መቀበል)

ዕድሜው ከ 16 ዓመት በላይ የሆነ የእስራኤል ዜጋ ሁሉ በየትም ወቅት ሁሉ ማታወቂያ መያዝ አለበት። ማታወቂያው ወደ መንግስታዊና ህዝባዊ ቢሮዎች በሄዱ ቁጥር ማንነትን የመለየት ሰነድ ነው። የተለያዩ ሰነዶች ለመቀበል ፣ በክኔሴት ምርጫና ወ.ዘ.ተ በመሳሱት ይጠቅማል።

በእስራኤል በመጀመሪያዎቹ የቆይታ ቀኖቻችሁ ወደ ህዝብ ምዝገባና ውጪ አገር የመጓዝ ቢሮ ሂዳችሁ ማታወቂያ ጠይቁ። ስትሄዱ የመኖሪያችሁ ማዕከል ሰራተኞች ይወስድዋችኋል። ከመሄዳችሁ በፊት አስቀድማችሁ በgovisit ኣፕሊኬሺን ወይም በስልክ ቁጥር *3450 ደውላችሁ ቀጠሮ ያዙ።

ማታወቂያ ለማውጣት የሚጠቅሙ ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ማታወቂያ ለማውጣት ወደ ህዝብ ምዝገባ (የኢሚግሬሺን የህዝብ ምዝገባ ክፍል) ይዛችሁት የምትሄዱ ጽሁፍ በአይር ማረፊያ ይሰጣችኋል
- የመብት ፈቃድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ ተደርጎ
- የፓስፖርት ፎቶ

በህዝብ ምዝገባና ውጪ አገር የመጓዝ ቢሮ ለስዎስት ወር የሚያገለግል ጊዜያዊ ማታወቂያ ይሰጣችኋል። ባዮመትሪክ ማታወቂያው በፖስታ በሁለት ሳምንት ውስጥ እንዲደትሳችሁ ተደርጎ ይላክላችኋል። ማታወቂያው ካልደረሳችሁ ወደ ህዝብ ምዝገባ ቢሮ ሂዳችሁ ጠይቁ።

አስተዉሉ !

አድራሻ፣ የቤተሰብ ሰታቱስ-ሁኔታ ፣ መውለድ በመሳሰሉት ለውጥ ከተፈጠረ የመታወቂያው ተያያዥ ወረቀት መለወጥ አለበት።

ማሳሰቢያ ! አዲስ ገቢ እስራኤል ከገባ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ በራባኑት የግቢ ምዝገባ ክፍያ የ40% ቅናሽ ይገባዋል።

በጤና ጣቢያ ምዝገባ

በመንግስት የጤና ዋስትና ህግ መሰረት የእስራኤል ዜጋ የሆነ ሁሉ የጤና ዋስትና አለው። የጤና አገልግሎት ለማግኘት ህል ከጤና ጣቢያዎቹ በአንዱ መመዝገብ ያስፈልጋል። በእስራኤል ላራት የጤና ጣቢያ ድርጂቶች ይገኛሉ። እነሱም ክላሊት፣ የስልክ ቁጥር፡- *2700 ፣ ማካቢ የስልክ ቁጥር፡- *3555 ፣ ምኡኼደት የስልክ ቁጥር፡-

በዚሁ መጽሄት የተለያዩ ቢሮዎች የሚያደርጉት እርዳታ በተመለከተም በከፊሉ መረጃ ሰጥተናል-ይገኝበታል። ለሙሉ መረጃ ጉዳዩ በሚመለከተው ቢሮ ጠይቁ።

የኢትዮጵያ አዲስ ገቢዎች እስራኤል ከገባችሁ ከ15 ዓመት በኋላ እርዳታ በተመለከተ በምትኖሩባቸው ከተሞች የሚገኙትን መዘጋጃ ቤቶች ጠይቁ ወይም ቀጥታ እርዳታው ወደ እሚሰጠው መንግስታዊ ቢሮ ሂዱ።

ከምትኖሩበት አካባቢ ተወካይ ጋር የመገናኘት መረጃ ለማግኘት ወደ እሚከተለው ሊንክ ግቡ፡-
https://www.gov.il/he/Departments/General/ath_contact

ወደ የእርዳታው መረጃ ለመግባት በሚከተለው ሊንክ ተጠቀሙ፡-
https://www.gov.il/he/departments/integration_program/govil-landing-page

መጽሄቱ በዕብራይስጥና አማርኛ በኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ለማንበብ ወይም መጽሄቱ ከድረ ገጹ ለማውረድ (down ለማድረግ) ወደ ሚከተለው ድረ ገጽ www.klita.gov.il ጉበታችሁ ወደ ገጹ ለመድረስ ተጭናችሁ "ለህዝብ መረጃ" ወደ ሚለው ርእስ ድረሱ። ለአዲስ ገቢ "በቋንቋው መረጃ" የሚለውን መርጣችሁ በአርእስቱ መሰረት መጽሄቱን አግኙት ወይም ወደ የኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የኢንተርነት ድረ ገጽ በኣማርኛ አድራሻው https://govextra.gov.il/moia/moia_amharit/home ግቡ።

ይህ መጽሄት ለእናንተ ሲባል በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በዕብራይስጥና አማርኛ የተሰራ መሆኑን አስተውሉ። የመጽሄቱመረጃ ወደ አማርኛ መተረጎሙ ለማወቅ ብቻ ያህል ነው። በዕብራይስጥ የተጻፈው ነው የሚወስነው። እንዲሁም በመጽሄቱ የተዘረዘሩት በተለያዩት የመንግስት ቢሮዎች ያሉት መብቶች ከፊሎቹ ለአጠቃላይ አዲስ ገቢዎች ሁሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ከኢትዮጲያ ለመጡት ብቻ የሚመለከቱ/የሚሆኑ ናቸው።

ከኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ጋር ግንኙነት የመፍጠር ዘዴዎች፡-

ስልክቁጥር፡- *2994 ወይም 03-9733333

በፋክስ፡- 072-3229697

ድረገጽ፡- www.klita.gov.il

በኣማርኛድረገጽ፡- https://govextra.gov.il/moia/moia_amharit/home

ኢሜል፡- info@moia.gov.il

አስተውሉ !

በዚህ መጽሄት የተጻፈው መረጃ ለማወቅ የሚረዳ ብቻ እንጂ የእርዳታ መብት እንዲኖር የሚያደርግ አይደለም። በእስራኤል የቆያችሁበት ጊዜ የቤተሰብ ለውጥ የመሳሰሉት መብቶቻችሁን በተመለከተ ተጽኖ ሊኖርባቸው ይችላል። ስለሆነም የሆነ ነገር ከማድረጋችሁ በፊት የሚገባችሁ መብት ካለ እወቁ።

የህግና እስተዳደር መረጃ መንግስታዊ ምንጮች መሆናቸውን በመግለጽ በሚቀርበው መረጃ ከህግና አስተዳደር ያልተመጣጠነ ስህተት ሊፈጥር ይችላል። እንዲሁም ትእዛዞቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ ሊኖርባቸው ይችላል። እንዲህ በመሰለ ሁኔታ በመጽሄቱ የሚገኘው መግለጫ ሳይሆን የሚወስነው ተጨባጩ ህግና አስተዳደር ናቸው። በተባዕት አነጋገር የተጻፈው መረጃው ሁለቱን ጾታዎች ይመለከታል።

በአየር ማረፊያ አቀባበል

በአየር ማረፊያ የሚሰጧዎችሁ ሰነዶች

የአዲስ ገቢ ማታወቂያ ወይም የመብት ፈቃድ

የአዲስ ገቢ ማታወቂያ / የመብት ማስታወሻው ለሚገባቸው ብቸኛ ወይም ቤተሰብ የሚሰጥ ሰነድ ነው። ማታወቂያው / ማስታወሻው አዲስ ገቢዎች በኑሮአቸው ሂደት በሚሰማሩበት ጊዜ የተደረገለቸው እርዳታ የሚጻፍበት ማታወቂያ ነው። ማታወቂያው የባለ መብቱ ፎቶ ይገኝበታል። የቤተሰብ በሆነ መታወቂያ የባሉና ሚስቱ ፎቶዎችና ከወላጆቻቸው ጋር እስራኤል የገቡ ዕድሚያቸው እስከ 21 ዓመት የሆነው ልጆች የልጆቻቸው ስም ይጻፋል። እድሚያቸው ከ 21 ዓመት በላይ የሆነ እና ያገቡ ፤ የተፋቱ፤ ባላቸው ፤ ሚስታቸው የሞቱባቸው ከሆኑ የየራሳቸው ፈቃድ ይሰጣቸዋል። የሚገባችሁን ለመቀበል ከኣሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ፤ ባንክ ፤ ቢጡዋኽ ልኡሚ ፤ እርዳታ በምትጠይቁበት በመሳሰሉት ጊዚያቶችና በጤና ጣቢያ በምትመዘገቡበት ወቅት ፈቃድ በእጃችሁ መገኘቱ አስፈላጊ ነው።

አስተውሉ !

እርዳታ የሆነ ሁሉ በቤተሰብ ቁጥር(ብዛት) እና በልጆቹ እድሜ መሰረት ስለሚሰጥ በመለያ ፈቃዱ የሚያስፈልገውን ሁሉ በትክክል መጻፉ አረጋግጡ። በመውለድ ፤ መጋባት ፤መፋታት ፤ ወይም ሞት ምክንያት በቤተሰቡ ለውጥ ከተፈጠረ የሚያሰፈልጉትን ሰነዶች ይዛችሁ ወደ አሊያናቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ በመሄድ ለውጡን አስመዝግቡ።

የህዝብ ምዝገባ ፎርም

ማታወቂያ ለመቀበል ከህዝብ ምዝገባ ቢሮ (የኢሚግሬሺን የህዝብ ምዝገባ ክፍል) ስትሄዱ ይዛችሁት የምትቀርቡ የምዝገባ ፎርም አየር ማረፊያ እንደደረሳችሁ ይሰጣችኋል።

በጤና ጣቢያ ምዝገባ

የጤና አገልግሎት ያለ መተጓጎል እንድታገኙ (እንዲኖራችሁ) አየር ማረፊያ እንደደረሳችሁ በምትመርጡት ጤና ጣቢያ መመዝገብ ትችላላችሁ። በአየር ማረፊያ ካልተመዘገባችሁ ከዛ በኋላ በአንዱ ፖስታ ቤት ወይም በቢጡዋኽ ልኡሚ ድረ ገጽ መመዝገብ ትችላላችሁ።

የመጀመሪያው የገንዘብ እርዳታ

ሳል ሀቅሊጣ የሚባለው የመጀመሪያው የገንዘብ እርዳታ በኣይር ማረፊያ ይሰጣችኋል። ሳል ሀቅሊጣ የሚባለው የገንዘብ እርዳታ በእስራኤል የአንድ ዓመት ቆይታችሁ ለኑሮአችሁ የሚሰጥ ገንዘብ ነው። በአየር ማረፊያ የሚሰጣችሁ የመጀመሪያው ክፊያ በጥሬ ገንዘብ (በካሽ) ሲሆን ከዛ በኋላ ወደ የባንክ ሂሳባችሁ እየተላከ ይሰጣችኋል።

በአየር ማረፊያ ተጨማሪ አገልግሎቶች

በአይር ማረፊያ በሚገኘው የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የሚጠብቋችሁ ተጨማሪ አገልግሎቶች፡-

- የእናቶች ክፍል-የህጻናት መንከባከቢያ ፤ ማጥቢያና የጽዳታቸው ጨርቅ መቀየሪያ
- እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አካለ ስንኩል ወይም እራሳቸው በራሳቸው መርዳት ለማይችሉ ነርስ
- በእስራኤል አገር ለሚገኙ ቤተሰቦቻችሁ መደረሳችሁ ለማሳወቅ በነጻ የስልክ አገልግሎት
- ቁርስ
- በእስራኤል የምትነጋገሩበት የሞባይል ሲምም ሊሰጣችሁ ይቻላል

በምዝገባውና ሰነዶችን በመቀበል የመረካዝ ቅሊጣው ሰራተኛ የሚረዳችሁ ሲሆን ከዛ በሁኋላም በእስራኤል ወደ መጀመሪያው መኖርያ ቤታችሁ ሁላችሁም ባአንድ ለይ በማኪና ይወስዳችኋል።

איסור הטעיה והפעלת השפעה בלתי הוגנת	75	ማሳሳትና ተገቢ ያልሆነ ተጽኖ ከልከል ስለመሆኑ
מה ניתן לעשות במקרה של הפרת חוק הגנת הצרכן	76	የገዢዎች መብት እንዲከበር የሚያደርግ ተከላካይ ህጉ ሲጣስ ምን ማድረግ ይቻላል
פניות ותלונות למשרד העלייה והקליטה	**76**	**የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ መጠየቅና ክስ ማቅረብ**
תלונות למשרד מבקר המדינה על גופים ציבוריים	**77**	**ህዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት በሀገሪቱ የቁጥጥር ባለስልጣን መክሰስ**
רגע מזמנך!	**78**	**!ከጊዜህ አንዲት ደቂቃ**
כתובות וטלפונים	**83**	**አድራሻዎች እና ስልኮች**

መግቢያ

ውድ አዲስ ገቢዎች !

እስራኤል አገር እንኳን ደህና መጣችሁ !

አዲሱ ኑሮአችሁ ጥሩና የተሳካ እንዲሆንላችሁ እንመኝላችሁ አለን::

እስራኤል መግባት በኑሮ ሁሉም ያካተተ አዲስ ጅምር ነው:- አዲስ ቋንቋ ፤ ቤትና ስራ ማግኘት ፤ ልጆች ወደ ት/ቤት ሲሄዱ መሸኘት ፤ በማህበረ ሰቡ ኑሮ መሰማራትና ወ.ዘ.ተ ...የአዲስ ገቢዎች የአሊያና ቅሊጣ ቢሮ በእስራኤል ኑሮአችሁ የተለያዩ መጀመሪያ መራመዳችሁ በመተባበር ይረዳችኋል::

በእስራኤል ኑሮአችሁ ሂደት ላይ እስራኤል በተለያዩ መስኮች እርዳታ ታደርግላችሁ አለች:- ቤት ፤ ስራና ትምህርት በመሳሰሉ እርዳታው በአዲስ ገቢዎች ቢሮና በሌሎች መንግስታዊ ቢሮዎችና ማዘጋጃ ቤቶች ፤ የገቢዎች ቢሮ ፤ መከላከያ ሰራዊት በመሳሰሉ::

በዚሁ የመረጃ ጽሁፍ የተለያዩ እርዳታዎች በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ ይሰጣችኋል:: እርዳታዎቹ የመቀበላቸው ቅድመ ሁኔታና ለመቀበላቸው እናንተ ምን ማድረግ እንዳለባችሁም በሚል::

እስራኤል በሀገሪቱ የመጀመሪያው ኑሮአችሁ መርካዝ ቅሊጣ በሚባልጊዚያዊ መጠለያ እንዲሆን ታደርጋለች:: በቦታው በእስራኤል ኑሮአችሁ መልካም እንዲሆን በሚያስፈልጋችሁ ሁሉ እርዳታ ይደረግላችኋል:: በምትኖሩበት የአዲስ ገቢዎች መጠለያ ማዕከል የአዲስ ገቢዎቹ ቢሮ የግል አማካሪ ይሰጣችኋል::አማካሪው የሚገባችሁን እርዳታ በተመለከተና እናንተ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ በሚል አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ይሰጣችኋል:: የቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ሰራተኛ ማድረግ ባለባችሁ ሁሉ ከጎናችሁ ቆሞ ይረዳችኋል:-የባንክ ሂሳብ መክፈት፤ ልጆችን በትምህርት ቤቶች ማስመዝገብ በሚል ሁሉ::

በመጠለያው ማዕከል በምትቆዩበት ጊዜ የእብራይስጥ ቋንቋ እና የጊዩር ትምህርት ኡልፓን ትማሩ አላችሁ:: ትምህርቱን ከጨረሳችሁ በኋላ ከናንተ ጋር በመተባበር የስራ ፕሮግራም ተሰርቶ እንዴት በስራ ቦታ መሰማራት እንዳለባችሁ እገዛ ይደረግላችኋል::

ከኑሯችሁ አማካሪ ጋር በምትገናኙበት ወቅት ጎን ለጎን በአዲስ ገቢዎች ቢሮ የግል ድረ ገጽ ብትመዘገቡ ይመረጣል:: መመዝገባችሁ በቅሊጣ ሚኒስቴር ቢሮ በኩል የተደረገላችሁ የእርዳታ ክፍያዎች በቀጣይም ምን እንደሚገባችሁ በተመለከተ መረጃ እንዲሰጣታችሁ ያደረጋል:: እንዲሁምበግላችሁ ድረ ገጽ (ሳይት) በኩል በቋንቋችሁ ወደ የኑሮአችሁ አማካሪ በአን-ላይን መልእክት መላክ ትችላላችሁ:: ወደ የግል ድረ ገጹ መመዝገቡ እንዴት እንደሆነ መረጃ በቢሮው ድረ ገጽ በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል:-
https://www.gov.il/he/service/private-area-new-immigrants-and-returning-residents

በዚህ መግለጫ የሚያስፈልጓችሁ ዋና ዋና መረጃዎች እናቀርባለን:: ሰፋ ላለተጨማሪ መረጃ ወደ ሚከተለው ቢሮና አማርኛን ጨምሮ በተለያዩ ቋንቋዎች ወደ አለበት ሌላ ተጨማሪ ደረ ገጽ ግቡ::

ከአዲሱ ኑሯችሁ አማካሪ ጋርም ተነጋገሩ:: ከየአሊያና ቅሊጣ ቢሮ መግለጨዎች ተጨማሪ መረጃ መቀበል አለባችሁ:: በተለያዩ መግለጨዎች የሚገኙበት የጽሁፍ ዝርዝርና የጥሪ ፎርም በጽሁፉ መጨረሻ ላይ ይገኛል::

እስራኤል ከደረሳችሁ እስከ 15 ዓመት ድረስ የሚገባችሁ እርዳታ ከሌሎች መንግስታዊ ቢሮዎች በመተባበር በአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ ሀላፊነት መሆኑ አስታዉሱ :: አዲስ ገቢ በመሆናችሁ በተጠቀሱት ዓመታት የሚገባችሁን ሁሉ በተመለከተ ወደ ቅሊጣና አሊያ ቢሮ በመሄድ ጠይቁ::

በኣሊና ቅሊጣ ቢሮ የሚደረግላችሁ እርዳታ እስራኤል ከገባችሁ ከ15 ዓመት በኋላ ያበቃል:: ከአበቃ በኋላም አዲስ ገቢ ያልሆነ ሁሉ ዜጋ እንደሚቀበለው እርዳታ እንደሚደረግለት ከመንግስታዊ ቢሮዎች ይደረግላችኋል:: እየአንድ አንዱ ቢሮ በሀላፊነቱ ስር በሆነ ሁሉ ይረዳል:- ቤትን በተመለከተ የግንቢታና ቤት ዕደላ መምራት(መሰጠት) ቢሮ እርዳታ ያደርጋል:: ለነጋዲዎች የኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፣ የጤና አገልግሎትጤና ጥበቃ ቢሮ፣የኑሮ ምቾትና የጠሮተኞች አገልግሎት ፣ የምቾትና ማህበራዊ ኑሮ ማረጋገጫ ቢሮ ፣ በስራ የስራ ቢሮና ወ.ዘ.ተ...

ለሳይንቲስቶች፣ ለአርቲስቶችና እስፖርተኞች እርዳታ	38
በስራ ሚኒስተር ቢሮ በኩል በስራ ላይ የማሰማራት ፕሮግራም	39
የሰራተኞች መብት	40
የስራ እቅድ	**41**
የስራ ፕሮግራም የማውጣት ማበረታቻ የአሊያና ቅሊጣ ቢሮ እርዳታ	41
የንግድ ድርጀት በማቋቋም የኢኮኖሚና ኢንዱስትሪ ሚኒስተር ቢሮ የማበረታቻ እርዳታ	43
በሳይንስ ስራ ማስያዝ (መስጠት) ማዕከል	**43**
ሳይንትስቶች ለስራ መቀበል	43
ለምርምር ተማሪዎች ስኮላርሺፕ	44
የጤና አገልግሎት	**44**
መንግስታዊ የጤና ዋስትና ህግ	44
በጤና ጥበቃ አገልግሎት ለአዲስ ገቢዎች ቅናሽ ከፊፍያ	44
የልጆች የጤና አግልግሎት	45
የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት	46
በተለያዩ ቋንቋዎች የሚሰራ (የሚመልስ) የስልክ ማዕከል	47
ትምህርት	**48**
ለአዲስ ገቢዎች ተማሪዎች እርዳታ	48
ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ	**50**
የአስተዳደሩ ለአዲስ ገቢዎች ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እርዳታ	50
ከከፍተኛ ትምህርት ኮሚቴ (ኮውንስል) እርዳታ	54
በመከላከያ ሰራዊት አገልግሎት	**55**
ከወታደርነት ምልመላ በፊት	55
መደበኛው አገልግሎት	56
ለወታደሮች እርዳታ	56
ሰዩ ለሕፃናት	56

ወደ ፊት (በሚቀጥለው) ወታደርነት የሚያገለግሉ አዲስ ገቢዎች ወታደራዊ አገልግሎት	58
ብሄራዊ ሲቪላዊ አገልግሎት	58
መንጃ ፈቃድ	**59**
የውጪ መንጃ ፈቃድ ወደ እስራኤል መንጃ ፍቃድ መለወጥ	59
በእስራኤል አገር መንጃ ፈቃድ ማውጣት	60
የብሄራዊ ዋስትና ተቋም (ሀሞሳድ ልቢጡዋኽ ልኡሚ)	**61**
የቢጡዋኽ ልኡሚ እና የጤና ዋስትና ከፊያ	61
ለጠሮተኞችና ለሌላ የሚገባቸው ከፍያ	62
የምቹ ኑሮ አገልግሎት (ሺሩቴይ ርቫኽ)	**68**
በመርካዝ ቅሊጣ የምቹ ኑሮ አገልግሎት	68
በመዘጋጃ ቤቶች የደህና ምቹ ኑሮ አገልግሎት	68
የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር ቢሮ የደህና ምቹ ኑሮ አገልግሎት	68
ጠሮተኞች	**70**
የጠሮተኛ ፈቃድ (ማታወቂያ)	70
የገቢ መረጋገጫ ከፍያ ለሚከፈላቸው ተጨማሪ ነገሮች	71
የጽዮን እስረኞችና በባእድ መንግስታት የተገደሉት	**72**
እውቅና እና መብቶች	72
ክብር	72
ለመረጃና ግንኙነት ለመፍጠር	72
እስራኤል ለመድረስ በመንገዳቸው/ጉዞኣቸው ሂወታቸው ያጡ ታሪክ ዘላኣለማዊ ማድረግ	73
በግር ብልህ መሆን	**73**
ኢቃ ከተገዛ በኋላ ግዢውን መሰረዝ	74
ኢቃው ከተሸጠ በኋላ የሚኖሮው ሃላፊነትና አገልግሎት	75

תוכן העניינים

מבוא	**7**
קליטה בנמל התעופה	**9**
מרכזי הקליטה – צעדים ראשונים	**10**
תהליך הקליטה במרכז הקליטה	10
פעולות חשובות בימים הראשונים בארץ	11
אולפנים ללימוד עברית ולגיור	15
סיוע במצבי מצוקה	16
עזיבת מרכז הקליטה	17
מעבר לדיור קבע	**18**
מענק דיור לרכישת דירה	18
סיוע בשכר דירה ליחידים ולקשישים	19
הליך קבלת מענק הדיור ורכישת הדירה	19
דיור ציבורי	22
ריכוז תחומי הסיוע הכספי ממשרד העלייה והקליטה	**23**
הקלות במכס	**26**
הקלות במס הכנסה	**30**
תעסוקה	**31**
הערכת תארים אקדמיים מחו"ל	31
קורסים לקידום מקצועי	33
תוכנית תעסוקתית אישית	34
קבלת רישיון לעיסוק במקצועות המחייבים רישיון ישראלי	35
חיפוש עבודה	38

משרד העלייה והקליטה
የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስቴር

מדריך מידע וזכויות ליוצאי אתיופיה

ከኢትዮጵያ ለመጡት የመብቶች መረጃ

הופק על ידי אגף א' מידע ופרסום
משרד העלייה והקליטה

מנהלת האגף: **אידה בן שיטרית**
תחקיר: **אשר שטוך ורחל חדד**
עריכת לשון בעברית: **רחל חדד**
תרגום לאמהרית: **אברהם ירדאי**
מספר קטלוגי: 1313423010

© כל הזכויות שמורות
ירושלים 2023

www.klita.gov.il
info@moia.gov.il
מרכז מידע טלפוני ארצי:
*2994 | 03-9733333

הודפס על ידי המדפיס הממשלתי
צילום העטיפה:
באדיבות לע"מ, אלעד זגמן, 2022

በመረጃና ገለጻ ክፍል የተዘጋጀ
የአሊያና ቅሊጣ ሚኒስተር

የክፍሉ ሀላፊ፡- **ኢዳ ቤን ሺጥሪት**
ጥናትና ቁጥጥር፡- **አሸር ሺጡኽና ራሼል ኻዳድ**
የዕብራይስጡ ቋንቋ ኤዲተር፡- **ራሼል ኻዳድ**
ከዕብራይስጥ ወደ አማርኛ ተርጓሚ፡- **አብርሀም ይርዳይ**
መለያ ቁጥር፡- 1313423010

© መብቱ ሁሉ የተጠበቀ ነው
እየሩሳሌም 2023

www.klita.gov.il
info@moia.gov.il
የስልክ አገር አቀፍ መረጃ ማዕከል፡-
*2994 | 03-9733333

በመንግስታዊው ፕሪንተሩ ታተመ

לידיעתכם,

מדריך מידע וזכויות ליוצאי אתיופיה מוגש לנוחיותכם בחוברת זו בשתי שפות: עברית ואמהרית.
שימו לב כי שתי השפות בחוברת זו מופיעות ברצף אחת אחרי השנייה לעיונכם.

משרד העלייה והקליטה
የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስቴር

ከኢትዮጵያ ለመጡት የመብቶች መረጃ

"ማዶራ እርሾና"- የመጀመሪያ ማህዶራ

משרד העלייה והקליטה
የዓልያና ቅሊጣ ሚኒስቴር



ከኢትዮጵያ ለመጡት የመብቶች መረጃ

מדריך מידע וזכויות ליוצאי אתיופיה

אמהרית | עברית